# አዲስ ዘመን

ሰኞ 81ኛ ዓመት ቁጥር 339 ነሐሴ 9 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ለሚርተኞች አፍራሽ ሃሳብ ቁብ ሳይሰጥ አገርን በሚያበለጽጉ ስራዎች በንቃት እንዲሳተፍ ጥሪ ቀረበ

## - በድሬዳዋ የተከፈተው ነጻ የንግድ ቀጠና ተመርቋል

**ጌትነት ምህረቴ**

ድሬዳዋ፡- እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ለሟርተኞች አፍራሽ ሃሳብ ቁብ ሳይሰጥ አገርን በሚያበለጽጉና ወገንን በሚጠቅሙ ስራዎች በንቃት መሳተፋ እንደሚኖርበት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ አሳሰቡ፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በድሬዳዋ የተከፈተውን ነፃ የንግድ ቀጠና መርቀው ከፍተዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በድሬዳዋ የተከፈተውን ነጻ የንግድ ቀጠና በትናንትናው እለት መርቀው ሲከፍቱ እንደተናገሩት፤ ነፃ የንግድ ቀጠና የወጪና የገቢ ንግዳችንን በማቀላጠፍ ዕድገታችንን ለማሳለጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

ሌሎች አገራት ነፃ የንግድ ቀጠና ከፍተው የዕድገታቸው አጋዥ አድርገው መጠቀም ከጀመሩ ብዙ ዓመታትን አስቆጥረዋል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ እኛም ነፃ የንግድ ቀጠና መከፈታችን ዕድገታችንን ለማሳለጥ ያስችለናል ብለዋል፡፡ በድሬዳዋ የተከፈተው ነፃ ንግድ ቀጠና ጠቀሜታና አዋጭነቱ እየታየ ወደ ሌሎቹ የአገሪቱ ክፍሎች እንደሚሰፋም ተናግረዋል፡፡

ነፃ የንግድ ቀጠናው መጀመር በተለይ እያደገ የመጣውን የግብርና ምርት ቀጣይነት እንዲኖረው ያደርጋል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የንግድ ሰንሰለቱን በማቀላጠፍ የኢትዮጵያን አምራችነት ይበልጥ እንደሚያጠናክርም ገልጸዋል፡፡

ነጻ የንግድ ቀጣናው የኢትዮጵያን መጻኢ ብልጽግና እውን ለማድረግ የሚያግዝ ጅማሮ መሆኑን ጠቁመው፤ ነጋዴዎች በድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጠና በመሳተፍ ራሳቸውንና አገራቸውን ሊጠቅሙ እንደሚገባ አስገንዝበዋል፡፡

ነጻ የንግድ ቀጣናው በግብርናው ዘርፍ እየተመዘገበ ላለው የምርት እድገት ምቹ ገበያ ለመፍጠር፥ ኢንቨስትመንትንና

እያንዳንዱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








# “አልሸባብ ላይ የተወሰደው እርምጃ ሽብርተኝነትን በመከላከል ረገድ እንደሀገር ያለውን አቅም ያሳደገ ነው”

## - ዶክተር በሽር አብዱላሒ የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- ሕዝብንና የጸጥታ ኃይሉን በማስተባበር አሸባሪው የአልሸባብ ቡድን ላይ የተወሰደው እርምጃ ሽብርተኝነትን በመከላከል ረገድ እንደአገር ያለውን አቅም ያሳደገ ነው ሲሉ የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር በሽር አብዱላሂ ተናገሩ።

ዶክተር በሽር አብዱላሂ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት እንደተናገሩት፤ በሶማሌ ክልል ሊገባ ያሰበው አሸባሪው አልሸባብ ቡድን በሕዝብና የጸጥታ ኃይል ጥምረት ተገቢው መልስ ተሰጥቶታል። የተወሰደው እርምጃ እንደሀገር ያለንን ሽብርተኝነት የመከላከል አቅም ያሳደገና ሉአላዊነታችንን ያስከበረ ነው።

"አልሻባብ ላይ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## በአራት ዓመታት 25 ቢሊዮን ችግኞች ተተክለዋል

# አረንጓዴ አሻራው የግብርና ምርታማነትን በማሳደግ ረገድ ለውጥ እያመጣ መሆኑ ተገለጸ

**ጌትነት ምህረቴ**

ድሬዳዋ፡- ኢትዮጵያ በአራት ዓመታት በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር 25 ቢሊዮን በላይ ችግኝ መትከሏ ስኬታማ ውጤት መሆኑን የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ፡፡ የተተከሉ ችግኞች የአየር ንብረት ተጽዕኖን በመቋቋምና የግብርናን ምርታማነት በማሳደግ ረገድ ለውጥ እያመጡ እንደሆነም ጠቅሰዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ትናንት በድሬዳዋ ከተማ በተካሄደው አራተኛው የአረንጓዴ አሻራ ማጠቃለያ መርሀ ግብር ላይ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ በአራት ዓመታት በአረንጓዴ አሻራ ያስገኘችው ውጤት ስኬታማ ነው፡፡

የአረንጓዴ አሻራ ውጤት የደን ሽፋንን ከማሳደግ ባለፈ ምርታማነት እንዲጨምር ማድረጉን አመልክተው፤ የምግብ ዋስትናን በአስተማማኝ መልኩ ለማረጋገጥ በፍራፍሬ ችግኞች ላይ ማተኮር ይኖርብናል ብለዋል፡፡

‹‹ከልማት ስራችን የሚያስቆመን ምንም ነገር የለም›› ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የኢትዮጵያን ብልጽግና ለማረጋገጥ ሁለንተናዊ ጥረት እያደረግን እንገኛለን ፤ የምናሳካው ነውም ብለዋል፡፡

በቀጣይ የአረጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ለገበያ በሚውሉ ችግኞችና ጥራት ላይ በማተኮር ስንዴ ብቻ

በአራት ዓመታት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









ዜና

# በከተማዋ ከ30ሺ በላይ ወጣቶች በክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ተሰማርተዋል

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ ፡- በአዲስ አበባ በአስራ አንዱም ክፍለ ከተሞች ከ30 ሺህ በላይ ወጣቶች በቋሚነት በክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተሰማርተው እንደሚገኙ የአዲስ አበባ ወጣቶች ማሕበር ገለጸ።

የአዲስ አበባ ወጣቶች ማሕበር ዋና ፀሐፊ አቶ ይሁነኝ መሀመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በጎነት ሰው ለሌሎች ማድረግ ከሚችለውና ከተረፈው ብቻ ሳይሆን ካለው ላይ የሚያደርገው ሰብዓዊ ተግባር ነው። በአዲስ አበባ በአስራ አንዱም ክፍለ ከተሞች ከ30 ሺህ በላይ ወጣቶች በቋሚነት በክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተሰማርተው ይገኛሉ።

በዘንድሮ ክረምት በከተማዋ ከ30 ሺህ በላይ ወጣቶች በቆሻሻ ማጽዳት፣ በችግኝ ተከላ፣ የትራፊክ ፍሰቱን የተሳለጠ ለማድረግ በማስተባበር፣ በሰላምና ጸጥታ ስራና በመሳሰሉት በጎ ተግባራት መሰማራታቸውን ጠቁመው፤ ይህም የበጎ ተግባር አገልግሎቶች በገንዘብ ሲተመን ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ የሚገመቱ መሆናቸውን ተናግረዋል።

የአዲስ አበባ ወጣቶች ማሕበር የወጣቶች የበጎ ፈቃድ ተግባርን መሰረት አድርጎ ከተቋቋመ 25 ዓመታት ማስቆጠሩን አስታውሰው፤ ሁሉም ሰው በበጎ ፈቃድ ሥራ መሳተፍ አለብኝ ብሎ እንዲያስብ እና ባህል እንዲሆን የሚያስችሉ ተግባራትን እየሰራ ይገኛል ብለዋል።



**አቶ ይሁነኝ መሀመድ**

ማሕበሩም የአቅመ ደካማ ቤቶችን በማደስ፣ ማዕድ በማጋራት፣ በችግኝ ተከላ እና እንክብካቤ፣ በክረምት የወጣቶች ማጠናከሪያ ትምህርት በመስጠት፣ በደም ልገሳና መሰል የበጎ ተግባራት ስራዎችን በየዓመቱ በክረምት ወቅት ዋና ስራው አድርጎ እያከናወነ መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ አቶ ይሁነኝ ገለጻ፤ ሰው ሙሉ የሚሆነው ስላለው ሳይሆን ለወገኑ ሲሰጥ፣ ሲያግዝ፣ ሲተባበርና ለሌሎች ማድረግ ሲችል ነው። ማሕበሩም በግጭት የተፈናቀሉ ዜጎችን ከመደገፍ ጀምሮ የተለያዩ በጎ ተግባሮች ሲያደርግ ቆይቷል።

በጎ በማድረግህ ደስታን የምታገኝበት ነው ያሉት አቶ ይሁነኝ፤ ወጣቶች ከበጎነት የሚገኘውን ሥነልቦናዊ እርካታ ለማግኘት እያደረጉት የሚገኘው ተግባር የሚደነቅ ነው ብለዋል።

በበጎ ተግባር የተሰማሩ ወጣቶች የአቅመ ደካማ ቤቶችን ለማደስ በሚያደርጉት ጥረትም የገንዘብና የግብዓት ድጋፍ የሚያደርጉት ተቋማትንና ሕብረተሰቡ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ደም መስጠት በገንዘብ የሚተካ ሳይሆን ሕይወት የማዳን ስራ መሆኑን የገለጹት አቶ ይሁነኝ፤ በጎ ፈቃደኛ ወጣቶች ደም በመለገስ የብዙዎችን ሕይወት የማዳን ተግባር የፈጸሙ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ወጣት ማሕበሩ ሀገር ተረካቢ ወጣቶችን ከማፍራት አኳያም በክረምት ወራቱ በቤታቸው የሚገኙ በርካታ ተማሪዎች ጊዜያቸውን በአልባሌ ቦታ እንዳያሳልፉ ከማድረግ በተጨማሪ በገንዘብ የማይተመን የማጠናከሪያ ትምህርት የመስጠት ስራ እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአደጉ አገራትም የክረምት፣ የበጋ በሚል የራሳቸው የበጎ ፈቃድ ዘመቻዎች እንዳላቸው ያስታወሱት ሃላፊው፤ በቋሚነት ሰውን ለማገዝ ተደራጅተው የሚሰሩ እንዳሉም ገልጸዋል። እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ታዳጊ አገራትም ብዙ የበጎ አድራጎት ስራ የሚጠይቁ በርካታ ተግባራት መኖራቸውን አብራርተዋል።

የወጣት ማሕበሩ ቀጣይ ትኩረትም በበጎ ፈቃድ ስራ የከተማዋ እና የሀገራችን ሰላምና ጸጥታ ማስጠበቅ፣ የወጣቶችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ እና የለማች አገር ለማድረግ በሚደረገው ሁለተናዊ ጥረት ወጣቱ ጉልህ ተሳታፊ እንዲሆን ማሕበሩ በትኩረት እደሚሰራም ጠቁመዋል፡፡

# በበጀት ዓመቱ በመንገድ ትራፊክ አደጋ አራት ሺህ የሚጠጋ የሰው ሕይወት ጠፍቷል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በ2014 በጀት ዓመት በመንገድ ትራፊክ አደጋ 3 ሺህ 971 ሰዎች ሕይወታቸው ማለፉን የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት አስታወቀ።

አገልግሎቱ በ2014 በጀት ዓመት በመንገድ ደህንነት ዙሪያ የተከናወኑ ስራዎችንና የተገኙ ውጤቶችን፣ በአገር አቀፍ ደረጃ የደረሰውን የትራፊክ አደጋ መረጃና በቀጣይ ሊሰሩ የታሰቡ ስራዎችን አስመልክቶ ሰሞኑን ጋዜጣዊ መግለጫ ተሰጥቷል።

የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ጀማል አባሶ እንደገለጹት፤ በ2014 በጀት ዓመት 3 ሺህ 971 የሞት አደጋ የደረሰ ሲሆን ከ2013 ተመሳሳይ ዓመት ጋር ሲነጻጸር በ4 ነጥብ 6 በመቶ ቀንሷል። እንዲሁም በ2014 በጀት አመት አጠቃላይ ሞትና የአካል ጉዳት 14 ሺህ 621 ሲሆን ከ2013 ተመሳሳይ ዓመት ጋር ሲነጻጸር በ4 ነጥብ 1 በመቶ እንደቀነሰ ገልጸዋል።

ባለፉት አራት ተከታታይ ዓመታት የትራፊክ አደጋ የመቀነስ አዝማሚያን እያሳየ ነው ያሉት አቶ ጀማል፤ በ2010 ዓ.ም በ10 ሺህ ተሽከርካሪ 54 ነጥብ 7 በመቶ የነበረው የሰው ሞት በ 2014 ዓ.ም 29 ነጥብ 7 ማድረስ መቻሉን ገልጸዋል። እንዲሁም በ2014 በጀት ዓመት ስምንት መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰላሳ ሁለት ተሽከርካሪዎች አስገዳጅ የ3ኛ ወገን የመድን ሽፋን እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል። ለሃያ ስድስት ሺህ አራት መቶ ዘጠና ዘጠኝ የተሽከርካሪ አደጋ ተጎጂዎች ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል ብለዋል።

እንደ ዋና ስራ አስፈጻሚው ገለጻ፤ በአገር አቀፍ ደረጃ አደጋ አምጪ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በማተኮር በአልኮል ቴስተር በመታገዝ የተጠናከረ ቁጥጥር ማድረግ ተችሏል። ጥፋቶች ላይ የተገኙ ተሽከርካሪዎች እንደየጥፋታቸው መጠን የተቀጡ ሲሆን በዚህም ከ141 ሚሊዮን ብር በላይ ለመንግሥት ገቢ ሆኗል።

ከክልሎች፣ ከከተማ አስተዳደር የትራንስፖርትና የትራፊክ ፖሊስ አባላትና ከፌዴራል ትራፊክ ፖሊስ ጋር በመቀናጀት በበጀት ዓመቱ ለአደጋ አጋላጭ በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ በማተኮር ሕግን የማስከበርና የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራዎች መከናወናቸውንም ዋና ስራ አስፈጻሚው ተናግረዋል።

እንዲሁም ነጻ የእግረኞች ቀን፣ የመንገድ ለሰው ቀንና ከጳጉሜ አስከ ጳጉሜ እንደርሳለን የሚሉ መሪ ቃሎችን በመጠቀም በድግግሞሽ ለ55 ሚሊዮን ዜጎችን በመንገድ ትራፊክ ደህንነት የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የማድረግ ስራዎች መከናዎናቸውን ገልጸዋል።

የፐብሊክ ሰርቪስ ድርጅት ከ460 በላይ ተሽከርካሪዎችን በየቀኑ ለአገልግሎት እንደሚያስማራ የገለጹት ዋና ስራ አስፈጻሚው፤ ዓመቱን ሙሉ ምንም አይነት አደጋ አለማድረሱን በአድናቆት ገልጸዋል። ሌሎች የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት የዚህን ተቋም አርያ በመከተል ራሳቸውንን ንብረታቸውን ከአደጋ እንዲጠብቁ አሳስበዋል።

በመጪው የ2015 በጀት ዓመት በ10 ሺህ ተሽከርካሪዎች የደረሰን የ29 ነጥብ 7 በመቶ የሰው ሞት ወደ 28 ለማድረስ፣ አደጋ አምጪ የሆኑ ጉዳዮችን በመለየት የቁጥጥርና የግንዛቤ ፈጠራ ስራዎችን ከሕብረተሰቡ፣ ከአሽከርካሪዎች ጋር በቅርበት በመስራት ከመንገድ ትራፊክ አደጋ የተጠበቀ ሕብረተሰብ ለመፍጠር እንደሚሰራ አቶ ጀማል በመግለጫቸው አስረድተዋል።



# በዞኑ በጎርፍ ይደርስ የነበረውን የዜጎች መፈናቀል ማስቀረት እንደተቻለ ተገለጸ

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- በደቡብ ጎንደር ዞን በሚገኙት የርብና ጉማራ ተፋሰሶች ዙሪያ በ60 ሺህ እማና አባወራዎች ላይ በክረምት ጎርፍ ይደርስ የነበረን የመፈናቀልና የንብረት ጉዳት ማስቀረት መቻሉን የአማራ ዲዛይንና ቁጥጥር ስራዎች ድርጅት አስታወቀ፡፡

የአማራ ዲዛይንና ቁጥጥር ስራዎች ድርጅት ፕሮጀክት ማናጀር ኢንጂነር ዘመኑ ሙሉነህ እንደገለጹት፣ በተከታታይ ዓመታት ከፌዴራል አስከ ክልል ድረስ በተቀናጀ የተፋሰስ ልማት በተሰራው ስራ በደቡብ ጎንደር ዞን በሚገኙት ሶስት ወረዳዎች አዋሳኝ የርብና ጉማራ ተፋሰሶች ዙሪያ በየክረምቱ በጎርፍ ሙላት ይደርስ የነበረውን የ60 ሺህ እማና አባወራዎችን የመፈናቀልና የንብረት ጉዳት ማስቀረት ተችሏል፡፡

የጎርፍ መከላከል ስራው በየዓመቱ ከሚያስፈልገው የግብዓት ስፋት አኳያ ከፍተኛ ቅንጅታዊ ርብርብ ተደርጓል ያሉት ኢንጂነር ዘመኑ፤ በትግበራው ተጋላጭ ቦታዎችን ቅድሚያ መለየታቸውን ተናግረዋል፡፡ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የችግሩን አሳሳቢነት ተረድተው ባደረጉት የርብርብ ስራ በየዓመቱ ይከሰት የነበረውን የሕብረተሰብ መፈናቀል፣ ሰብዓዊና ቁሳዊ ጉዳት በዚህ ዓመት በከፊልና ሙሉ በሙሉ መከላከልና መቀነስ መቻሉን ተናግረዋል፡፡

ፕሮጀክቱ በእቅዱ መሰረት የመከላከልና የጉዳት መቀነስ ስራውን 105 ነጥብ 62 በመቶ ማከናወን መቻሉን ገልጸዋል፡፡

እንደ ኢንጅነር ዘመኑ ገለጻ፣ በተሰራው የቅድመ ጎርፍ መከላከያ ስራ በደቡብ ጎንደር ዞን የደራ፣ የፎገራና የሊቦከምከም ወረዳዎች አዋሳኝ በሆነው የታችኛው ርብና ጉማራ ወንዞች ተፋሰሶች ዙሪያ ልማት ላይ ከፌዴራል እስከ ክልል ድረስ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ተረባርበዋል፡፡

ባለድርሻ አካላቱ ባደረጉት የተቀናጀ የግብዓቶች ማሟላት ስራም ይደርስ የነበረውን የሕብረተሰብ መፈናቀልን የመከላከል ስራ ምቹ ሁኔታን ተፈጥሯል ብለዋል፡፡

በቅንጅታዊ አሰራሩ በተፈጠረው ምቹ ሁኔታም በርብና ጉማራ ተፋሰሶች መሙላት ሳቢያ በክረምቱ ሊከሰቱ የሚችሉ የጎርፍ ችግሮችን ከሕብረተሰቡ ጋር ተናቦ በመፍታት የታቀደውን አፋጣኝ የጎርፍ መከላከያ ስራ በስኬት ተሰርቷል ብለዋል፡፡

በዞኑ የተጀመሩ ቀሪ ስራዎች በማርዝ ፣ በጓንታ፣ በሺኒ፣ በርብና በናቹሪት ወንዞች መኖራቸውን የገለጹት ማናጀሩ፣ የውሃ መውጫ በሮችንና መሸጋገሪያ ድልድዮችን በርብና ጉማራ ወንዞች ላይ ያልተሰራላቸው መኖራቸውንም ጠቁመዋል፡፡

እነዚህ ምንም የአደጋ መከላከል ስራ ያልተሰራላቸው ወንዞች በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቷቸው መሰራት ያለባቸው እንደሆኑ ተናግረዋል፡፡

በርብ ላይ በተሟላ አቅም በመደበኛ የግንባታ ወቅት ያልተሰሩ ስራዎች መኖራቸውን ያመላከቱት ማናጀሩ፣ የመልሶ ስራ ማጠናከርና ማስተካከል ያስፈልጋቸዋልም ብለዋል፡፡ በተያዘው የነሃሴና የመስከረም ወራትም ስራው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቁመዋል፡፡



# ከሀገራት ጋር ቀጣይነት ያለውን የገበያ ትስስር ለማጠናከር እንደሚሠራ ሚኒስቴሩ ገለጸ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ከነባርና አዳዲስ የኢትዮጵያን ምርት ገዢ ሀገራት ጋር ቀጣይነት ያለው የገበያ ትስስርን ለማጠናከር እንደሚሠራ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ገለጸ።

በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የውጭ ንግድ መሪ ዋና ሥራ አሥፈፃሚ አቶ ገመቺስ መላኩ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ሀገራት በሚያዘጋጇቸው ኤክስፖዎች በመገኘት ምርቶቿን ለአዳዲስ የገበያ መዳረሻዎች ስታስተዋውቅ ቆይታለች። ከአዳዲስ ሀገራት ጋርም የገበያ ትስስሮችን ፈጥራለች። ከነባርና አዳዲስ የኢትዮጵያን ምርት ገዢ ሀገራት ጋር የገበያ ትስስርን ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማጠናከር በትኩረት ይሠራል።

እንደ አቶ ገመቺስ ገለፃ፤ ኤክስፖዎችን መሳተፍ የገበያ ዕድል ይዞ ይመጣል። ስለዚህም በሚዘጋጁ ዓለም አቀፍ የምግብ የንግድ ትርዒቶች ላይ ላኪዎች በማስተባበር ከነባር ገዢዎቻቸው ጋር ቀጣይነት ያለው የገበያ ትስስርን እንዲያጠናክሩ ተደርጓል። ከአዳዲስ ገዢዎች ጋር እንዲገናኙ እንዲሁም ምርቶቻችን በተሻለ ዋጋ እንዲሸጡ በተደረገው የመሪነት ሚና በየዘርፉ የገበያ ትስስር እየተፈጠረ ይገኛል።

ኢትዮጵያ በበርካታ ሀገራት በተደረጉ ኤክስፖዎች ላይ በመገኘት ምርቶቿን ማስተዋወቅ እንደቻለች አቶ ገመቺስ ተናግረዋል። በ2014 በጀት ዓመት በዱባይ ገልፍ ፉድ፣ በዱባይ ኤክስፖ 2020፣ በናይጄሪያ፣ በቻይና ሻንጋይ፣ በቻይና ቻንግሻ እንዲሁም በኦንላይን ሰሊጥና ቡና የማስተዋወቅ ሥራ ተሠርቷል።

ከተጠቀሱት ሀገራትና ከኤክስፖው ተሳታፊዎች ጋር በርካታ የገበያ ዕድሎች ተፈጥረዋል ያሉት ስራ አስፈጻሚው፤ ለአብነትም በተደረገው የገበያ ትስስር በዱባይ ገልፍ ፉድ ብቻ 46 ነጥብ 26 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ሊያወጣ የሚችል የሽያጭ ኮንትራት ውል መገባቱን አብራርተዋል። ከተደረጉ የገበያ ስምምነቶች በተጨማሪም የሀገር ገጽታን የሚያገነቡ ተግባራት ተከናውነዋል ብለዋል።

የገበያ ትስስርን በዘላቂነት ከማጠናከርና የኢትዮጵያን ምርቶች ከማስተዋወቅ ጎን ለጎን በወጪ ንግድ የታዩ ማነቆዎችን ተከታትሎ መፍታት መቻሉ ለኤክስፖርት ዘርፉ ውጤታማነት አስተዋፅኦ ማድረጉንም አቶ ገመቺስ ጠቁመዋል።

በበጀት ዓመቱ በርካታ የወጪ ንግድ ማነቆዎች ተለይተው የመፍትሄ አቅጣጫዎች መቀመጣቸውና መተግበራቸውን አቶ ገመቺስ ገልፀዋል። የወጪ ንግድ ማነቆዎች በሀገራት መካከል የሚከሰቱ በመሆናቸው በኢትዮጵያ ላኪዎችና በተቀባይ ሀገራት መካከል የተከሰቱ አለመግባባቶችን በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ከኤምባሲዎች ጋር በመነጋገር በስምምነት ሊፈቱ መቻላቸውን አሳውቀዋል።

በወጪ ንግድ ረገድ ከአንዳንድ ሀገራት እና ድርጅቶች ጋር ተፈጥረው የነበሩ አለመግባባቶችም በመነጋገር መፈታታቸውን ጠቁመዋል።

በአጠቃላይም ወጪ ንግድ ላይ በገዢ ሀገራት የሚነሱ ቅሬታዎችን በመፍታት፤ ለዘላቂ የገበያ ትስስር እንደሚሠራ የተናገሩት አቶ ገመቺስ በ2015 በጀት ዓመት አዳዲስና ነባር የምርት ገዢ ሀገራትን የገበያ ትስስር ለማጠናከር በትኩረት እንደሚሠራ ጠቁመዋል።

# በተለያዩ አውዶች ላይ የዲያስፖራውን አቅም አሟጦ መጠቀም እንደሚገባ ተጠቆመ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት የዲያስራውን የገንዘብ፣ የዕውቀትና የክህሎት አቅም እንዲሁም የተለየ ልምምድ ለሀገር ፋይዳ በሚሰጥ መንገድ አሟጦ መጠቀም እንደሚገባው በድር ኢትዮጵያ ገለጸ፡፡

የብድር ኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት አቶ አሕመድ ወርቁ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ዲያስፖራው ማኅበረሰብ የገንዘብ እና የዕውቀት እምቅ አቅም አለው፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ ክህሎቶች እና እንደሚኖርበት ሀገር የሚወሰን የችግር አፈታት ልምምድ ይኖራል፡፡ መንግሥት እዚህን የመሳሰሉ አቅሞች ለሀገር ፋይዳ በሚያመጡበት መንገድ አሟጦ መጠቀም ይገባዋል፡፡

ከዲያስፖራው በኩልም እነዚህ አቅሞች የህዳሴው ግድብ ላይ በገንዘብ በመርዳት እና በዲፕሎማሲ ዕውነቱን በማሳወቅ እየተሠሩ መሆኑንና ቀጣይነት እንዲኖራቸው ተደርጎ እንደሚከናወኑ አቶ አህመድ ገልጸዋል፡፡ ከዚህ አንፃርም በድር ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የሙስሊሞች ተቋም ለግድቡ በዲፕሎማሲና ዕውነቱን በማሳወቅ እንዲሁም በገንዘብ በሚደረግ ድጋፍ በቁርጠኝነት ሲሠራ እንደቆየ ገልጸዋል፡፡

ዲያስፖራው ማሕበረሰብ በሀገሩ ጉዳይ ላይ የሚጨነቅ የማሕበረሰቡ አካል ነው ያሉት አቶ አሕመድ፤ በሀገሩ ጉዳይ ላይም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ብዙ ተሳትፎዎች እንደሚያደርግ ገልጸው፤ በሀገራዊ ምክክሩ ላይ ተመሳይ ተሳትፎዎችን እንደሚያደርግ ይጠበቃል ሲሉ አብራርተዋል፡፡



አቶ አሕመድ ወርቁ

በዋናነት በሀገራችን ከዚህ በፊትም ሆነ አሁን ችግሮች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ዲያስፖራው ያሉ ችግሮችን ለመፍታት ድጋፍ በማድረግ እና የዕውቀት ሽግግር በማድረግ የራሱን አስተዋፅኦ ያደርጋል ሲሉም አክለዋል፡፡

ዲያስፖራው እንደ ሁለተኛ ዜጋ የመታየቱ ሁኔታ ተቀርፏል ያሉት አቶ አሕመድ፤ ዲያስፖራው ማሕበረሰብ በሚያገኘው የሀገርን ገጽታ የሚለውጥ ተግባር ላይ በቀጥታ ተሳታፊ በመሆን ዕድሉን እንዲጠቀም አደራ እላለሁ ብለዋል፡፡

እንደ አቶ አሕመድ ገለፃ፤ ከለውጡ ማግሥት ጀምሮ የተወሰኑ የዴሞክራሲ ጭላንጭሎች በመታየታቸው ዲያስፖራው ማሕበረሰብ ይህን ዕድል ተጠቅሞ በሀገሩ ጉዳይ ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ ማድረግ ጀምሯል፡፡ በተለይ ደግሞ ሀገራዊ ምክክሩ ላይ ዲያስፖራው ወደ ሀገር ውስጥ በመጋበዝ እንዲወያይ መደረጉ የሚያበረታታ ነው፡፡

ሀገራዊ ምክክር ወሳኝ ነው የሚሉት አቶ አሕመድ፤ አሁን የተጀመረው የሀገራዊ ምክክር ሂደት ተስፋ ሰጪ ነው ብለው እንደሚያምኑ ገልጸው፤ ሃሳቦችን ማንሸራሸር ከተቻለ እና ግለሰቦችም ይሁኑ ተቋሞች በጋራ ጉዳያቸው ላይ መወያየት ከቻሉ ሀገር ወደ ፊት መራመድ ትችላለች ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ካልሆነ ግን አሁን እየታዩ ያሉ ምልክቶች በሰውም በሀገርም ላይ ጥፋት እያጠፉ የሚቀጥሉ ስለሚሆን ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ነፃ ሆኖ እና ሁሉንም የሚያካትት መልኩ ሥራዎችን ሊሠራ እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

ዲያስፖራው በሀገራዊ ምክክር ላይ ካለው ተሳትፎ በተጨማሪ በጦርነትና በተለያዩ ምክንያቶች የተጎዱና የተፈናቀሉ ዜጎችን ወደ ቀድሞው ሁኔታቸው ለመመለስ ከመንግሥት ጋር እንዲሠራም አሳስበዋል፡፡

መንግሥት ዲያስፖራው ላይ በሁሉም ዘርፍ በጣም ትልቅ አቅም እንዳለ ሊገነዘብ እንደሚገባ የገለጹት ፕሬዚዳንቱ፤ በሁሉም ዘርፍ ዲያስፖራው ተሳታፊ እንዲሆን ቢደረግ እንዲሁም ታላላቅ ጥሪዎች በተደጋጋሚ ቢደረጉ ብዙ ችግሮችን በቀላሉ መፍታት ይቻላል፡፡

# ኢትዮጵያ በ2014 በጀት ዓመት ከስጋና የስጋ ተረፈ ምርት 119 ሚሊዮን ዶላር ማግኘቷ ተገለጸ

**ዳንኤል ዘነበ**

አዳማ፡- ኢትዮጵያ በ2014 በጀት ዓመት ለውጭ ገበያ ከቀረበው 22 ነጥብ 699 ሺህ ቶን ስጋና የስጋ ተረፈ ምርት 119 ሚሊዮን ዶላር ገቢ መገኘቱን የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አምባሳደር ድሪባ ኩማ ገለጹ።

ዋና ዳይሬክተር አምባሳደር ድሪባ ኩማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ፤ ኢትዮጵያ በ2014 በጀት ዓመት ለውጭ ገበያ ከቀረበው 22 ነጥብ 699 ሺህ ቶን ስጋና የስጋ ተረፈ ምርት 119 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ተገኝቷል። በበጀት ዓመቱ ከስጋና የስጋ ተረፈ ምርት የተገኘው የውጭ ምንዛሬ ገቢ ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር 40 በመቶ ከፍተኛ ብልጫ ያለው መሆኑን ገልጸው ፤ በ2013 ዓ.ም ወደ ውጭ ገበያ የተላከው ስጋና የስጋ ተረፈ ምርት በአጠቃላይ 15 ሺህ 800 ቶን ተልኮ 79 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ተገኝቷል ። ስለዚህ በዘንድሮው በጀት ዓመት የተገኘው የውጭ ምንዛሪ በጣም ከፍተኛ ነው ብለዋል።

በበጀት ዓመቱ የተመዘገበው ውጤት ከፍተኛ ቢሆንም፤ ሀገሪቱ ካላት አቅም በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ገልጸዋል። ለዚህ ደግሞ ዋነኛው ምክንያት ቄራዎች ካላቸው የማምረት አቅም የሚጠቀሙት ከ30 በመቶ በታች መሆኑንም ተናግረዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ማብራሪያ ፤ የእንስሳት ግብይት ሥርዓቱ ፤ የእንስሳት ሀብት ልማቱ ፤ የእንስሳት በኮንትሮባንድ ወደ ውጭ ሀገር ስለሚወጣ ባለሀብቱ በበቂ ሁኔታ የእንስሳት ሀብትን አላገኙም። በዚህ የተነሳ ያለውን ሀብት የሚመጥን ውጤት አልተገኘም ። በሌላ በኩል የበሽታ ቁጥጥር ኳራንቲን፣ የምርት ጥራት ቁጥጥር አለመኖሩ በዘርፉ ላይ እንቅፋት ፈጥሯል ።

ጠንካራ ተቋም ገና አሁን ነው የተመሰረተው የሚሉት አምባሳደሩ ፤ በአዲሱ ዓመት የነበሩትን ጠንካራ ጎኖች በማጠንከር የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት እንደሚሰራም አስገንዝበዋል ።

በባለሥልጣኑ የኤክስፖርት ቄራዎች ኢንስፔክሽን እና ሰርተፊኬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ዶክተር አያሌው ሹመት በበኩላቸው ፤ በሀገራችን በሥጋው ኢንዱስትሪ እየተፈጠረ ያለው አቅም ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ተስፋ ሰጪ ነው ። በስጋው ኢንዱስትሪ የተፈጠረው የማምረት አቅም ከዛሬ 10 ዓመት በፊት ከነበረው ዓመታዊ የማምረት አቅም በከፍተኛ ሁኔታ ማደጉን አመልክተዋል ።



አምባሳደር ድሪባ ኩማ

በ2014 ዓ.ም በጀት ዓመት በሀገራችን ኤክስፖርት ቄራ ከተጀመረ ጀምሮ በታሪክ ተመዝግቦ የማያውቅ ውጤት ለመመዝገቡ መሠረቱ ለጥራትና ደህንነት የተለየ ትኩረት በመስጠቱ ነው ። ከጥራትና ደህንነት ጋር ተያይዞ የነበሩ ችግሮችን ለመፈታት የሀገራችን ምርት በውጭ ሀገራት ዘንድ ተፈላጊነቱ በከፍተኛ ደረጃ እንዲጨምር አድርጓል ። ይሁንና ሀገሪቱ ያላት አቅም ከመጠቀም አኳያ እጅግ በጣም ብዙ የሚቀሩ ሥራዎች አሉ ብለዋል።

በዋነኝነትም ገበያ መር የእንስሳት እርባታ ማካሄድ ፣ ድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታ ቁጥጥር ስራ ማጠናከር፣ የእንስሳት ልየታ ምዝገባ ሥርዓት መዘርጋት ፣ ጠንካራ የእንስሳት ደህንነት ፣ጥበቃ ፣አያያዝና ሥርዓት መፍጠር፣ የመደራደር አቅም ማጎልበት ፣ አማራጭ በረራዎችን ማስፋት ማለትም ከክሎች ቀጥታ ወደ መዳረሻ ሀገራት ስጋ መላክ እንዲሁም የዘርፍ ማህበራት አቅም በማጎልበት ሕጋዊ መሠረት ያለው አቅም መፍጠር እንደሚያስፈልግ ዶክተር አያሌው አስታውቀዋል።

ሀገራችን 42.9 ሚሊዮን በግ 52.5 ሚሊዮን ፍየል፤ 70.2 ሚሊዮን የቀንድ ከብት እና ስምንት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ግመል (CSA,2020/21) በመያዝ በዓለም አቀፍ ደረጃ በቀንድ ከብት ብዛት አምስተኛ እንዲሁም ፤ ከአፍሪካ አንደኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች። በተጨማሪም በበግና በፍየል ብዛት ደግሞ ዘጠነኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች። ኢትዮጵያ ከፍተኛ የእንስሳት ቁጥር ቢኖራትም ተጠቃሚነቷ ካላት ሀብት አኳያ እዚህ ግባ የሚባል እንዳልሆነ ይታወቃል።

# በዞኑ ከ104 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የተገነቡ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ተመረቁ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- በደቡብ ክልል ጋሞ ዞን በተለያዩ ወረዳዎች ከ104 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የተገነቡ የመስኖና የንጹህ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ተመረቁ።

የክልሉ ውሃ መስኖና ማዕድን ልማት ቢሮ ኃላፊ ኢንጂነር አክሊሉ አዳኝ እንደገለጹት፤ በክልሉ በዚህ ዓመት 18 የመስኖ ተቋማት ግንባታ በማጠናቀቅ አንድ ሺህ 800 ሄክታር መሬት ለማልማት እየተሰራ ነው።

የሕብረተሰቡን የንጹህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚነት ለማሳደግ በተደረገ ጥረት 305 ፕሮጀክቶችን በማጠናቀቅ ለምረቃ ማብቃት መቻሉንም ኢንጂነር አክሊሉ ተናግዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ በጋሞ ዞን በተለያዩ ወረዳዎች ከ104 ሚሊዮን ብር በላይ 10 የመስኖና የንጹህ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ግንባታቸው ተጠናቆ ለአገልግሎት ማብቃት ተችሏል፡፡ አርሶ አደሩ ከዚህ ቀደም እያካሔደ ያለውን የመስኖ ተጠቃሚነት ውጤታማ ለማድረግ ዘመናዊ የመስኖ ተቋማትን ለማስፋፋት እንደሚሰራም ጠቁመዋል።

የደቡብ ክልል የመስኖ ተቋማት ልማት እና አስተዳደር ኤጀንሲ ምክትል ስራ አስኪያጅ አቶ ካሳሁን ወልደ ጊዮርጊስ፤ በክልሉ በ2014 በጀት ዓመት ከአንድ ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ 46 የልማት ፕሮጀክቶች ግንባታ ሲካሄድ መቆየቱን አብራርተዋል።

ከነዚህ ውስጥ 18 ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ እንደተቻለ መናገራቸውን ከክልሉ መንግሥት ኮሙኒኬሽን የተገኘው መረጃ ያመላክታል፡፡

## “አልሸባብ ላይ የተወሰደው...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በሶማሌ ክልል ጥሶ ሊገባ ያሰበው አልሸባብ ከዚህ በኋላ ዳግም ቢመጣ እንኳን የበለጠ ቅጣት እንደሚደርስበት ያስተማረ እርምጃ መወሰዱ ተገቢ ነው ያሉት ዶክተር በሽር፤ እርምጃው ለሌሎችም አካላት ተገቢውን ትምህርት የሰጠና አገራዊ የሽብርተኝነትን መከላከል አቅማችንን በአግባቡ ያሳየ ነው ብለዋል።

እንደ ዶክተር በሽር ገለጻ፤ ባለፉት ሶስት ሳምንታት በሶማሌ ክልል የታየው ሕዝብን ያስተባበረ ሽብርተኝነትን የመከላከል ተግባር እንደአገር ያለውን የደህንነትና ጸጥታ ሥራ ያሳደገና ችግሮችን በጋራ የመከላከል ልምዳችንን ያጎለበተ ነው።

ሕብረተሰቡ ደም ከመለገስ አንስቶ፣ መረጃ እስከማቀበልና ሽብርተኞችን እስከማጋለጥ የደረሰ ትብብር ማድረጉን ያወደሱት ፕሬዚዳንቱ፤ ዩኒቨርሲቲውም ምሁራንን በማስተባበር የተለያዩ የወንጀል መከላከል ተግባራትና ሕዝብ የማስተባበር ሥራዎችን እየደገፈ መሆኑን ጠቁመዋል።

ዳር ድንበር ላይ የሚገኘው ሕዝብ በአንድነት ስሜት አገሩን ከጥቃት ለመከላከል ያሳየው ትብብር እንደ ሀገር ውጤታማ አድርጎናል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ የሶማሌ ክልል ፕሬዚዳንት ሙስጠፌ መሐመድ ግንባር ድረስ በመሄድ ያሳዩት ቁርጠኝነት ለክልሉና ለፌዴራል መንግሥት ጸጥታ ኃይሎች ትልቅ የሞራል ስንቅ ሆኗል ሲሉ አስረድተዋል።

በሽብር ቡድኑ ላይ የደረሰው ኪሳራ በሕዝቡና በመንግሥት ዘንድ ያለውን ጥምረትና በጋራ የመሥራት ልምድ ከፍ ወዳለ ደረጃ ያሳደገ መሆኑን የጠቆሙት ዶክተር በሽር፤ ይህንን የተናበበ የጸጥታና ደህንነት ሥራ በተለያዩ አካባቢዎች ላይ በዘላቂነት ማስቀጠል እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

ሽብርተኛው አልሸባብ ለ30 ዓመታት ሶማሊያ ውስጥ ያደረሰው ጥፋት ኢትዮጵያ ውስጥ አንድም ጊዜ ሊያደርገው እንደማይችል ያመላከተ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ተገቢው የጸጥታ እርምጃ መወሰዱ እንደአገር ያለንን የትብብር አቅም ያሳየም ነው ብለዋል።

ዶክተር በሽር እንዳስታወቁት፤ በአሁኑ ወቅት በሶማሌ ክልል እየተከናወኑ ያሉ ሽብርተኞችን የማጥራት ተግባራት የሕብረተሰቡን የደህንነት ስጋት በማስወገድ ረገድ ጠቀሜታው የጎላ ነው። እያንዳንዱ ወደክልሉ የሚገባና የሚወጣ ሰው አስፈላጊው ፍተሻ ተደርጎለት ያልፋል።

በተለያዩ ጊዜያትም በህብረተሰብና በጸጥታ ኃይሎች ቁጥጥር ከፍተኛ አውዳሚ መሳሪያዎች ጭምር መያዛቸው የአገራችንን የደህንነትና የጸጥታ ቁጥጥር ሥራ ውጤት ማምጣቱን ያሳያል ሲሉ ተናግረዋል።

በአገራችን ላይ የሚቃጡ ጥቃቶችን በአግባቡ በመከትን ቁጥር የአንድነት ስሜታችን እየተጠናከረ ይመጣል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በየጊዜው የሚያጋጥሙ የደህንነትና የጸጥታ ችግሮችን ከመከላከል እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ ከመንግሥትና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተባብሮ የመስራቱ ልምድ ሊቀጥል ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ዶክተር በሽር እንዳስታወቁት፤ በሶማሌ ክልል ሽብርተኞችን በመከላከል ረገድ የተወሰደው እርምጃ እንደዜጋ እያንዳንዱ ሰው ኃላፊነቱን መወጣት ከቻለ ማንኛውም ጥቃት ቢሰነዘር በአጭር ጊዜ አስተማሪ የሆነ መልስ መስጠት እንደሚቻል በተግባር ያሳየ ነው።

## እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ንግድን ለማቀላጠፍ እንደሚያግዝ ጠቅሰው፤ ኢትዮጵውያን በጋራ እናሳድጋታለን ሲሉም ተናግረዋል፡፡

ሁሉም ኢትዮጵያውያን ለሟርተኞችን አፍራሽ ሃሳብ ቁብ ሳይሰጥ አገርን በሚያበለጽጉና ወገንን በሚጠቅሙ ስራዎች በንቃት መሳተፋ እንደሚኖርበትም አሳስበዋል፡፡

የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አቶ ከድር ጁሃር በበኩላቸው አገራዊ ለውጡን ተከትሎ ድሬዳዋና አካባቢውን የኢኮኖሚ ኮሪደር ለማድረግ የተለያዩ ስራዎች መከናወናቸውን ገልጸዋል።

ከተከናወኑ ተግባራት መካከልም የተመረቀውን ነጻ የንግድ ቀጣና እንዲሁም የድሬዳዋ ደረቅ ወደብና ሌሎች መሰረተ ልማቶችን በአብነት አንስተዋል። የከተማ አስተዳደሩ የነጻ ንግድ ቀጠናው የታለመለትን ዓላማ እንዲያሳካ የሚጠበቅነትን ድጋፍ ያደርጋል ብለዋል።

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስትሯ ወይዘሮ ዳግማዊት ሞገስ በበኩላቸው የገቢና ወጪ ንግድን ለማሳለጥ የተለያዩ ስትራቴጂዎች ተቀርጸው እየተተገበሩ መሆኑን ገልጸዋል። የነጻ ንግድ ቀጣናው ለስራ ዕድል ፈጠራም ከፍተኛ ሚና እንዳለው ተናግረዋል።

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ስራ አስፈጻሚ ሳንዶካን ደበበም ለነጻ የንግድ ቀጣናው የሚሆኑ መሰረተ ልማቶችን የማሟላቱ ስራ ተጠናክሮ መቀጠሉን ገልጸዋል። የሕግ እና የአሰራር ዝግጅት ስራዎች በመጠናቀቅ ላይ መሆናቸውንም ጠቁመዋል።

## በአራት ዓመታት 25...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ሳይሆን ወይንና ሻይ ቅጠል የመሳሰሉ ምርቶችን በማምረት በስፋት ለውጭ ገበያ ማቅረብ እንችላለን ሲሉም ገልጸዋል

በጥቂት ሚሊዮኖች ችግኝ መትከል እንደ ድል በምትቆጥር ዓለም ላይ በአራት ክረምት 25 ቢሊዮን ችግኞችን በመትከል ማሳካት እንደሚቻል አሳይተንበታል ብለዋል።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ገለፃ፤ አረንጓዴ አሻራ መጀመሩ ለኢትዮጵያ ሁለት ወሳኝ እድሎችን ፈጥሯል። አንደኛ በትልቁ አስበን ከተባበርን በትልቁ ማሳካት እንደምንችል ምስክር ሆኖናል፤ ሁለተኛ ለብልጽግና መሠረት የሚሆን ባህል ፈጥረናል::

ችግኝ የመትከል ባህል ሲውል ሲያድር በምግብ ራሳችንን እንድንችል፣ ግድቦቻችን ዘላቂ ዝናብ እንዲያገኙ፣ ለም አፈራችን እንዳይሸረሸር እንደሚያደርግም ገልጸዋል::

የግብርና ሚኒስትሩ አቶ ዑመር ሁሴን በበኩላቸው እንደገለጹት፤ በአራት ዓመታት በአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር 20 ቢሊዮን ችግኞች ለመትከል ታቅዶ ከ25 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን መትከል ተችሏል::

በአራተኛው አረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብርም እስካሁን ሰባት ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ችግኞች ተተክለዋል:: ይህም የሕዝብ ተሳትፎ ያስገኘው ትልቅ ስኬት ነው ብለዋል::

በአሁኑ ጊዜ ያልተተከሉ አምስት መቶ ሚሊዮን ችግኞች መኖራቸውን ጠቅሰው፤ ዝናብ በሚጀምርባቸው አካባቢዎች የአገሪቱ ክፍሎች እንደሚተከሉም ጠቁመዋል :: በቀጣይም ችግኝ የመትከሉ ባህል ሰርፆ የዘወትር ተግባር እንዲሆን ይሰራል ብለዋል::

# ርዕሰ አንቀፅ

## የድል ዘመን ለኢትዮጵያ!

"በታሪክ ውስጥ ማለፍ እና ታሪክ መስራት ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። በታሪክ ውስጥ ማለፍ እድል ነው። በታሪክ ውስጥ ማለፍ አንድ ሁነት ሲከወን ነበርኩ፤ አይቻለሁ፤ ሰምቻለሁ፤ ብሎ መመስከር መቻል ነው። በዚህ ታሪክ ውስጥ ማለፍ ብቻ ሳይሆን ታሪክ መስራት ግን እድል ብቻ ሳይሆን ድልም ነው። በመገኘት እውቀትን ፣ ገንዘብን ፣ ሃሳብን ጉልበትን በመስጠት አንድ ሁነት እንዲከወን ማድረግ ከእድል ያለፈ ድል ነው፤" የሚለው የጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ንግግር፤ የኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን አሁናዊ የድል መንገድና ጉዞ በእጅጉ ቁልጭ አድርጎ የገለጸ ነበር:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ሁለተኛው ተርባይን ኃይል የማመንጨት ብስራትን ባሰሙበትና የእንኳን ደስ ያለን መልዕክት ባስተላለፉበት ወቅት ነበር ዛሬ ላይ ያሉ ኢትዮጵያውያን ባለ እድልም፣ ባለ ድልም መሆናቸውን፤ ኢትዮጵያንም የድል ባለቤት ማድረጋቸውን የገለጹት::

ይህ ያለምክንያት የተሰነዘረ ሃሳብ አይደለም:: ይልቁንም ታሪክ መስራት እና የባለታሪኮች ታሪክ ውስጥ መኖር ለየቅል መሆናቸውን በእጅጉ የሚያስረዳ እንጂ:: ምክንያቱም ዛሬን ያሉ ኢትዮጵያውያን በቀደምቶቻቸው የታሪክን የተግባር ፍሬ ውስጥ የመኖር እድልን አግኝተዋል፤ ይህ በታሪክ ውስጥ የመኖር እድለኝነት ግን ባለ ድል አያደርግም:: እናም የድል ባለቤት የሚያደርጋቸውን ገድል ፈጸሙ:: በዚህም አገራቸውን ከህልውና ስጋት ነጻ ማድረግ ቻሉ፤ የዲፕሎማሲውን የተዛነፈ ቅርጽ መቀየር ቻሉ፤ በዓለም አደባባይ ኢትዮጵያን አሸናፊ አድርገው ብሔራዊ መዝሙሯ ደመቅ ብሎ እንዲዘመር አደረጉ፤ የዘመናት ሕልሟን በዓባይ ላይ መስርተው በጉባ በረሃ ብርሃንን አሳዩ:: እናም ዕድለኝነትም፣ የድል ባለቤትነትም ለዚህ ትውልድ መሰጠቱ፤ የኢትዮጵያንም የድል ከፍታ መመስከሩ ተገቢነት ያለው ነው::

በተለይ ይህ ዘመን፣ ይህ ዓመት የኢትዮጵያ ግን ከፈተናዎቿ በላይ ገዝፎ መታየት ያስቻሉ የድል ብስራቶች የበዙበት ሆኗል:: ኢትዮጵያ በዓመቱ መጀመሪያ ላይ በሕልውናዋ ላይ የተደቀነውን አደጋ በልጆቿ ብርቱ ክንድ መቀልበስ ቻለች:: በኋላም በጉባ በረሃ ላይ ያኖረችውን የዘመናት ህልሟን አንድ ብላ በብርሃን መግለጥ ጀመረች:: እነዚህን ሁለት ሁነቶች ተከትሎ ዓለማቀፍ ጫናው፤ ዲፕሎማሲያዊ ፍትጊያው አየለ:: ይሁን እንጂ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ወዳጆች ተባብረው በሰሩት ስራ የተዛባውን የዲፕሎማሲ አተያይ ማስተካከልና ዲፕሎማሲያዊ ድል ማስመዝገብ ተቻለ::

በዓመቱ ማገባደጃ ላይ ደግሞ ሌላ የአሸናፊነት ገጽ ተከፈተ፤ ኢትዮጵያ በአትሌቶቿ በዓለም አደባባይ ከፍ ብላ ደምቃ ታየች:: በ18ኛው የኦሪገኑ የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና በዓለም ሁለተኛ ሆና ማጠናቀቋ የኢትዮጵያ የአሸናፊነትና ታላቅነት ማህደር ዳግም እንዲገለጥ ያስገደደ የአትሌቶቻችን ገድል ነበር:: ከዚህ ድል በመከተልም ኮሎምቢያ ካሊ ላይ የተካሄደው ከ20 ዓመት በታች የአትሌቲክስ ሻምፒዮናም ኢትዮጵያ በወርቅ ደምቃ ከፍ ያለችበት፤ ከዓለምም ሦስተኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣ ሃያላኑን ከታች ያስቀመጠችበትን ድል በወጣቶቿ አስመዘገበች:: ይህ የድል አድራጊነት ስሜት ግለቱን ሳይለቅ ሌላ በብርሃን የታጀበ ድል ከወደ ጉባ ተደመጠ፤ ኢትዮጵያ ከዘመናት ህልሟ ማህደር በዓባይ ላይ ሁለተኛውን ተርባይን ኃይል እንዲያመነጭ አድርጋ፤ ሦስተኛውን ዙር ውሃ ሙሊት በስኬት አጠናቅቃ ከፍታዋን አጸናች የሚል::

ይህ የኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያውያን ከፈተናዎች ልቆ በድል ጎዳና መጓዝ ለኢትዮጵያውያን ልዩ ስሜት ነበረው:: የአትሌቶቻችን ድል የፈጠረበት ስሜት ከቃል በላይ መሆኑን ቀድሞ ያስረዳው አትሌት ሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴ፤ የግድቡን በዚህ መልኩ ሃይል ማመንጨትና ውሃ መያዝ ብስራት ሲሰማ "ግብጻውያንና ሱዳናውያን እህት ወንድሞቻችን ኢትዮጵያ እንኳንም የህዳሴ ግድብን ገነባችልን የሚሉበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም" ሲል ነበር የገለጸው:: ይሄም የኢትዮጵያውያንን የእውነትና የድል አድራጊነት መንገድ ወዳጅ ሀገር ቀርቶ የኢትዮጵያን ዕድገትና ከፍታ የማይሹ እንደ ግብጽ ያሉ ሀገራት ጭምር አምነው መቀበላቸው ግድ እንደሚሆን ያስረገጠ ነበር::

በሌላ በኩል፤ በኮሎምቢያ ካሊ በወርቅ ነግሰው አገር ያነገሱ አትሌቶችን የጀግና አቀባበል ለማድረግ በቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ተገኝተው መልዕክት ያስተላለፉት የባህልና ስፖርት ሚኒስትሩ ቀጄላ መርዳሳ፤ "ዛሬ ዝናብ እየዘነበ ነው፤ ዝናቡ ዘንቦ ግድባችንን ሞልቷል፤ መብራቱም በርቷል፤ ዝናብ ብቻም አይደለም፣ ወርቅም፣ ብርም፣ ነሃስም ዘንቧል፤ እናም ዛሬ ድል በድል ሆነናል" ሲሉ ነበር ዘመኑ የኢትዮጵያ የድልና አሸናፊነት መሆኑን የገለጹት!

እርግጥ ነው፤ ዘመኑ የኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያውያን የፈተና ዘመን ብቻ አልነበረም:: ይልቁንም በፈተና ውስጥ ጸንቶ አንድነትን የማስቀጠል፤ ሕልውናን የማስጠበቅ፤ የተዛባ ዲፕሎማሲያው እይታን የማረቅ፤ አገራዊ የልማት ሕልሞችን እውን የማድረግ ትልልቅ ስኬቶችን ማስመዝገብ ተችሏል:: አረንጓዴ አሻራው በማጠቃለያ መርሃ ግብሩ ላይ ከታቀደው በላይ የተሳካበት፤ የግብርናው ዘርፍ በተለይም የስንዴ ልማት ላይ የተሰጠው ትኩረት በራስ አቅም የዳቦ ጥያቄን መመለስ፤ ከዚህ አልፎም ለውጭ ገበያ ማቅረብ የሚያስችል አቅም መኖሩን የታየበት ስኬት የተመዘገበበት ነበር:: ለዚህም ነው ይህ ትውልድ ባለ እድልም፣ ባለ ድልም ሆኖ ኢትዮጵያን ለድል እንድትበቃ አድርጓል መባሉ::

**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

**የባህልና ስፖርት ሚኒስትር አቶ ቀጄላ መርዳሳ ከ20 ዓመት በታች የአትሌቲክስ ሻምፒዮና ልዑካን ቡድን በስካይ ላይት ሆቴል በተካሄደ እውቅና መርሃ ግብር ላይ ያስተላለፉት መልዕክት፤**

# "የዛሬ ድላችሁ የነገ ስንቃችሁ ነውና ጥረታችሁን ቀጥሉ"

\- የባህልና ስፖርት ሚኒስትር አቶ ቀጄላ መርዳሳ

የተከበሩ አቶ አገኘው ተሻገር፣ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ፤

ክቡራን የባህልና ስፖርት ሚኒስትር ዴኤታዎች፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስራ ኃላፊዎች፣ ክቡራን እንግዶች፣ እንኳን ለዚህ ዛሬ እያየን ላለነው ድል አበቃን፤ እንኳን ደስ ያላችሁ፤ እንኳን ደስ ያለን ማለት እፈልጋለሁ፡፡



በያዝነው በ2014 ዓ.ም በለስ ቀንቶናል፤ ታግለን ሰርተን ውጤት አግኝተናል፡፡ በተለይ በስፖርቱ ቀደም ሲል ከነበረ ችግር ወጥቶ፣ በተለይ ከቅርብ ዓመታት ወደዚህ በስፖርቱ አካባቢ የመዳከም ሁኔታዎች ሲታዩ የነበረበትና ህዝቡ ትንሽ ያዘነበት፤ በተለይ በቶኪዮ 2020 ያዘነበትን እናስታውሳለን፡፡ ከዛ አንሰራርቶ ዛሬ አንጸባራቂ የሆኑ ድሎች እየተገኙ እንደሆነ ሁላችንም እየተከታተልን ነው፡፡

በዚህ ዓመት እ.አ.አ ከማርች 18 እስከ 20 በነበረው የሰርቢያ ቤልግሬድ የቤት ውስጥ ውድድር ብዙ ያልተነገረለት፤ ግን ከዓለም አንደኛ የሆንንበት፣ አትሌቶቻችን "ታላቋ" የምትባለውን አሜሪካን አሸንፈው በአንደኝነት የገቡበት ድል ነበር፡፡ በዛ ውድድር ዘጠኝ ሜዳሊያዎች ተገኝተዋል፡፡ በመቀጠል እአአ ከጁላይ 15 እስከ 24 በነበረው በ18ኛው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ውድድር ድል ስንከታተለውና ስናከብረው የከረምነው የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው፡፡ እናም ኢትዮጵያ ገጽታዋ ከፍ ያለበት፤ የኢትዮጵያ ህዝብም የኮራባቸውን ትልቅ ድል አትሌቶቻችን አስገኝተውልናል፡፡

አሁን ደግሞ በመቀጠል በእናንተ በአፍላ ወጣቶች፣ በጥሩ እድሜ ላይ ያሉና ገና ሮጠው ባልጠገቡ አትሌቶቻችን በኮሎምቢያው ከ20 ዓመት በታች የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና 12 ሜዳልያዎችን በማስገኘት ከዓለም ሶስተኛ፣ ከአፍሪካ ደግሞ አንደኛ ሆነው እንደዚህ በድል ሲገቡ ቀደምት አትሌቶች አንጋፋዎቻቸውን ፈለግ ተከትለው ድሉን በማስቀጠላቸው እንኳን ደስ ያለን፤ እንኳን ደስ ያላችሁ፤ እነዚህን ልጆች በደማቅ ጭብጨባ አመስግኑልኝ፡፡

የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ከዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫ መስኮች አንዱ ብቁና ንቁ ዜጋ፣ አሸናፊ ዜጋን ማፍራት ነው፡፡ እናንተም እንኳን አሸነፋችሁ፡፡ ዓላማውም ብቁ እንድትሆኑ፣ ብቁ እንድንሆን ነበርና፤ እንኳን ለዚህ በቃችሁ፤ እንኳን ለዚህ አበቃችሁን፡፡ እንኳንም ለድል በቃን፤ ለማለት እፈልጋለሁ፡፡

**ይሄንን ስፖርት ለመደገፍ፣ ለማጠናከር በገንዘብም፣ በሞራልም በሃሳብም የሚደግፉትን በሙሉ ማመስገን እፈልጋለሁ፡፡ ከሩቅም ከቅርብም ሆነው ደግሞ መረበሽ የሚፈልጉትን ተሰብሰቡ፤ ተቆጠቡ በማለት መልዕክት ማስተላለፍ እፈልጋለሁ**

ሌላው የባህልና ስፖርት ግብ ተተኪ ስፖርተኞችን ማፍራት ነው፡፡ እነዚህ ዛሬ በድል የገቡት ልጆች ተተኪ አትሌቶች ናቸው፡፡ ተተኪ አትሌቶችን መፍጠር ነው ስራችን፤ እናንተም እንኳን ተተኪ ሆናችሁ ተፈጠራችሁ፡፡ ለወደፊቱም በቀጣይ ላሉት አህጉራዊና ዓለማቀፍ ውድድሮች ኢትዮጵያን ወክላችሁ፤ በተለይም ከሁለት ዓመት በኋላ ዛሬ አፍላ ወጣቶች ያልኳቸው ነገ ደግሞ ከሌሎች ወጣቶችም ጋር በእድሜና በደረጃቸው ፈረንሳይ ፓሪስ በሚካሄደው የኦሎምፒክ ውድድር ላይ እንደምትሳተፉ ከወዲሁ እተማመንባችኋለሁ፤ እንተማመንባችኋለንም፡፡ ስለዚህ የዛሬ ድላችሁ የነገ ስንቃችሁ ነውና ጥረታችሁን ቀጥሉ ማለት እፈልጋለሁ፡፡

ለምንድን ነው ይሄንን ሁሉ ድል ማግኘት የቻልነው ብለን ካልን፤ የአመራር፣ የአሰራር፣ በተለይ ደግሞ በስፖርቱ አካባቢ ሰላም ማስፈን በመቻሉ ነው፡፡ ስፖርቱን የሚያውኩ አየሮች አሉ፤ ስፖርቱን የሚረብሹ አካሄዶችን ቀስ ብለን እያስወገድን በመስራታችንና በስፖርቱ ጎራ በተለይ በአትሌቲክሱ ጎራ የተረጋጋ ስራ በመሰራቱ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ ይሄንን ስፖርት ለመደገፍ፣ ለማጠናከር በገንዘብም፣ በሞራልም በሃሳብም የሚደግፉትን በሙሉ ማመስገን እፈልጋለሁ፡፡ ከሩቅም ከቅርብም ሆነው ደግሞ መረበሽ የሚፈልጉትን ተሰብሰቡ፤ ተቆጠቡ በማለት መልዕክት ማስተላለፍ እፈልጋለሁ፡፡

በመጨረሻም፣ እንኳን ደስ ያለን፤ እንኳን ደስ ያላችሁ በማለት፤ በዚህ አጋጣሚ ደግሞ ልክ እንደነዚህ ወጣቶች በየጦር ግንባር በተለይም ደግሞ በጉባ በረሃ ላይ የህዳሴን ግድብ በመገንባት የሁለተኛው ተርባይን ኃይል እንዲያመነጭ እና የሶስተኛ ዙር የውሃ ሙሌት እንዲከናወን ላበረከቱ ወጣቶች፤ እንዲሁም ለሌሎች መሐንዲሶቻችን፣ ሰራተኞቻችን ምስጋና ይገባችኋል ማለት እፈልጋለሁ፡፡ እንኳን ደስ አለን፤ አመሰግናለሁ!

# ፋሽን

## ውስጥን የሚያሳይ ፈጠራ

**ዋስልኝ አየለ**

መገናኛ 24 ተብሎ የሚጠራው አካባቢ ያለው ኮከብ ሕንጻ ነበር ጉዳዬ:: አካባቢውን እንጂ ሕንጻውን አላውቀውም ነበር:: ዳሩ ግን ማንንም መጠየቅ ሳያስፈልገኝ የሄድኩበትን ጉዳይ የሚያመለክት ምልክት ማየት የጀመርኩት ከሕንጻው ከብዙ ርቀት ነው::

የሄድኩበት ጉዳይ ሔዋን የፋሽን ዲዛይን፣ የፀጉር፣ የሜካፕ እና ዲኮር ማሰልጠኛ ተማሪዎችን ስለሚያስመርቅ ለመታደም ነበር:: ገና ከርቀት ጋወን የለበሱ ተማሪዎችን አየሁ:: ሌላ የሚያስመርቅ ዩኒቨርሲቲ ወይም ኮሌጅ አለ ይሆን ተጠራጠርኩ:: ዳሩ ግን የአንዳንዶች አለባበስ እንዳልጠራጠር አደረገኝ:: ፋሽን ተኮር ነው:: ጋዎን የለበሱትን የደረታቸውን ማዕረግ ጠጋ ብየ ሳይ ‹‹የፋሽን ዲዛይን....›› ሙሉውን ለማየት ያልቋጨሁት ጽሑፍ አየሁ::

ቀጥታ ወደ አዳራሹ ገባሁ:: የተለያየ አይነት ዲዛይን የለበሱ ቆነጃጂት ይታያሉ:: አብዛኞቹ ግን የለበሱት የተማሪዎቹን የምርቃት ጋዎን ነው::

ወዲያውኑ የፋሽን ሾው ተጀመረ:: የተለያየ አይነት ዲዛይንና ፈጠራ ይታያል:: በነገራችን ላይ እነዚህ ፈጠራዎች የውስጥን ምንነት የሚያሳዩ ናቸው:: ምክንያቱም ፋሽን የውስጥ ስሜት ነው:: ፋሽን ፍልስፍናም ነው:: ፋሽን ፈጠራ ነው::

በመድረኩ ላይ በነበረው ትዕይንት የተለያዩ ፈጠራዎች ታይተዋል:: ከላባ የተሰሩ የዲዛይን አይነቶች፣ ከቃጫ የተሰሩ የዲዛይን አይነቶች አሉ:: ከተለያዩ ልብ ከማንላቸውና ትኩረት ከማንሰጣቸው ነገሮች የተሰሩ ብዙ አይነት ዲዛይኖች አሉ::

እነዚህን በአካባቢያችን ያሉ እና ልብ ያላልናቸውን ነገሮች ትኩረት ሰጥቶ እንደዚያ አይነት ማራኪ ዲዛይን መሥራት ጥበብ ይጠይቃል::

የፋሽን ፍልስፍና የውስጥን እውነታ ለውጭ ማሳየት ነው:: የውስጥ እውነታ ማለት በዲዛይነሯ ውስጥ የተፈጠረው ስሜት ወይም ዕይታ ማለት ነው:: ያንን የውስጥ ዕይታ አውጥታ በልብስ መልክ ለውጭው ታሳያለች:: ይህ ነው የፋሽን ፍልስፍና የሚባለው::

እንዲህ አይነት የፈጠራ ባለቤት የሆኑ ባለሙያዎችን ነው ሔዋን የፋሽን ዲዛይን፣ የፀጉር፣ የሜካፕ እና ዲኮር ማሰልጠኛ ባለፈው እሁድ ያስመረቀው::



የማሰልጠኛው መሥራችና ባለቤት ወይዘሮ ሔዋን ቀለመወርቅ በእለቱ እንደገለጹት፤ በፋሽን፣ በፀጉር፣ በዲኮር፣ በሜክአፕ፣ በጥልፍ እና በሌሎችም ዘርፎች ሲሰለጥኑ የቆዩ ተማሪዎች ስልጠናቸውን በብቃት አጠናቀው ተመርቀዋል:: በዕለቱ ምርቃቱ ላይ ብዙ የፈጠራ ሥራዎች ታይተዋል፤ እነዚያን ሥራዎች የሰሯቸው እዚሁ ማሰልጠኛ ውስጥ ሆነው ነው::

ማሰልጠኛ ተቋሙ እነዚህን ባለሙያዎች ማሰልጠን ከጀመረ ሰባት ዓመታት ሆነውታል:: ሔዋን የፋሽን ዲዛይን፣ የፀጉር፣ የሜካፕ እና ዲኮር ማሰልጠኛ ተቋም ባለፈው ሳምንት እሁድ ያስመረቃቸው ተማሪዎቹ 15ኛ ዙር ሰልጣኞች መሆናቸውን የማሰልጠኛው መሥራችና ባለቤት ገልጸዋል::

በ2007 ዓ.ም ስልጠና መስጠት የጀመረው ማሰልጠኛ ተቋሙ፤ ከአመት አመት የሚቀበላቸው ተማሪዎች ቁጥር እየጨመረ መጥቷል፤ በዚህም ምክንያት ተማሪዎቹን በዓመት ሁለት ጊዜ የሚያስመርቅ መሆኑንም ወይዘሮ ሔዋን ገልጸዋል።

እንደ ወይዘሮ ሔዋን ገለጻ፤ ከማሰልጠኛው ተመርቀው የሚወጡ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የራሳቸውን የሥራ ዕድል ፈጥረው በግል እና በማህበር እየተደራጁ የሚሰሩ መሆን ችለዋል::

ማሰልጠኛው በቀጣይ ሌሎች ተጨማሪ የሙያ ዘርፎችን መጨመር እና ማሳደግ ላይ ይሰራል ያሉት ወይዘሮ ሔዋን፤ በመንግሥት የተያዘውን በክህሎት የዳበረና የሠለጠነ ወጣት በማፍራት ለሥራ እድል ፈጠራ መስፋፋት የበኩሉን ሚና ለማበርከት ጥረት እንደሚያደርግም አስታውቀዋል።

የፋሽን ኢንዱስትሪ በዓለም አቀፍ ደረጃ አንድ የሚመሰገንበት ነገር አለው:: ይሄውም የአየር ብክለትን ማስቀረቱ ነው:: ከወዳደቁ ነገሮች ዲዛይን የሚሰሩ ዲዛይነሮች አሉ:: እነዚህ ዲዛይነሮች ለአየር ብክለት ምክንያት የሚሆኑ ቁሶችን ወደ ጠቃሚ ምርት ይቀይሯቸዋል ማለት ነው::

በፋሽን ኢንዱስትሪው ውስጥ ዘላቂነት ያለው እና ጊዜያዊ የሚባል አለ:: ጊዜያዊ የሚባለው ቶሎ ሊበላሽ ስለሚችል ከጊዜ በኋላ የሚጣል ሊሆን ይችላል:: ዘላቂው ግን በዘላቂነት የአየር ብክለትን ይቀንሳል ማለት ነው::

የዘላቂ ፋሽንን ጽንሰ ሀሳብ የመጣው በሎንዶን ውስጥ የዘላቂነት ዲዛይን እና ፋሽን ፕሮፌሰር ኬት ፍሌቸር በአውሮፓውያኑ 2007 በፈጠረው ፈጠራ ነው :: ይህ ሃሳብ እንደሚለው በሚያመርተው ምርት ውስጥ አካባቢን በሚያከብሩ የማኑፋክቸሪንግ ምርቶች ላይ እንዲሁም አንድ ልብስ ለሸማቾች በማምጣት ላይ ባሉት ሁሉም ሂደቶች ውስጥ ብክለት የሌለበት መሆን እንዳለበት ነው::

ትላልቅ የኢንዱስትሪ የፋሽን ኩባንያዎች ብዙውን ጊዜ የደህንነት መመዘኛዎች ባልተሟሉባቸው ሀገሮች ውስጥ ሁሉ ይሰራሉ:: በእነዚህ ሁኔታዎች ታዲያ ዘላቂ የሆኑ የፋሽን ብራንዶች የሚዘጋጁት በአዘጋጆቹ ጥንቃቄና ጥሬ ዕቃዎችን በኃላፊነትና በአግባቡ በመጠቀም ነው::

ሰናይት ማሪዎ የተባለች ፋሽን ዲዛይነር በአንድ ወቅት ከሪፖርተር ጋዜጣ ጋር ባደረገችው ቆይታ እንደገለጸችው፤ ፋሽን የሚያድገው በግለሰብ ብቻ አይደለም:: ለዚህም እምቅ ችሎታ ያላቸው ወጣት ዲዛይነሮች አሉ:: ለእነርሱ ደግሞ ዕድል መስጠትና መድረክ መፍጠር ኢንዱስትሪውን ከሚያሳድጉት መካከል አንዱና ዋነኛ ነው:: በሌላ በኩል እነዚህ ዲዛይነሮች በየአካባቢው እየዞሩ የአገራቸውን የባህል አልባሳት ምቹ አድርገው ለገበያ በማቅረብና ራሳቸውን ኢንተርናሽናል ዲዛይነር ለማድረግ ነው ጥረት የሚደረገው:: የኢትዮጵያ አልባሳት በአብዛኛው የሚሠሩት በጥጥ በመሆኑ ለበጋም ሆነ ለክረምት ምቹና ጤናማ በመሆኑ ቀልብ የሚስብ ነው:: ለዚህም ነው አብዛኛዎቹ የዓለም አገሮች ዲዛይነሮች ጥሬ ዕቃ ከዚህ ወስደው መልሰው የሚሸጡልን:: ታዲያ እንደዚህ ዓይነት መድረኮችን በመፍጠር ዲዛይነሮችን በማበረታታት ከአገራቸው አልፈው አህጉራቸው፣ ከዚያም ዓለም አቀፍ ብራንድ እንዲኖራቸው ነው የምንሠራው ብላለች::

በተዘዋወረችባቸው የዓለም አገራት እንደታዘበችው የኢትዮጵያ የፋሽን ኢንዱስትሪ አላደገም:: አገራት የየራሳቸውን መገለጫ ሲለብሱ ኢትዮጵያውያን ግን የሌሎችን አገራት ነው የሚለብሱት:: በመሆኑም የኢትዮጵያ የፋሽን ኢንዱስትሪ ማደግ እንዳለበት ታሳስባለች::

የፋሽን ኢንዱስትሪ ጥቅምን ለማወቅ ያደጉ አገሮችን ማየት ብቻ በቂ ነው:: ለምሳሌ ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ምርቶችን በአገር ምርት ቢተካ አንደኛው ጥቅም ነው:: በሌላ በኩል ፋሽን እያደገ ሲመጣ የተለያዩ የዓለም ዲዛይነሮች፣ ሞዴሎች፣ ፋሽን ተከታዮች ወደ ኢትዮጵያ ይዘው የሚመጡት የውጭ ምንዛሪ አለ:: በተጨማሪም በሆቴል ይጠቀማሉ፣ ይዝናናሉ፣ የተለያዩ ዕቃዎችን ይሸምታሉ፣ ከፍ ሲል እዚሁ የመሥራት ፍላጎት ሊኖራቸው ይችላል:: ስለዚህ የፋሽን ኢንዱስትሪ አገሪቷን ሊደግፍና ሊያቀና የሚችል ኢንዱስትሪ ነው::

እነዚህ ነገሮች ይሆኑ ዘንድ ደግሞ የፋሽንና ዲዛይን ማሰልጠኛዎች ሊጠናከሩ ይገባል!

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ስለ ስለሳ አንዳንድ ነገሮች

**አቤል ገ/ኪዳን**

የህዝባችን የፖለቲካ እውቀት ቀን በቀን እያደገ ነው:: ፖለቲካውን የሚተነትነው ሰው ቁጥር ከኑሮ በፈጠነ ሁኔታ ቀን ከቀን እያሻቀበ ነው:: በቅርቡ ሀገራችን በፖለቲካ ተንታኞች በኩል ራሷን እንደምትችልም ምንም ጥርጥር የለውም:: ይሄ ቀላል እመርታ አይደለም:: ፖለቲካና ኮረንቲ በሩቁ ነው በሚባልበት ሀገር እንዲህ ሰዎች ራሳቸውን የፖለቲካ ተንታኝ አድርገው የሚሾሙበት ሁኔታ መፈጠሩ አስገራሚ ነው:: ችግሩ ብዙው ትንታኔ በትንታ የሚገድል መሆኑ ነው:: በህይወታቸው አንድም ነገር አስተዳድረው የማያውቁ ሰዎች ሀገር እንዴት መተዳደር እንዳለባት ያለምንም ችግር ሲተነትኑ መስማት አስገራሚ ነገር አለው:: አንድ መጽሀፍ አንብበው የማያውቁ ሰዎች በማንኛውም ጉዳይ ላይ አስተያየት ሲሰነዝሩ ማየትም አስቂኝ ነው::

የዛሬው ጉዳዬ ግን ፖለቲካ ለምን ተተነተነ አይደለም:: እሱ መብት ነው:: ገባህም አልገባህም ፤ ትክክል ሆንክም አልሆንክም የመናገር ነጻነት ህገ መንግስታዊ መብት እስከሆነ ድረስ የታየን መናገር አይከለከልም:: ችግር የሚሆነው ግን መንግስት በንግግሬ ምክንያት እኔን እየፈለገኝ ነው የሚል እምነት ከተፈጠረ ነው:: ደግሞም ተፈጥሯል:: እርግጥ ይህ እሳቤ ሀሰት ነው ማለት አይቻልም:: በእኛም ሀገር በሌሎችም ሀገራት ያለ ነገር ነው:: የስለላ መዋቅሩ የሀገርን ደህንነት ስጋት ውስጥ የሚከት መረጃ ያሰራጫሉ የሚላቸውን አካላት ይከታተላል ፤ ያስቆማል ፤ በቁጥጥር ስር ያውላል ፤ ይከሳል ፤ ያስፈርዳል:: ይሄ መደበኛ ሂደት ነው::

ነገር ግን በእርግጥ በዚያ ልክ አንገብጋቢ የሆነ እና ሀገርን አደጋ ውስጥ የሚከትት መረጃ ያላቸው እና የሚያሰራጩት እነማን ናቸው ሲባል ብዙውን ጊዜ እነዚያ አካላት በጣም ጥቂት ሆነው ይገኛሉ:: ሌላው ግን በአብዛኛው አእምሮው ውስጥ ያለውን መረጃ የሚተነፍስ እና ያን ያህልም ተጨባጭ መረጃ የሌለው ህዝብ ነው:: ይህን መንግስትም የደህንነት መዋቅሩም ያውቀዋል:: ታዲያ ለምን እነሱን ይከታተላል? አይከታተልም:: ብዙ ሰው ግን እንደዚያ ይመስለዋል:: "ምንድን ነው ስልካችን እየተጠለፈ ነው እንዴ?" ይልሀል በስልክ ስታወራው:: ከመሬት ተነስቶ "ፌስቡኬን ሀክ ሊያደርጉት ነው" ይልሀል:: "መንገድ ላይ ሲከተሉኝ ነበር" ይልሀል::

እንዲህ አይነቱ ቅዠት ከብዙ ነገር ሊመነጭ ይችላል:: አንደኛው ለራስ ከሚሰጥ የተጋነነ ግምት ነው:: አንዳንዱ ሰው በማህበራዊ ሚዲያ ብዙ ተከታይ ሲኖረው በጣም ተጽእኖ ፈጣሪ እንደሆነ እና መንግስትን ሁሉ እስከመቀየር የሚደርስ ጉልበት እንዳለው ይሰማዋል:: እንዲህ አይነት ሰዎች በፊትም አሁንም አሉ:: በአንድ ወቅት አንድ ሰባኪ በጣም ከተማው ላይ ዝነኛ ከመሆኑ የተነሳ እኔና ፓትርያርኩ እኩል ሰው ነው የምናሰልፈው ብሎ ተናግሮ ነበር:: ዛሬ ላይ ያን ያለው ሰው ማንም የማይሰለፍለት መደበኛ ሰው ሆኖ እየኖረ ነው:: በቅርቡም በሀገሪቱ ሁለት መንግስት ነው ያለው የሚል ሰው ነበር:: አንደኛው መንግስት አሁንም አለ:: ሁለተኛው ግን አልተገኘም:: እንዲህ አይነት ለራስ የሚሰጥ የተጋነነ ምልክታ እየተሰለልኩ ነው ፤ እየተከታተሉኝ ነው ምናምን ወደሚል እሳቤ ይመራል::

ሁለተኛው የእንደዚህ አይነት እሳቤ መንስኤ ከአእምሮ ጤና መዛባት የሚመነጭ ነው:: የስነ ልቡና ባለሙያዎች ሺዞፈርኒያ ይሉታል:: እውነታን መረዳት ከሚገባን በተቃራኒው ገልብጦ የመረዳት ችግር ነው:: ይህ ገልብጦ የመረዳት ችግር ቅዠትን እና ብዥታን ይፈጥራል:: የሌለ ነገር እንዲታየን ፤ ስጋት ያልሆነ ነገር ስጋት እንዲሆንብን ፤ ተጠራጣሪነት እንዲወርሰን ወዘተ..በር ይከፍታል:: ከዚያ በኋላ ያልታየ ነገር ሁሉ እየታየን በራሳችን ጥላ የምንደነግጥ እንሆናለን:: ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው በእውነተኛ ታሪክ ላይ ተመስርቶ የተሰራው ኤ ቢውቲፉል ማይንድ የተሰኘ ፊልም ነው:: ይህ ፊልም የሂሳብ ሊቅ ስለሆነው ጆን ናሽ የሚያወራ ነው:: ናሽ በሂሳብ ዘርፍ አለምአቀፍ እውቅና ያስገኘለት ትልቅ ሂሳባዊ ግኝት ቢያገኝም የሩሲያ ሰላዮች እየተከተሉኝ ነው የሚለው ቅዠቱ ግን ከእውቀቱ በላይ ዋነኛ መታወቂያው ሆኗል:: ናሽ ገና በጊዜ የዚህ ህምም ተጠቂ መሆኑ ታወቆለት እርዳታ ሲያገኝ የኖረ ሲሆን በእኛ ሀገር ግን ስለነገሩም ያለን ግንዛቤ አነስተኛ በመሆኑ ብዙ ሺህ ሰለባ የሆኑ ሰዎች ልታሰር ነው ፤ እየተከተሉኝ ነው ሲሉ አብረናቸው እየተከተልን እናብዳለን:: እነዚህ ሰዎች አንዳንዴም በሀይማኖት ተቋማት ውስጥ ገብተው ራእይ ታየን ፤ ትንቢት ተነገረን ፤ እንዲህ ሊመጣ ነው ፤ እንዲህ ልንሆን ነው እያሉ ህዝብን ያስጨንቃሉ:: የሆነ ሆኖ ግን ብዙውን ጊዜ ተግባራቸው በአደባባይ የሚታይ በመሆኑ እነሱን የሚከተል ሰላይም ሆነ ሌላ የለም::

ሶስተኛው እና ዋነኛው ጉዳይ ብዙዎች እንዲዚህ የሚሉት የሚኖሩበትን ሀገር ከመርሳት ነው:: የምንኖረው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው:: ኢትዮጵያ ደግሞ በየደቂቃው አዳዲስ ጠላቶች ተፈልፍለው የሚያድሩባት ሀገር ናት:: እስኪ ዙሪያችንን እንመልከት ፤ በምስራቅ አልሸባብ አለ:: አልሻባብ የቀን እና የሌሊት ምኞቱ የአፍሪካ መዲና የሆነችው አዲስ አበባ ገብቶ ቦንብ አፈንድቶ የቻለውን ያህል ኢትዮጵያዊ መፍጀት እና የዜና ርእስ መሆን ነው:: በምእራብ ኦንግ ሸኔ ፤ የጋምቤላ ነጻ አውጪ ፤ የቤኒሻንጉል ነጻ አውጪ ወዘተ አሉ:: የእነዚህ ምኞት ደግሞ ኢትዮጵያን ማፍረስ ነው:: በሰሜን ህወሀት አለ:: ከዚያ ደግሞ የግብጽ እና ሌሎች የኢትየጵያ ጠላቶች ከነተላላኪዎቻቸው አሉ:: ሌሎች ወዳጅ ነን የሚሉ ሀገራትም እንደ አቅማቸው ለራሳቸው ጉዳይ አስፈጻሚነት የሚያሰማሯቸው ብዙ ሀይሎች አሉ:: በመንግስት ውስጥ ተሰግስገው ለጠላት መረጃ የሚያቀብሉ ባንዳዎችም በስፋት አሉ:: ታዲያ እነዚህ ሁሉ ባሉበት መንግስት እንዳንተ አይነቱን የፌስቡክ አርበኛ ሲከታተል የሚውልበት ምን ምክንያት አለው ያለንበትን ሀገር እና ሀገራችን ያሏትን ጠላቶች ብዛት እና የጥፋት እቅድ ብናውቅ እንዲህ አይነት ቅዠት ውስጥ አንገባም::

ሲጠቃለል ፤ ለማለት የተፈለገው ፤ ወገኔ ሆይ በሌለ ነገር ራስህን አታስጨንቅ:: ከመጻፍ እና ከመናገር ያለፈ ሀገርን የሚጎዳ ነገር ውስጥ እስካልገባህ ድረስ ጀርባህን አይከበድህ:: ዘና ብለህ ኑር::

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

## በዓባይ ላይ የጀገነ እድለኛና ባለድል ትውልድ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ሰው ብዙ ተፈጥሮ አለው፤ ከዛኛው አለም ወደዚህኛው አለም ሲመጣ ለራሱና ለሌሎች ታሪክ ሰርቶ እንዲያልፍ ነው:: የሰው ልጅ አቅሙን፣ ሀይሉንና ተፈጥሮውን መጠቀም ከቻለ ታሪክ የማይሰራበት ምንም ምክንያት የለም:: ታሪኮቻችን የተቀመጡት በእኛ የማሰብ አቅምና የማድረግ ሀይል ውስጥ ነው:: ታሪክ መስራት ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ብርቃችን አይደለም:: በተለያየ ጊዜ አለምን ያስደነቁ፣ ከሰው ልጅ አቅም በላይ የሆኑ በርካታ ታሪኮችን ሰርተናል:: አሁንም እየሰራን ነው:: ለአብነት ብንጠቅስ እንኳን የአድዋ የድል ታሪክ አለም የሌለው፣ ለአፍሪካውያን ብርቅ የሆነ የእኔና የእናተ የጋራ ታሪካችን ነው:: በተለያዩ ጊዜ፣ በተለያየ ቦታ አባቶቻችን በአንድነትና በህብረት ታሪክ ሰርተዋል:: ዛሬ ላይ በክብር የምንጠራባቸውን እልፍ የኩራትና የሞገስ ታሪኮችን አስረክበውናል:: የአባቶቹን የጽናት ክንድ የወረሰው ይሄኛው ትውልድ ደግሞ በአባይ ላይ ጀግኖ እንሆ የአባቶቹን ህልምና ምኞት እውን አድርጎታል:: ይሄ ትውልድ እኔና እናተ ነን፤ ይሄ ትውልድ በመቻል፣ በማድረግ፣ በማሸነፍ የተካነ የአባቶቹ የጽናት ጽንስ የጸነሰው ትውልድ ነው::

ሀገርና መንግስት ከግለሰብ የሚጀምሩ የብዙሀን ስፋት ናቸው:: ሀገር ራዕይ እንዳለው ትውልድ፣ ራዕይ እንዳለው መሪ፣ ራዕይ እንዳለው ዜጋ የሚባርካት የለም:: አሁን ላይ ሀገራችን ኢትዮጵያ ራዕይ ባላቸው መንግስትና ህዝቦቿ እየተባረከች ነው:: ይሄን እውነት ከሚያረጋግጡ ማስረጃዎች ውስጥ ሁለቱን መዘዤ ላውጋችሁ:: መነሻዬ በአባይ ላይ ስለጀገኑ እድለኛና ባለ ድል ትውልዶች ነው:: ታላቁን የህዳሴ ግድብ ተንተርሼ ስለዚህ ትውልድ እድልና ድል ላውጋችሁ:: እንደሚታወቀው ይሄ ትውልድ ቁጭት የነቀነቀው፣ የአባቶቹን አደራ ውስጡ አኑሮ እድልና ድልን በመጠበቅ የሚንቀሳቀስ ትውልድ ነው:: ከስንት አንድ ጊዜ ካልሆነ ብዙ ጊዜ እድልና ድል አንድ ላይ አይመጡም:: ሲመጡ ግን ሌላ ናቸው..ትውልዱን ባለታሪክ፣ ህዝቡን ባለማዕረግ ነው የሚያደርጉት:: እድልና ድል በአንድ ላይ ሲመጡ ተዐምር ነው የሚፈጥሩት..ታሪክ ነው የሚሰሩት:: ይሄኛው በአባይ ላይ የገነነው የእኔና የእናተ ትውልድ እድልና ድል በአንድ ላይ የመጡለት ትውልድ ነው::

በዚህ ትውልድ አብራክ ስር እንደ መብቀል ኩራትና ሰውነት አለ ብዬ አላስብም:: በሁለት ተርባይንና ጀነሬተሮች ይሄ ትውልድ ታሪክ ከመስራት ባለፈ የአባቶቹን እውነት፣ የያኔውን ትውልድ ምኞት የመለሰ ትውልድ ነው:: ጠቅላይ ሚኒስተር አብይ አህመድ በሶስተኛው የውሀ ሙሌት ስነስርዐት ላይ ተገኝተው ባስተላለፉት መልዕክት ላይ በአባይ ላይ የጀገነውን ይሄኛውን ትውልድ ‹እድለኛና ባለ ድል ትውልድ› ሲሉ ነበር የገለጹት:: አያይዘውም ‹አባይ ሲገደብ እንደማየት፣ ሲፈስ እንደማየት፣ በእጅ እንደመዳሰስ ፣ ሀይል ሲያመነጭ እንደማየት እድለኝነት አለ አልልም:: ይሄ ትውልድ እድለኛና ባለ ድል ትውልድ ነው› ነበር ያሉት:: እውነት ነው የዚህ ትውልድ አንድ አካል ሆኖ በአባይ ላይ እንደመጀገን እድለኝነት አለ አልልም:: የጥንት አባቶቻችን አባይን ገድበው ሀይል የማመንጨት ጽኑ ፍላጎት ነበራቸው:: ግን እድል አልነበራቸውም:: ግድቡን ገድቦ ሀይል እንዲያመነጭ የሚያደርግ እውቀትና ቴክኖሎጂ፣ የተማረ የሰው ሀይልም አልነበራቸውም:: ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ የግድቡን ወጪ የሚሸፍን የፋይናንስ አቅም አልነበራቸውም::

ከእኔና ከእናንተ በፊት ያሉት አባቶቻችን ልክ እንደቀደሙት ሁሉ አባይን ከመገደብ ባለፈ ህልምና ምኞታቸውን እውን የሚያደርጉበት ምንም አጋጣሚ አልነበረም:: እርግጥ ላመል እድል ነበራቸው ድል ግን አልነበራቸውም:: አንድ ነገር በተፈለገው መልኩ ውጤት እንዲያመጣ እድልና ድል ግድ ይሉታል:: እድል ወደ ድል የሚወስድ ጎዳና ነው:: በሰአቱ አባቶቻችን እድላቸውን እንዳይጠቀሙና ወደ ድል እንዳይቀይሩት ሳንካ ተፈጥሮባቸው ነበር:: የግብጽና የአንዳንድ ምዕራባውያን ክፋትና ራስወዳድነት ታክሎበት አባይ ሳይገደብ በምኞት ብቻ እንዲቀር ሆነ:: አባይ ግን አልሞተም በእያንዳንዱ ልብ ውስጥ በቁጭትና በሀሳብ ነበር:: በዘፈንና በግጥም፣ በፉከራና በቀራርቶ እየተሰደበና እየተገላመጠ፣ እየተናቀና እየተወደሰ መኖሩን ቀጠለ:: አባቶቻችን አርግዘው ሳይወልዱት ለእኛ አደራ ብለውን አለፉ:: እንሆ አባይ ተንከባሎ እድለኛውና ባለድሉ ትውልድ ላይ ደረሰ:: እንሆ በኢትዮጵያውያን የተባበረ ክንድ አባይ ተሞሸረ:: እኛም እልል አልን::

> **ሀገር ትውልድ ብኩን የሚሆኑበት አንድ አጋጣሚ ቢኖር መለያየት..መገፋፋት ነው:: ትውልድ በአንድነት ከቆመ ሁሌም ታሪክ አለው:: ሁሌም ታሪክ መስራት ይችላል:: አድዋም ሆነ አባይ የምንም ሳይሆን የአንድነታችን ሚስጢር ነው**

አባይ ሊዳር አሸወይና እየተባለለት ነው..:: በዋዜማው እለት ላይ በብዙ ሳቅና በብዙ ተስፋ ገጻችንን በብርሀን ኩለን እየጠበቅነው ነው:: ጎጆ ወጥቶ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ከድህነትና ከኋላቀርነት ሊያወጣ እንሆ ከነግርማ ሞገሱ እየደነፋ ነው:: ተጠናቆ እልል የምንልበት ጊዜ የሁላችንም የዳግም ትንሳኤ ቀን እንደሚሆን አምናለው:: እስከዛው ግን እንደ አይናችን ብሌን፣ እንደ ህልውናችን መሰረት እንጠብቀዋለን ምክንያቱም አባይ ማለት ከግድብ ባለፈ የአንድነታችን ምስክር፣ ከሀይል ማመንጨት ባለፈ የወንድማማችነታችን ካርታ ነውና:: አፋፍ ላይ ነን..በአባይ ልንስቅ..በአባይ መከራችንን ልንረሳ:: በአባይ የልፋታችንን ልንበላ፣ የአንድነታችንን ውጤት ልናይ:: በአሁኑ ወቅት የግድቡ የሲቪል ስራዎች ግንባታ ዘጠና አምስት ከመቶ የተጠናቀቀ ሲሆን ሌሎች ተያያዝ ስራዎች እንዳሉ ሆነው አጠቃላይ አፈጻጸሙ ደግሞ ሰማኒያ ሶስት ከመቶን የዘለለ ሆኖ ተገኝቷል:: በዚህም መሰረት በያዝነው አመት የህዳሴ ግድቡ ካሉት ተርባይኖች በሁለት ዩኒት (በሁለት ተርባይንና ጀነሬተር ) ሀይል ማመንጨት እንዲጀምር የማድረግ ስራው ተጠናቆ በሁለት መቶ ሰባ አምስት ሜጋ ዋት ታላቁ የህዳሴ ግድባችን ሀይል ማመንጨት ጀምሯል::

አጠቃላይ የፕሮጀክቱ ስራ በሁለት አመት ውስጥ እንዲጠናቀቅ እየተሰራ ሲሆን በቀጣይ አመታት ውስጥ አባይ አልቆ ሙሉ በሙሉ ሀይል ወደማመንጨት ሲሸጋገር ከእድገትና ከስልጣኔ ባለፈ ደስታችንን በጋራ የምንቋደስበት ጊዜ ሲሩቅ አይሆንም:: እስከዛው የቀሩትን ጥቂት አመታት በተለመደው አንድነትና ፍቅር በተባበረ ክንድ ትንሳኤውን እውን ማድረግ ይጠበቅብናል:: አባይ በብዙ ልዩነት ውስጥ አንድነትን የሰጠን ፣ በብዙ መለያየት ውስጥ ያስተቃቀፈን ጽናታችን ነው:: ከአድዋ ቀጥሎ የተከሰተ የትውልድ ክስተት ነው:: ኢትዮጵያውያን በአንድነት ከተነሱ ምንም ማድረግ እንደሚችሉ ለአለም ያሳዩበት፣ ጠላቶቻችንን አንገት ያስደፋንበት የክብራችን ማህተም ነው:: ከአድዋ ቀጥሎ ትውልድ የሚዘክረው የዚህኛው የእኔና የእናተ ሀቅ ነው:: ኢትዮጵያ የምትጠራበት የዚህኛውና የዚያኛው ትውልድ እልፍ የታሪክ ጌጥ ያላት ቢሆንም:: አባቶቻችንን ስናስብ አድዋን ይሄኛውን ትውልድ ስናስብ ደግሞ የህዳሴ ግድባችንን እናስታውሳለን::

ትውልድ ሁሌም ታሪክ እንደሰራ ነው:: የታሪክ ማብቂያ መለያየት ነው:: ሀገር ትውልድ ብኩን የሚሆኑበት አንድ አጋጣሚ ቢኖር መለያየት..መገፋፋት ነው:: ትውልድ በአንድነት ከቆመ ሁሌም ታሪክ አለው:: ሁሌም ታሪክ መስራት ይችላል:: አድዋም ሆነ አባይ የምንም ሳይሆን የአንድነታችን ሚስጢር ነው:: አሁንም በአንድነት ቆመን እንደ ህዳሴ ግድባችን አይነት ከድህነትና ከኋላቀርነት ከልመናም ሊያወጣን የሚችል የእድልና የድል አሻራችንን እንድናሳርፍ አደራ እላለው:: በአባይ ጉዳይ ላይ የግብጽና የሱዳን የሌሎች ምዕራባውያን ተጽዕኖ ምን ያክል እንደነበር እናውቀዋለን:: በአንድነት መክተን አሸነፍነው እንጂ ተለያይተን ቢሆን ኖሮ አባይን በዚህ ልክ አናየውም ነበር:: ጠላቶቻችን መቼም የእኛን ደስታ፣ የእኛን ሳቅ፣ የእኛን ስኬት ማየት አይፈልጉም:: ከሰው በታች፣ ከሀገር ኋላ ቀርተን ለማኝና ተመጽዋች ሆነን፣ ሲጠሩን አቤት ሲልኩን ወዴት እያልን ታዛዥ ሆነን እንድንኖር ነው የሚፈልጉት:: በተመኙነው ልክ እንድናድግ፣ በምንፈልገው ልክ ቀና እንድንል የአንድነት ክንዳችን በፈጠሩት አባይ ላይም ሆነ በማንኛውም ሀገራዊ ጉዳይ ላይ ልንተባበር ይገባል::

ጠላቶቻችንን የምናሳፍርበት ብቸኛው መንገድ አንድነት ነው:: ኢትዮጵያዊነት አስፈሪና ገናና የሚሆነው በአንድነት ውስጥ ብቻ ነው:: አባይ እንዴት ተገነባ? የአድዋ ድል እንዴት መጣ? ጣሊያንንና ግብጽን፣ እንግሊዝንና ሱማሊያ፣ ሌሎች ወደረኞቻችንን እንዴት ረታን ብለን ስንጠይቅ ስልጣኔ ሳይሆን፣ ዘመናዊነት ሳይሆን፣ እውቀትና ጥበነብ ሳይሆን አንድነትን ነው የምናገኘው:: ማሸነፋችን ያለው አንድነታችን ውስጥ ነው:: አብዛኞቹ ታሪኮቻችን፣ አብዛኞቹ እሴቶቻችን በጋራ ሀሳብ፣ በጋራ እምነት፣ በጋራ ፍቅር እውን የሆኑ ናቸው:: እናም በእድለኛና በባለድል ስም አባይን ጨርሰን ሌላ ግድብ፣ ሌላ ታሪክ እንድንሰራ የጽናት ክንዶቻችን ከአብሮነት አይቦዝኑ እላለው:: ለሀገር መልፋት ለራስ መልፋት ነው:: ይሄ ትውልድ ዝም ብሎ ባለድል አልሆንም..:: የገባው የሆነ ነገር አለ እላለው:: ሰው እውነት ሲገባው ለእውነት ብቻ ነው የሚለፋው:: ሰው ፍቅርና ፍትህ ሲገባው ለፍቅርና ለፍትህ ብቻ ነው የሚኖረው:: መለያየት ምን ያክል ክፉ እንደሆነ ይሄ ትውልድ ገብቶታል እላለው:: ከአባቶቹ የወረሰውን የመቻልና የማድረግ ወኔ አባይን እንዲገነባ መንገድ ከፍቶለታል:: ድህነት፣ ኋላ ቀርነት ክብረ ነክ እንደሆነ አውቆታል::

ልክ እንደ ህዳሴ ግድባችን አንዳንድ ታሪኮች ፍቅር ብቻ ነው የሚፈልጉት:: አባይ የመቶ ሀያ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን የፍቅር፣ የጽናት፣ የተስፋ፣ የህብረት ውጤት ነው:: የብዙ ድሀ ልቦች፣ የበርካታ ምስኪን ነፍሶች የደግነትና የመስጠት ሚስጢር ነው:: እንጂማ ምን ኖሮን፣ ምን ተርፎን አባይን የሚያክል ግዙፍ ፕሮጀክት እንገነባለን? አትጠራጠሩ አባይ የቆመው በፍቅር ነው:: አትጠራጠሩ አባይ የቆመው በህብረት ነው:: አባይ የቆመው በጽናት ነው:: ከድሀ እናት ላይ በተሰጠ አምስት ሳንቲም እውን የሆነ ነው:: አለም ፍቅር ያልታከለበት ታሪክ የላትም:: ውብ ነገሮች ሁሉ በፍቅር ቀለም የተቀለሙ ናቸው:: ፍቅር ያልታከለበት ታሪክ ታሪክ መሆን አይችልም:: የታሪክ መሰረት ፍቅር ነው:: ልብ በታሪክ ውስጥ ፍቅርን ሲያጎድል ትውልድ አስቦ የማይደርስበት የሆነ ባዶነት ይፈጠራል:: እነዛ ባዶነቶች የሚያጨቃጭቁን፣ የሚያገፉፉን፣ የሚያጠላሉን፣ የሚለያዩን፣ እኔነትን የሚፈጥሩብን፣ ራስወዳድነትን የሚያለብሱን፣ ብሄር ተኮር፣ ዘር ተኮር እሳቤን የሚያስተምሩን ናቸው:: እናም በታሪኮቻችን ላይ የጻፍናቸውና እየጻፍናቸው ያሉ አንዳንድ ጎደሎ ታሪኮች ፍቅር ባልነካው ልብ የሆኑ ናቸው ብል አደራ እመኑኝ:: ምክንያቱም ፍቅር ለምንም ነገር ምንም ነገር ነውና::

ሰው የሆነ ቦታ ላይ ፍቅርን በሚያውቅ ልቡ ሀገሩን ይፈጥራል:: በህልሙ ውስጥ ራሱን፣ በራሱ ውስጥ ሀገሩን:: ሰው በህልሙ ውስጥ ራሱን ከፈጠረ፣ በራሱ ውስጥም ሀገሩን ከሰራ ብቻውን ታሪክ የሰራ ጀብደኛ ነው:: አባይ በፍቅር ላይ የቆመ ነው ብያችሁ የለ? እስኪ ፍቅር በተሞላ ልብ በህልማችን ውስጥ ራሳችንን፣ በራሳችን ውስጥ ሀገራችንን እንፍጠርና ትውልድ ገልጦ የሚያነበን ጀብደኞች እንሁን:: ሰው ፍቅር ከገባው ምንም ባይገባው ልክ ነው:: ብዙ ነገሮቻችን ልክ የሚሆኑት፣ ብዙ ጥያቄዎቻችን መልስ የሚያገኙት በፍቅር ውስጥ ስንከውናቸው ነው::አባይን በፍቅር ገድበንዋል::በአንድነት ከምንምነት ወደልዕልና መልሰንዋል:: አሁንም ፍቅር የሚሹ አንድነት ግድ የሚላቸው ብዙ ምንሞች በዙሪያች አሉ:: ጥላቻና መገፋፋት፣ ቂም በቀል ያሻገታቸው ብዙ ምንሞች አሉን..በፍቅር እስካላከምናቸው፣ በውይይት እስካልፈታናቸው ድረስ ነፍስ አይዘሩም:: በእድልና በድል በአባይ ላይ እንደገነነን ሁሉ በችግሮቻችን ላይም ለመግነን ፍቅርና አንድነት ያሹናል::

ኢኮኖሚ

# ግብርና

## የፋይናንስ አማራጮች የሚፈልገው የግብርና ዘርፍ

ስምስም መንግሥቱ



ግብርናው በፋይናንስ አቅርቦት ከተደገፈ ዘመናዊ እርሻን በማስፋፋት ከግብርናው የሚጠበቀውን ምርትና ምርታማነት ማሳካት ይቻላል፤

የግብርናውን ዘርፍ በገንዘብ ለመደገፍ በተለይም ባንኮች የብድር አገልግሎት ለዘርፉ አለማመቻቸታቸው በዘርፉ እድገት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ በዘርፉ እንዲሁም በምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች እንዲሁም በመንግስትም ዘንድ በተደጋጋሚ ይገለጻል:: የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በማንቀሳቀስ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው ግብርና የፋይናንስ አቅርቦት ትኩረት ሳያገኝ ባንኮች ባለሀብቶች በከተሞች ለሚገነቧቸው ህንጻዎች በማበደር ላይ ብቻ መጠመዳቸውን ሁሌም እየተተቸ ነው:: ሀገሪቱ ለግብርናው ዘርፍ ፋይናንስ የማይቀርብባት ተብላም በግብርናው ዘርፍ ባለሙያዎች ትጠራለች::

ግብርናው በባንክ ብድር አለመደገፉን በተመለከተ የወጪ ንግዳቸውና የተለያየ ምርታቸው በግብርና ምርት ላይ የተመሰረተው ባለሀብቱ አቶ በላይነህ ክንዴ ፤እንደ ሀገር ግብርናውን ፋይናንስ የማድረግ ፍላጎት ዝቅተኛ እንደሆነ ይገልጻሉ:: ‹‹ባንኮች የብድር ማስያዣና የሚያምኑት ደንበኛ ይፈልጋሉ የሚሉት ባለሀብቱ፣ የግብርና ሥራ ተፈጥሮን መሠረት አድርጎ ወቅትን ጠብቆ መከናወኑና የመስኖ ልማትም አለመጠናከሩ የግብርናው ዘርፍ ከባንክ ብድር እንዳያገኝ አመኔታ እንዳይኖር ያደረገ አንዱ ምክንያት ሆኖ ይወሰዳል ሲሉ ያብራራሉ::

ምርትን በመጨመር ካፒታልን ማሳደግ እንደሚቻል ባለሀብቱ ጠቅሰው፣ በሙሉ አቅም ያለማምረትና ለእርሻ የሚውለውን መሬት ሁሉ ለግብርና ሥራው ያለማዋል ክፍተት ለምርትና ምርታማነት አለማደግ አንዱ ምክንያት መሆኑንም ያመለክታሉ::

እንደ ባለሀብቱ ገለጻ፤ በግብርና ሥራ ብቻ ለውጥ ለማምጣት ከፍተኛ ጥረት ቢደረግ እንዲሁም ሁለትና ሶስት እጥፍ ማምረት ቢቻል የግብርና ውጤትን ለውጭ ገበያ በመላክ የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ማሳደግ ይቻላል:: የቅባት እህል የሚመረትባቸው አካባቢዎች በፀጥታ ምክንያት የምርት መስተጓጎል አጋጥሟቸው እንኳን ቡና ለውጭ ገበያ በማቅረብ የተሻለ ገቢ መገኘት መቻሉ ግብርናው ምን ያህል ኢኮኖሚውን እንደሚያግዝ አንዱ ማሳያ ነው:: በመስኖ የማልማት ጥረቶች ቢኖሩም ከፍተኛ ውጤት በሚያስገኝ መልኩ ባለመከናወኑ ምርታማነቱ የሚፈለገውን ያህል አልሆነም:: በመስኖ የማልማቱ ባህል ቢጠናከር ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ ይቻላል::

ለአብነት ቡናን ወስደው ሲያብራሩም ቡናን በመስኖ ማልማት ቢቻል ከተለመደው የልማት ዘዴ ከሁለት እጥፍ በላይ ምርት ማግኘት እንደሚቻል ተሞክሮዎች ይጠቁማሉ ሲሉ ይገልጻሉ:: የመስኖ ልማቱ በተፈጥሮ የሚከናወነውን የግብርና ሥራ ማገዝ ከቻለ ምርትና ምርታማነት ከፍ እንደሚልና ለካፒታል እድገት አስተዋጽኦ እንደሚኖረው አመልክተዋል:: ከዓለምአቀፍ ድርጅቶች ጋር መልካም ግንኙነት በመፍጠር ብድር የሚገኝበትን ዘዴ ማመቻቸትም ከመንግሥት እንደሚጠበቅ ነው ያመለከቱት::

የግብርናው ዘርፍ በፋይናንስ በሚፈለገው ልክ አለመታገዙና በተለይም ከባንክ ብድር አለማግኘቱ ለምን ይሆን? በሚል ጥያቄ ያቀርብናላቸው የምጣኔ ሀብት እና የፖሊሲ ባለሙያው ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በረኸተስፋ እንደሚሉት፤ ኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አላት:: በውሃ ሀብቷ የምሥራቅና የሰሜን አፍሪካ የውሃ ቁንጮ በሚል ትታወቃለች:: በየአመቱ ከ120 ቢሊየን ኪዩቢክ ኪሎ ሜትር በላይ በአማካይ በሀገሪቱ አራት አቅጣጫዎች ወንዞች ይፈሳሉ:: ወደ72ሚሊየን ሄክታር የሚሆን ለእርሻ የሚውል መሬትም አላት:: የህዝብ ቁጥሯም እየጨመረ ነው::

ሀገሪቱ የውሃና የመሬት ሀብቱ እንዲሁም የሚሰራ የሰው ኃይል እያላት የምግብ አቅርቦት እንደ ችግር ሊነሳ አይገባም ነበር ሲሉ ይገልጻሉ:: የፋይናንስ አቅርቦት ግብርናውን ለማሳለጥ ዋና መሠረት መሆኑንም ይጠቁማሉ::

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው የሌሎች ሀገሮችን ተሞክሮ በመጥቀስ ሲያብራሩ እንዳሉት፤ ብዙ የአፍሪካ ሀገሮች በቅኝት ግዛት ዘመን ያዳበሩት ሥርዓት አላቸው:: ለአብነትም ዚምባቡዌ የዶላር ምንዛሬ ዋጋ ሲጨምርና የተለያየ ችግር ሲያጋጥም የምግብ ጉዳይ ግን ሀገሪቱ ውስጥ እንደችግር ተነስቶ አያውቅም:: ሀገሪቱ የግብርና ውጤቶችን ለውጭ ገበያ በማቅረብ ገቢ ታገኛለች:: ችግሮችም ኖሮው በሀገሪቱ የምግብ አቅርቦት ችግር አለመፈጠሩና በወጪ ንግዱ ላይም ተጽዕኖ አለመፈጠሩ የግብርና ሥራው የተስፋፋ በመሆኑ ነው:: የግሉ ዘርፍም በሀገሪቱ በስፋት ይንቀሳቀሳል::

**የግል ባንኮች እስካሁን ለእርሻ ልማት ወይንም ለኢንዱስትሪ ያመቻቹት ብድር ወይንም ፋይናንስ በማድረግ የሰጡት አገልግሎት ይኖር እንደሆነ ቢጠየቅ ምናልባት አንዳንዶች ይኖሩ እንደሆን እንጂ መልስ ለማግኘት እርግጠኛ ለመሆን ያስቸግራል፡፡ ባንኮቹ የልማት ሳይሆኑ ለአክሲዮን ባለድርሻዎቻቸው የሚያገለግሉ ናቸው፤ የፖሊሲ ባንኮች አይደሉም**

የኢትዮጵያ ግብርና የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችንም ጭምር ለተቃውሞ ያነሳሳ እንደነበር ጠቅሰው፣ ለዚህም የተማሪዎችን የመሬት ላራሹ ጥያቄ በአብነት ያነሳሉ:: ባለፈው ስርአትም መንግሥት አራት ሚሊየን ሄክታር መሬት በሊዝ ለኢንቨስተሮች ለመስጠት ውሳኔ በማሳለፍ ወደ እንቅስቃሴ ገብቶ እንደነበርም አስታውሰው፣ ውሳኔው ግን የሚፈለገውን ውጤት አላስገኘም፤ ከባድ ችግር ነው ያጋጠመው ይላሉ::

ኢንቨስተሮቹ ከልማት ባንክ ገንዘብ ወስደው ገንዘቡን ለሚፈለገው ዓላማ ሳያውሉት በመቅረታቸው በባንኩ ላይ ችግር መፍጠራቸውን ጠቅሰው፣ በእርሻ ሥራ ላይ ለመሰማራት ከልማት ባንክ ብድር የወሰዱ የሀገር ውስጥ ባህብቶችም ቢሆኑ፣ የእርሻ ሥራን የማያውቁ ስለነበሩ ገንዘቡን ለግል ጥቅማቸው ነው ያዋሉት ሲሉ ያብራራሉ::

በፋይናንስ አጠቃቀም ላይ ክፍተቶች ቢኖሩም፣ አሰራርን ማስተካከል እንጂ ፋይናንስ ለዘርፉ አስፈላጊ ነው የሚሉት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፣ በግብርናው ዘርፍ ለመሰማራት ለሚፈልጉ ኢንቨስተሮች የብድር አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ያስፈልጋሉ ብለዋል :: ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የፋይናንስ ሥርዓት ለውጭ ባለሀብቶችም ሆነ ለውጭ ባንኮች ዝግ እንደሆነም ተናግረው፣ ይህም አንዱ ችግር መሆኑን ነው ያስታወቁት:: የግብርናው ዘርፍ በፋይናንስ ተጠቃሚ ሲደረግም የማስተዳደር አቅም ሊኖር እንደሚገባም ነው ያመለከቱት::

የግል ባንኮች እስካሁን ለእርሻ ልማት ወይንም ለኢንዱስትሪ ያመቻቹት ብድር ወይንም ፋይናንስ በማድረግ የሰጡት አገልግሎት ይኖር እንደሆን ቢጠየቅ ምናልባት አንዳንዶች ይኖሩ እንደሆን እንጂ መልስ ለማግኘት እርግጠኛ ለመሆን ያስቸግራል የሚሉት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፣ ባንኮቹ የልማት ሳይሆኑ ለአክሲዮን ባለድርሻዎቻቸው የሚያገለግሉ እንጂ የፖሊሲ ባንኮች አይደሉም ነው የሚሉት::

በአጼ ኃይለሥላሴ ዘመን የግብርናውን ዘርፍ ለማገዝ ተብሎ የተቋቋመ የእርሻና የኢንዱስትሪ ልማት ባንክ የሚባል እንደነበር አስታውሰው፤ አሁን ለግብርናው ዘርፍ የፋይናንስ አገልግሎት በማቅረብ በኩል ልማት ባንክ ብቻ እየሰራ መሆኑን ይገልጻሉ:: እርሱም ቢሆን ከፍተኛ ኢንቨስትመንትና ዩኒየኖች ላይ እንደሚሰራ ተናግረው፣ ምክንያቱ ደግሞ የሚያስይዙት ሀብት ስላላቸው መሆኑን ይናገራሉ:: አርሶ አደሩን በአነስተኛ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት በኩል በወረዳ ደረጃ ለማገዝ ጥረት ካልተደረገ በስተቀር አሁን ያለው አሰራር በዚህ መልኩ የተደራጀ ነው ይላሉ::

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የፋይናንስ ሥርዓቱን ለማስተካከል በሚኒስትሮች ምክር ቤትና በብሄራዊ ባንክ ደረጃ የሚደረጉ ጥረቶች ስለመኖራቸው በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን መረጃዎች ሲተላለፉ እንደሚሰማ አመልክተው፣ ከእነዚህ መካከል አንዱ የካፒታል ገበያ መቋቋም፣ሌላው የውጭ ባንኮች ካፒታል ይዘው ሊመጡ የሚችሉበትን መንገድ ለመፍጠር የሚያስችል መሆኑን ያብራራሉ::

እሳቸው እንደሚሉት፤ ኢትዮጵያ ከሌሎች ሀገሮች የተለየች መሆን የለባትም:: ጅቡቲ፣ኬኒያ ታንዛኒያ፣ዩጋንዳ ደቡብ ሱዳን፣የውጭ የፋይናንስ ተቋማት ያላቸው ሀገራት ናቸው:: በኢትዮጵያ ግን ሀገር በቀል ባንኮች እንዲስፋፉ ነው የሆነው:: በዚህ ላይ ሰፋ ያለ ውይይት አልተካሄደም:: እንደ ቻይና፣ዱባይ የመሳሰሉ ሀገራት የዕድገታቸው ምንጭ ምን እንደሆነ ተሞክሮአቸውን ማየትና መፈተሽ ይቻላል::

ከውጭ በግዥ ወደ ሀገር የሚገባውን የስንዴ ምርት ማስቀረት ብቻ ሳይሆን፣ለውጭ ገበያም በማቅረብ የውጭ ምንዛሪ የሚገኝበትን መንገድ ለማሳካት የሚቻለውም በመሥራትና ለግብርናው የሚያስፈልገውን በማሟላት ነው ይላሉ::

የመሬት ጥያቄን በተመለከተም ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በትንታኔያቸው፤የመሬት ጥያቄ ከፖለቲካ ጋር የማያያዝ ነገርም ስላለው ውስብስብ እንዲሆን አድርጎታል ይላሉ:: እርግጥ አነስተኛ እርሻ ያላቸው አርሶ አደሮች መኖራቸው ለአካባቢ ዘላቂነት ጥሩ ነው:: ነገር ግን የህዝብን ፍላጎት ማሟላት ወይንም የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ያስፈልጋል ሲሉ ይገልጻሉ::

አርሶ አደሩ መሬት ካለውና ካመረተ፣እንስሳትም ካለው ይህን ሀብቱን በማስያዝ ከባንክ የብድር አገልግሎት ማግኘት ያልቻለበት ምክንያት ምን ይሆን? የሚል ጥያቄ ያነሳንላቸው ዶክተር ቆስጠንጢኖስ ፣ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ እያሉ መንግስት አርሶ አደሩ መሬቱን አስይዞ ከባንክ መበደር የሚያስችለው መመሪያ ወጥቶ እንደበር አስታውሰው፤ አሁን ባለው አሰራር መሬት የገበሬው አይደለም ::መሬት የኢትዮጵያ ህዝብ ነው በሚል በአዋጅ ተቀምጧል:: በአዋጅ ያልተፈቀደ መሬት ይዞ ባንኩ የብድር አገልግሎት ቢሰጥና ብድሩ ባይመለስለት መሬቱን ሸጦ ብድሩን ለማስመለስ ህጉ አይፈቅድለትም ይላሉ::

የፕላን ሚኒስትር ዶክተር ፍጹም አሰፋ በቅርቡ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ባዘጋጀው በአዳማ ባካሄደው ስለ ኢትዮጵያ መድረክ ላይ የአርሶ አደሩን የመሬት ሰርተፍኬት አስመልክተው የሰጡት ግን ከባንክና መሬት ጋር የተያያዘው የአርሶ አደሩ ችግር እየተፈታ የመጣ መሆኑን ያመለክታል::

መንግስት መሬትን የኢኮኖሚ መሳሪያ ለማድረግ ባከናወነው ተግባር አርሶ አደሩ የመሬት ሰርተፍኬት እንዲያገኝ መደረጉን ሚኒስትሯ ገልጸዋል:: አርሶ አደሩ ሰርተፍኬቱን አስይዞ ከባንክ እንዲበደር እድል መፈጠሩን ጠቅሰው፣ የግብርና ስራውም የኩታ ገጠም የአስተራረስ ዘዴን በመከተል እየተከናወነ መሆኑንም ገልጸዋል:: እንዲህ ያለው እንቅስቃሴ ለምርትና ምርታማነት እድገት ትልቅ የሚባል ለውጥ እንደሆነም ነው ያስታወቁት::

ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፣ በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት አርሲና ባሌ ላይ ‹‹የጭላሎ አግሪካልቸራል ዴቨሎፐመንት ዩኒት ካዱ›› ተብሎ የሙከራ ፕሮጀክት ሥራ እንደነበር ያስታውሳሉ:: አርሲና ባሌን የስንዴና የገብስ አምራች ያደረጋቸው በወቅቱ የተቀረፀው ፕሮጀክት እንደሆነም ተናግረው፣ በወቅቱ ፕሮጀክቱ አራት ሚሊየን ዶላር ብቻ እንደወጣበትና ከስዊድን ሀገር በተገኘ እርዳታ የተከናወነ መሆኑንም ጠቁመዋል::

ሌላ ፕሮጀክት ዋዱ ተብሎ ወላይታ አግሪካልቸራል ፕሮጀክት ዩኒት ተብሎ ሊስፋፋ ሲል የወታደራዊ ደርግ መንግሥት ሀገሪቱን ሲቆጣጠር ተቋርጦ መቅረቱን ጠቅሰው፣ እንዲህ ያሉ ውጤት የሚያስገኙ ተሞክሮዎች እያሉ እንደ አዲስ ጥናት ማካሄድ አስፈላጊነቱ እንዳልታያቸውም ነው የምጣኔ ሀብት ባለሙያው የሚናገሩት::

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ‹‹ዛሬ የአርሲ ገበሬ ትራክተርና ኮምባይነር ይከራያል:: ካመረተ በኋላ ነው ክፍያ የሚፈጽመው:: በአካባቢው ላይ እንዲህ ያለ ሥርዓት ተዘርግቷል::›› ሲሉ ጠቅሰው፣ ይህን ተሞክሮ ማስፋት እንደሚያስፈልግም ያስገነዝባሉ:: ዝናብ ጠብቆ የሚያርስን ገበሬ በፋይናንስ ልደግፍ ብሎ የሚነሳ ባንክም ሆነ የኢንሹራንስ ኩባንያ አይኖርም ይላሉ::

ሀገሪቱ ከታክስ፣ከእርዳታ፣ከብድርና ከተለያየ ምንጮች የምታገኘው ገንዘብ አነስተኛ መሆኑን ጠቅሰው፣ መንግሥት ሁሉንም ፋይናንስ በማድረግ ለመደገፍ አቅም አይኖረውም ይላሉ:: የግሉ ዘርፍ ገብቶ ሲሰራ ግን የመንግሥትን ጫና እንደሚቀንስ ይገልጻሉ:: ግብርናውን ፋይናንስ በማድረግ በኩል አቅም መፍጠር እንደሚያስፈልግ ተናግረው፣ ለእዚህም ከውጭ ኢንቨስትመንትን መሳብ ይገባል፤ ይህም ኢንቨስትመንት አምራች እንዲሆን የውጭ ባንኮችና የካፒታል ገበያ በሀገር ውስጥ መደራጀት ይኖርባቸዋል ነው ያሉት::

ኢትዮ ቴሌኮም ላይ የተወሰደውን እርምጃ በአብነት ጠቅሰው ሲያብራሩም፣ መንግሥት አገልግሎቱን ለግሉ ዘርፍ ክፍት ሲያደርግ ሳፋሪኮም ኩባንያ ካፒታል ይዞ ወደ ሥራው መግባቱን ይገልጻሉ:: ወደዚህ መንገድ ለመሸጋገር ብዙ ጊዜ ቢወስድም መጀመሩ በጥሩ እርምጃ ይወሰዳል ብለዋል::

በሙስና በኩል የሚስተዋለው ችግር አንዱ ማነቆ እንደሆነ ያነሱት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፣ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ደሳለኝ ኃይለማርያም በስልጣን ላይ በነበሩበት ዘመን፣ወጣቱን በግብርናው ዘርፍ የሥራ ዕድል እንዲፈጠርለት መንግሥት ወደ አስር ቢሊየን ብር መድቦ ለምን ጥቅም እንደዋለ ግልጽ ሳይሆን እንዲሁ መቅረቱን አስታውሰው፣ ገንዘብ መመደብ ብቻ ሳይሆን ገንዘቡ በአግባቡ ለታለመለት ዓላማ መዋሉም ክትትል ሊደረግበት እንደሚገባም አስገንዝበዋል::

ዶክተር ቆስጠንጢኖስ እንደሚሉት፤ ለግብርናው ዘርፍ የተለያዩ የፋይናንስ አማራጮች መዘርጋት ያስፈልጋል፤ የፋይናንስ አቅርቦቶቹ ከውጭም ከሀገር ውስጥም መሆን ይኖርባቸዋል፤ በብድር የተገኘ የፋይናንስ አጠቃቀም ላይ ባለፉት ጊዜያት የታዩ ስህተቶች እንዳይደገሙም ፋይናንስ ማስተዳደር ላይ አቅምን ማጎልበት ይገባል:: የግብርናውን ዘርፍ ተሞክሮዎችን ከሀገር ውስጥም ከውጭ ባለሀብቶችም ሆነ ከሀገሮች ወስዶ መስራትም ሌላው የግብርናውን ዘርፍ ውጤታማ የሚያደርግ ተግባር ነው::

ማህበራዊ

# አስኳላ

# የመውጪያ ፈተናና እድሉቹ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ትምህርት የዜጎችን ሁለንተናዊ አቅም የመለወጥ አቅም አለው:: ይህ የሚሆነው ግን በአግባቡ ከተሰጠና ቅቡልነቱ ከተረጋገጠ ነው:: እናም ይህንን ለማረጋገጥ እንደአገር ብዙ ተግባራት መከወን እንዳለባቸው እሙን ነው:: አንዱና ዋነኛው ግን ብቃት የተላበሰ ተማሪ ከማንኛውም ተቋም ውስጥ ማውጣት ነው:: በተለይም ዩኒቨርሲቲ ላይ ብቃት ያለውን ተማሪ ማውጣት ካልተቻለ በብቃት የሚሰራ ባለሙያ በሁሉም ዘርፍ ለማግኘት ይቸግራል::

በብዙዎች ዘንድ አሁን ላይ እየታየ ያለውም ይኸው ነው:: ችግሩ በዋነኝነት በትምህርት ዘርፉ ውስጥ ያሉ አካላት ላይ ማነጣጠሩ አይቀሬ ነው:: ነገም ቢሆን ከታች ጀምሮ በጥራቱና ብቃት ላይ ያለው ክፍተት ካልተደፈነ ጣት መጠቋቆሙ መቀጠሉ የሚቀር አይሆንም:: እናም ለዚህ መፍትሄ ያሸዋልና እንደአገር እቅድ ተይዞላቸው የተለያዩ ተግባራት መከናወን ጀምረዋል:: ከእነዚህ ተግባራት አንዱ ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ ይተገበራል የተባለለት የዩኒቨርሲቲ መውጫ ፈተና ነው:: ለመሆኑ ይህ ፈተና መሰጠቱ ምን አይነት እድሎችን ይዞ ይመጣል ስንል የተለያዩ የዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ ኃላፊዎችን አነጋግረናል::

በመጀመሪያ ሃሳባቸውን ያጋሩን የአምቦ ዩኒቨርሲቲ የአስተማሪዎችና የተማሪዎች አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር ሰለሞን አለሙ ሲሆኑ፤ መውጫ ፈተና በርካታ መልካም ጎኖች እንዳሉት ይናገራሉ:: አንዱ ተማሪዎች በትምህርታቸው ላይ እንዲያተኩሩና ተግተው እንዲማሩ የሚያደርግ ስርዓት መሆኑ ነው:: በተማሪዎች መካከል ያለን የመወዳደር ስሜት የመጨመሪያ መንገድም ነው:: ምክንያቱም የመውጫ ፈተናውን ካላለፉ ሥራ ጭምር ማግኘት እንደማይችሉ ያውቃሉና ቀድመው እንዲዘጋጁ፤ ከጓደኞቻቸው በበለጠ ጠንክረው እንዲያጠኑና የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ያስችላቸዋል::

የጥራት ጉዳይ ተመርቆ ከወጣና ሥራ ላይ ከገባ በኋላ ጭምር የሚታይ ሆኗል:: እናም የመውጪያ ፈተናው ይህንን ከመቀነስ አኳያ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል:: ምክንያቱም ተማሪዎች መውጪያ ፈተናውን ሲያስቡ ከክፍል ፈተናው ባለፈ አገራዊ ፈተናውን አስበው በቂ እውቀት ለመጨመጥ እንዲጥሩ ይሆናሉ:: ተወዳድረው ለመመረጥ ደግሞ አንዱ መስፈርት የሚሆንበት አጋጣሚ ይኖራልና ይህንን እውን ለማድረግም ትጉ እንዲሆኑም ያስችላቸዋል:: ከዚህ ትይዩ ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡትንም ሆነ ለመመረቅ የተቃረቡትን ከገቡበት ዓመት ጀምሮ እስከሚመረቁበት ዓመት ድረስ ያለውን ጊዜ በአግባቡ እንዲጠቀሙና በቂ እውቀት ጨብጠው እንዲወጡ ከማስቻሉም አኳያ የማይተካ ሚና እንደሚኖረው ይናገራሉ::

ዩኒቨርሲቲዎች ዓለም አቀፍ ውድድሩን ለመሸከም የሚያስችል ዕውቀት ማፍሪያ ማዕከል እንዲሆኑም እድል የሚሰጥ ነው የሚሉት ዶክተር ሰለሞን፤ ከትምህርት ጥራቱ ይልቅ ቁጥሩ የሰፋበትን አጋጣሚም ለማመጣጠን ይህ እድል ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል:: በተመሳሳይ ዩኒቨርሲቲዎች ጥሩ ዕውቀት ያላቸው ተማሪዎች ማፍራት ብቻ ሳይሆን ጥሩ ዜጎችም የሚገኙበት ተቋም እንዲሆን ያስችላል:: ከዚያም ሻገር ሲል ተማሪዎች በመጨረሻ ፈተና እንደሚወስዱ አውቀው ቀድመው በአካል፣ በስነ-አዕምሮና በስነ- ልቦና በመዘጋጀት ጠንክረው እንዲሰሩ እንደሚያደርጋቸውም ያነሳሉ::

የመውጪያ ፈተና ከአምስት በመቶ በላይ መድገም የለባቸውም የሚለውን የዩኒቨርሲቲዎች አሰራርም የሚያስቆም ነው:: ብቃት ከሌላቸው መመረቅ እንዳይችሉ ያደርጋል:: የዚህን ጊዜ በመውጫው ፈተና የማሳለፍ ምጣኔ መሰረት በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በትምህርት ክፍልና በመምህር ጭምር ተጠያቂነት እንዲኖርና የመወዳደር ስሜት እንዲፈጠር እድል እንደሚሰጥም ይናገራሉ::

አሰራሩ ከዚህ ቀደም በህግ እና ጤና ትምህርት ክፍል እንደነበር የሚጠቅሱት ዶክተር ሰለሞን፤ አሁን ልዩነቱ ሁሉም ላይ መሆኑ ነው:: ጥራቱ ላይ በሁለቱ የትምህርት መስኮች የታየውንም ይደግመዋል እንጂ ተማሪው ላይ የሚፈጥረው አሉታዊ ተጽዕኖ አይኖርም:: ስለሆነም ተማሪዎች እኛ ላይ ችግር ለመፍጠር አስበው ነው በሚል ሳይጨናነቁ ትምህርታቸው ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ያሳስባሉ:: ለዚህ ደግሞ ዩኒቨርሲቲያቸው ከወዲሁ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል::

እንደ አገር ፈተናው የሚሰጥ ከሆነ አንዳንድ ክፍተቶች ሊኖሩ ይችላሉ:: ምክንያቱም በተማሪዎችና በዩኒቨርሲቲዎች መካከል እንደ ትውልድ(ጀነሬሽን) ልዩነቶች ተፈጥረዋል:: ለምሳሌ፡- ዩኒቨርሲቲ ሲገቡ ከፍተኛ ውጤት ያመጡት የመጀመሪያ ምርጫቸው ይከበርላቸዋል:: በዚህም የመጀመሪያ ትውልድ (ጀነሬሽን) የሚባሉት አቅም ያላቸውን ተማሪዎች የመሰብሰብ አጋጣሚ ይፈጠርላቸዋል:: እናም ሌሎቹ እንደአምቦ ዩኒቨርሲቲ የመሳሰሉት ላይ ይገባሉ:: ይህ ደግሞ የተማሪዎች የብቃት ልዩነት እንዲኖር ያደርጋል:: በተጨማሪም በግብዓት አቅርቦት እኩል ሊወዳደሩ አይችሉም:: ስለሆነም ቀጣዮቹ እየተስተካከሉ ሊመጡ እንደሚችሉ አመላካች ነገሮች በመኖራቸው የአሁኑ ላይ ግን ብዙ ጥንቃቄ እንደሚፈልግ ይናገራሉ::

የደብረታቦር ዩኒቨርሲቲ አካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር ክንዴ ገበየሁ እንደሚያምኑበት በትውልድ(ጀነሬሽን)መካከል የሚመጣ ልዩነት መኖሩ አይካድም:: ይሁን እንጂ የመውጪያው ፈተና ሙያ ተኮር በመሆኑ ያንን ማለፍ ካልቻሉ የትውልዱ ልዩነት ነው ልንል የምንችልበት ሁኔታ አይኖርም:: ተማሪዎቹ ባለሙያ ሆነው አገራቸውን በሚጠቅሙበት ልክ መውጣት አለባቸው:: ምክንያቱም ሲወጡ የእንትና ዩኒቨርሲቲ ተማሪ ሳይሆን የሚባሉት በዚህ ሙያ የተመረቀ ተማሪ ነው:: እናም በሁሉም የአገሪቱ ክፍል እንደሚመደቡ ይታወቃልና ለሙያው ብቃት ያላቸው ተማሪ መሆን ግዴታቸው ነው:: ለሥራ ብቁ ሳይሆኑ ማስመረቅ ደግሞ አደጋው ምን ያህል እንደሆነ እንደሀገር ተመልክተነዋል ይላሉ:: ስለሆነም ይህንን አስቦ መሥራት እንደሚያስፈልግ ይናገራሉ::

የመውጫ ፈተናው ለትምህርት ጥራት መረጋገጥ ብቸኛ ባይሆንም ወሳኝ ጉዳይ እንደሆነ የምንገነዘበው ተማሪዎቻችን ብሔራዊ ፈተናውን ተፈትነው ሲያልፉ ነው:: ይህንን ደግሞ ዩኒቨርሲቲያችን ከዚህ ቀደም ያገኛቸው ነገሮች አሉትና ያንን እናስቀጥላለን የሚሉት ዶክተር ክንዴ፤ በጤናው ዘርፍ እስካሁን ያስመረቅናቸው ተማሪዎች በስነምግባርም ሆነ በብቃት የተሻሉ ለመሆናቸው መንስኤው ብሔራዊ ፈተና ወስደው በብቃት በማለፋቸው ነው:: አሁንም የመውጪያ ፈተና እንዳለባቸው አውቀው በቂ እውቀት ለመጨበጥ እየተጉ ይገኛሉ:: በተለይም እንደዩኒቨርሲቲ ብቃታቸውን ለመለካት ተደጋጋሚ ፈተናዎችን ያለማመድን በመሆኑ አሁን በተሞክሮ እንድንጓዝም ያደርገናል::

በሁሉም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ላይ መውጫ ፈተና መጀመሩ እንዳስደሰታቸው ያነሳሉ:: በሌሎች ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች ለማፍራት ጥሩ አጋጣሚ እንደሆነም ያስረዳሉ::

እንደመጀመሪያ ብዙ ነገሮች ፈተና እንደሚሆኑ ያልካዱት ዶክተር ክንዴ፤ ቀጣዮቹን ብሩህ ተስፋ ለማየት ይህ እድል አስፈላጊ ነው:: ስህተታችን ምን ላይ እንደሆነ እንድናይም ያደርገናል:: በተመሳሳይ አብዝቶ መትጋትን ለዩኒቨርሲቲዎች፤ ለተማሪዎችና ለመምህራኑ የሚያስተምር ነውና ጥሩና ቀጣይነት ያለውን ስርዓት ለመፍጠርም ያስችላልና ሁሉም አወንታዊ ጎኑን በማየት መስራት እንዳለበት ይጠቁማሉ::

አገራዊ ውድድር ሲታሰብ የበለጠ መትጋት ግድ እንደሆነ የሚያነሱት ዶክተር ክንዴ፤ የምናስመርቃቸው ተማሪዎችን ልዩ ትኩረት እንድናደርግባቸው ያስችለናል:: አገራችንን አስበንም እንድንንቀሳቀስ ያደርገናል:: ምክንያቱም አስመርቀን ለአገራችን የምናበረክታቸው ተማሪዎች ብቁ ባለሙያ እንዲሆኑ ማስቻል አለብንና ነው:: ከአገር አልፎ አለም ላይ የሚወዳደርና የአገሩን ስም ከፍ የሚያደርግ ትውልድ እንድንፈጥርም ይህ የመውጪያ ፈተና ትልቅ አቅም ይኖረዋልም ብለዋል::

እንደ ዶክተር ክንዴ ገለጻ፤ የመውጪያ ፈተና ሲታሰብ ኮርጆና በሌላ ላይ ተንጠልጥሎ ማለፍንም የሚያስቀር ነው:: ምክንያቱም ነገ ብቻውን የሚፈተንበት አገራዊ ፈተና እንዳለ ያስረዳዋል:: ስለዚህም ትምህርቱን በአግባቡ መከታተል ብቻ ሳይሆን በቂ እውቀት ለመጨበጥ ይጥራል:: ይህ ደግሞ መንግስትን ጠባቂ ከማድረግም ይታደጋል:: ተቀጥሬ የሚለውን ስሜትም ያጠፋል:: ምክንያቱም በጨበጠው እውቀት የራሱን የሥራ እድል በራሱ ለመፍጠር ይሞክራል:: እናም አገርን ከፍ የሚያደርጉ በራሳቸው ጭምር የሚሰሩ ባለሙያዎችን ከማፍራት አንጻር መውጫ ፈተናው ትልቅ አቅም ይኖረዋል::

የአፈጻጸም ችግሮች ካልገጠሙ በስተቀር የመውጪያ ፈተናው ከምንም በላይ ለተማሪዎች የሚጠቅምበት ሁኔታ በራስ የመተማመን አቅም እንዲኖራቸው ማድረጉ ነው:: ገና እየተማረ ባለበት ሁኔታ ለወደፊት ህይወቱ ቀድሞ እንዲዘጋጅ፤ ተወዳዳሪ እሆናለሁ የሚል ወኔ ውስጥ እንዲገባና በየትኛውም ደረጃና አካባቢ ቢመደብ ፈተና እንደማይጥለው እንዲያስብ ያደርገዋል:: አለፍ ሲልም ፍላጎቱን መሰረት ያደረጉ ሥራዎችን እንዲመርጥና እንዲሰራ ይሆናል:: ይህንን ሲያደርግ ደግሞ በአገራዊ ስሜትና በደስታ ሁኔታዎችን እንዲፈጽም እድል ይፈጥርለታልም ይላሉ::

የዶክተር ክንዴን ሀሳብ የሚደግፉት የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ዳምጠው ዳንሳ በበኩላቸው እንዳሉት፤ የመውጪያ ፈተና በእኛ አገር ብቻ ሳይሆን በሌሎች አገራት ጭምር የሚደረግና ውጤት ያመጣ ሥራ ነው:: እኛ ጋርም በተለያዩ መስኮች ሲደረግ ውጤቱ ምን እንደሚመስል ታይቷል:: አሁን በሁሉም የትምህርት መስኮች መደረጉ ደግሞ የትምህርት ጥራቱን ከማረጋገጥ አኳያ ብቸኛ ባይሆንም ትልቅ መፍትሄ የሚያጎናጽፍ ነው::

የመውጪያ ፈተናው እንደ አገር ሁለት አይነት ውድድሮችን እንድናጎላቸው ያደርገናል:: የመጀመሪያው ከአቻ ጋር የሚደረግ ውድድር ሲሆን፤ ተማሪዎች በሚመረቁበት ሙያ የሚያደርጉት ፍልሚያን ያሳየናል:: ዩኒቨርሲቲዎችም እንዲሁ:: ይህ ደግሞ ለተማሪውም ለአገርም የመሥራት አቅምን የሚጨምር ነው:: ሁለተኛው የመስፈርት ወይም ከስታንዳርድ ጋር የሚደረገው አይነት ሲሆን፤ ተማሪና ተቋማት ወይም ዩኒቨርሲቲዎች ለተሰጠው መስፈርት ብቁ መሆናቸውን የሚያረጋግጡበት ውድድር ነው:: እናም የመውጫ ፈተና በሁለቱም መልኩ የሚለካ በመሆኑ አገርን ከመጥቀም አኳያ የማይተካ ሚናን ይጫወታል ይላሉ::

የመውጪያ ፈተናው ይሰጣል ከተባለ ቆይቶ እንደነበር የሚያነሱት ዶክተር ዳምጠው፤ በኮቪድና መሰል ነገሮች ቆሞ እንጂ ውጤቱን አሁን ላይ እንመለከተው ነበር:: አሁንም ቢሆን ውጤታማ እንደሚያደርገን አምነን ልንሰራበት ይገባል:: የተለየ ነገር አድርጎ በአሉታዊ መመልከቱ ዋጋ ያስከፍላል እንጂ ብቃት ያለው ተማሪን እንድናፈራ አያደርገንም:: ስለሆነም ዩኒቨርሲቲዎች ያንን አስበው ሊንቀሳቀሱ እንደሚገባም አስረድተዋል::

ከመውጪያ ፈተናው በኋላ ጥራት ያለው ተማሪ ማፍራት የማይችሉ፣ ደረጃውን የጠበቀ ምርምር የማያካሂዱና የአካባቢውን ማህበረሰብ የማይጠቅሙ ዩኒቨርሲቲዎች ሊዘጉ እንደሚችሉ የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ ሲናገሩም ነበርና ዩኒቨርሲቲዎች ለዚህ የሚተጉበትን አማራጭ መቀየስ እንዳለባቸው የሚያሳስቡት ዶክተር ዳምጠው፤ እንደ አገር ብቁ ዜጋን ማፍራት እንዳይዘጋ ብሎ መሥራት አይደለም:: ግዴታና የዩኒቨርሲቲዎች ዋና ተልእኮ ነው:: ስለሆነም እንደእኛ ዩኒቨርሲቲ ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ ተግባሩ እየተከናወነ ቀጥሏል:: ዝግጅቶቻችንም ከሞላ ጎደል ጥሩ እየሄደ ነው:: እናም ሁሉም ዩኒቨርሲቲ ከተሰጠው ተልእኮ አንጻር እያየ መሥራት ይጠበቅበታል:: በተለይም በቂ ባለሙያን አፍርቶ ለአገር ጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ላይ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ እንደሚገባ አስገንዝበዋል::

እኛም ምክረ ሃሳቦቹ ጠቃሚ በመሆናቸው ተማሪዎቹም ሆኑ ዩኒቨርሲቲዎቹ ቢጠቀሙባቸው ጎልተው ሊወጡ ያስችሏቸዋል እያልን ለዛሬ ሃሳባችንን ቋጨን:: ሰላም!!

> **የመውጪያ ፈተናው ከምንም በላይ ለተማሪዎች የሚጠቅምበት ሁኔታ በራስ የመተማመን አቅም እንዲኖራቸው ማድረጉ ነው፡፡ ገና እየተማረ ባለበት ሁኔታ ለወደፊት ህይወቱ ቀድሞ እንዲዘጋጅ፤ ተወዳዳሪ እሆናለሁ የሚል ወኔ ውስጥ እንዲገባና በየትኛውም ደረጃና አካባቢ ቢመደብ ፈተና እንደማይጥለው እንዲያስብ ያደርገዋል**

# ‹‹የህዳሴ ግድቡ ገሃድ እየሆነ በመጣበት በዚህ ጊዜ ራሱ የኢትዮጵያውያን ተሟጋች መሆን ይጀምራል››

**- አቶ ክፍለዮሐንስ ጠመረ**
**የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያና የውሃ ተመራማሪ**

አስቴር ኤልያስ

**ከቀናት በፊት የኢትዮጵያውያን አይኖች በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል በጉባ ወረዳ ካለው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ላይ እንደነበሩ ይታወቃል፡፡ በአሁኑ ወቅት ግድብ ግንባታ ሥራ ወደ 83 ነጥብ 3 በመቶ መድረስ የቻለ ሲሆን፣ ሶስተኛው ዙር የውሃ ሙሊት መጠናቀቅን ተከትሎም ሁለተኛው ተርባይን ኃይል ማመንጨት መጀመሩ እውን ሆኗል፡፡ ይህን ጊዜ ሲናፍቁ የቆዩትም ኢትዮጵያውያኑ ከጉድለታቸው አንስተው ለህዳሴ ግድቡ እውንነት ያበረከቱት አስተዋጽዖ ፍሬ ማፍራቱን በአይናቸው በብረቱ ማየት ችለዋል፡፡ የልፋታቸውንም ዋጋ ያልዘነጋው ዓባይ የምስራቹን እነሆ ማለት ጀምሯል፡፡ በእርግጥ በዚህ በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ላይ ያልተነገሩ የሐሰት ትርክቶች አልነበሩም ማለት ይቻላል፡፡ ግድቡን አስመልክተው በጣም ብዙ መግለጫዎች ወጥተዋል፤ በሰፊውም ሲሰራጩ ቆይቷል። እንደ አስመታደል ሆኖ አብዛኛዎቹ መግለጫዎች፣ መረጃዎች ብሎም ሪፖርቶች የተደራሲውን አስተሳሰብ ለማዛባት ሆነ ተብለው የሚነገሩ እንደነበሩ የአደባባይ ምስጢር ሆኖ ሰንብቷል፡፡ በኢትዮጵያ በኩል በተቻለ ሁሉ ትክክለኛ መረጃዎች ብሎም አቋሞች እየተሰጡ በመምጣታቸው ዛሬ የህዳሴ ግድቡ እንደተባለለት የሐሰት ትርክት ሳይሆን ኢትዮጵያውያኑ እንደፈለጉት ብርሃን ሲፈነጥቅ ችሏል፡፡ ከዚሁ ከታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ሶስተኛው ዙር የውሃ ሙሊት በስኬት መጠናቀቅ እና ሁለተኛው ተርባይን ኃይል ማመንጨት መጀመር ጋር ተያይዞ በውሃ ላይ ጥናት ካደረጉትና የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያ ከሆኑት ከአቶ ክፍለዮሐንስ ጠመረ ጋር ቆይታ አድርገን እንደሚከተለው አጠናቅረነዋል። ምልካም ንባብ!**


ፎቶ - ሀዲስ አበርሃ

**አዲስ ዘመን፡- በውሃ ጉዳይ ጥናት ስማድረግ ያነሳሳዎት ምክንያት ምንድን ነው?**

**አቶ ክፍለዮሐንስ፡-** ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ከተቸረቻቸው ሀብቶች መካከል ውሃ ትልቁን ቦታ ይይዛል:: ባላት ልክም ለሌላው አገር ልግስናዋን ነፍጋ አታውቅም:: በኢትዮጵያ ወንዝ የተጠማ ሲጠጣ፤ አቅም ያለውም ሲያለማበት ቆይቷል:: ይሁንና ይህ ብዙ ጊዜ ጎልቶ ቦታ ሲሰጠው አይታይም:: ከወንዞቿ የተጎነጨ ብሎም የበለጸገ ምስጋና ሲያቀርብ አይስተዋልም:: ኢትዮጵያ የዓለም ውቅያኖሶች ቤተ መንግስት ናት ማለት ይቻላል:: እንዴት የሚባል ከሆነ ፓሲፊክም ፤ አትላንቲክም፤ ቀይ ባህርም ወቅቱን እየጠበቀ በሚነፍሰው ነፋስ ምክንያት በሚነሳው ማዕበል መዳረሻቸው እዚሁ በአገራችን በመሆኑ ነው:: ይህ በራሱ ስለውሃ ለማጥናት የሚያነሳሳ ጉዳይ ነው::

በሌላ በኩል አብዛኛው የዓለም ክፍል ኢትዮጵያን የውሃ ማማ እንደሚያደርጋት ይታወቃል፤ በእርግጥም ኢትዮጵያ የብዙ ወንዞች ባለቤት ስለመሆኗ አይካድም:: ከእነዚህ ወንዞች ብዙዎቹ የአባይ ገባር የሆኑ ናቸው:: አባይ እነዚህን ወንዞች ቀምቶን ወደ ጎረቤት አገር ሱዳን ብሎም ግብጽ ይዟቸው ሲገባ ኖሯል:: ኢትዮጵያ ስትቀማ የኖረችው ውሃዋን ብቻ ሳይሆን ለም አፈሯንም፣ ዛፍ ቅጠሏንም እንዲሁም ማዕድኗን ጭምር ነው:: ይህ ደግሞ ሲሆን የነበረው ለብዙ ምዕተ ዓመት እንጂ ለተወሰኑ ዓመታት ብቻ አለመሆኑ እሙን ነው::

ሁኔታዎች ባለመመቻቸታቸው ለዘመናት ይህን ሁሉ ሀብት አስረክበን ተቀምጠን ቆይተናል:: አንጡራ ሀብታችንን በአባይ ወንዝ አማካይነት ለሱዳንና ለግብጽ ስንሰጥ የቆየን ሕዝቦች ብንሆንም አባይ ወንዛችንን ‹ተው› ለማለት ብንመኝም ሳንተገብረው ቆይተናል:: ይሁንና ለእነዚህ በርካታ ዓመታት በተፈጥሮ ሀብታችን ሳንጠቀም ብንቆይም በተቃራኒው ለበርካታ አስርት ዓመታት ሲጠቀሙበት የነበሩ አገራት ለነጻ ለስጦታችን የሰጡን ምላሽ ምስጋና አልነበረም :: ምስጋና ሊቸሩን ሲገባ በምትኩ ግን ንቀት ከንቀትም አለፍ ሲል ደግሞ ሲያካሂዱብን የነበረው ትንቅንቅን ነው::

ስለዚህ እኔ ላጠና የተነሳሳሁበት አንዱ ምክንያት ጥያቄዬ ምላሽ እንዲያገኝ ከመፈለግ ነው:: ይኸውም ስለምን ውሃ እየሰጠን ውሃችንን በሚጠቀሙ አገሮች ሰላማችን ይቀማል የሚል ነው:: ሌላው ጥያቄዬ ለእናት አገሬ ኢትዮጵያ ያቀረብኩት ጥያቄ ሲሆን፣ ይኸውም ውሃ እየሰጠሽ ሰላምሽን የምታስቀሚው ለምንድን ነው የሚል ነው:: በተጨማሪም ሌላውን ጥያቄዬ የሰነዘርኩት ለራሱ ለዓባይ ወንዝ ሲሆን ፣ ይህም በራሱ በአባይ ወንዝ ላይ 86 በመቶ ያህል ድርሻ ያላት አገሬ ( እንደ እኔ ግንዛቤ ኢትዮጵያ በአባይ ላይ ያላት ድርሻ ከ86 በመቶ በላይ ነው ) አንተን የሚያክል ኃያል ጉልበት ያለው ታላቅ ወንዝ አላትና ጉልበትህ ከምን ብዬዋለሁ::

ለዚህም ጥያቄዬ በተለይ ከዓባይ ወንዝ ያገኘሁት ምላሽ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግስት ይዘዘኝ እንጂ ኢትዮጵያን ጠላቷ ከሆነው ድህነትም ሆነ ከሚያደባባት ሴረኛ ሊከላከላት አቅም እንዳለው ነው እንዳስተውል ያደረገኝ:: በእርግጥም በጥናቴ ያገኘሁት ነገር ቢኖር ወንዝ ከጠላት መከላከል እንደሚችል ነው:: ደግሞም የአባይን ወንዝ ወደጠንካራ መከላከያነት መቀየር እንደሚቻል በማስተዋል ላይም እንገኛለን::

በተለይ ለትምህርት ጀርመን አገር በሄድኩበት ጊዜ እማር የነበረው ከተለያየ ከአፍሪካ አህጉርም ሆነ ከሌሎች አህጉሮች ከመጡ ተማሪዎች ጋር ነበር፤ በወቅቱ በጀርመን ለአምስት ዓመት ያህል በትምህርት ላይ ነበርኩ:: በትምህርት ላይ ሳለን በአስተማሪዎቻችን እንባል የነበረው ሁሉም ተማሪ በአገሩ ጉዳይ ላይ ምርምር ይስራ የሚል ነበር፤ ለዚህም ድጋፍ ይደረግ ነበር:: እኔም እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ተማሪ ምርምር ለማድረግ ያሰብኩት በኢትዮጵያ የውስጥ ጸጋና ስጋት ላይ ነበር::

**አዲስ ዘመን፡- ዓባይ ኢትዮጵያን ከጥቃት የመጠበቅ አቅም አለው ብለዋል፤ ይህ ምን ማለት ነው?**

**አቶ ክፍለዮሐንስ፡-** ኢትዮጵያን ከጥቃት ለመጠበቅ ሁለት ኃይል አለ:: አንደኛው የኢትዮጵያ መንግስት ሲሆን፣ እኔ ደግሞ በኢትዮጵያ መንግስት ሙሉ እምነት አለኝ:: ምክንያቱም አቅም ያለው መንግስት ስለሆነ ነው:: ሌላው ኃይል ደግሞ እንዳልኩሽ የዓባይ ወንዝ ራሱ ነው:: ምክንያቱም እኛ ኢትዮጵያውያን መርሳት የሌለብን ነገር ለአባይ ወንዝ የምናደርገው አበርክቶ ከፍተኛው እጅ እንደመሆኑ በተሰጠን የተፈጥሮ ጸጋ የመልማት መብታችንም ምሉዕ መሆኑን ነው:: እኛ በርትተን በዓባይ ወንዝ ላይ በምናደርገው የልማት ተጋድልዎ እና በምንከፍለው መስዋዕትነት የምናተርፈው በዓባይ ወንዝ ላይ የተገደበው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የሚያመነጨውን የኤሌክትሪክ ኃይል ብቻ ሳይሆን ከዚሁ ጋር ተያይዘው የሚመጡ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያላቸውን ምቹ ሁኔታዎችን ጭምር ነው:: የገቢ ምንጫችን ከፍ ሲል ከሚሰነዘርብን ንቀትም ሆነ ጥቃት እንጠበቃለን:: ዓባይ ደግሞ በዚህ ጉዳይ ከኢኮኖሚያዊው ጠቀሜታው በተጨማሪ ካላስፈላጊ ንትርክና አተካራ ይታደገናል የሚል እምነት አለኝ::

በተለይ በህዳሴው ግድብ ምክንያት በተለያየ አካላት ሲሰነዘርብን የቆየውን ክስ ማርገብ ይችላል:: የህዳሴ ግድቡ ገሃድ እየሆነ በመጣበት በዚህ ጊዜ ራሱ የኢትዮጵያውያን ተሟጋች መሆን ይጀምራል:: ስለዚህም ኢትዮጵያ ምንም እንኳ ከየትኛውም አገር ጋር ያላት ዲፕማሎሲያዊ አካሄድ ሰላም እንዲሆን ፍላጎቷ ቢሆንም ከዚህ አልፎ ሊተነኩሳት የሚችል አካል የሚኖር ከሆነ ዓባይ የተሳተፈበት መከላከል ማድረግ ትችልበታለች:: ይህ በእርግጥ የራሱ የሆነ ቴክኒክ እና አካሄድ ስላለው ለሚመለከተው እተወዋለሁ:: ከዚህ ውጭ ግን ውሃን ለልማት ብሎም ለአገር ኢኮኖሚ እድገት ማዋሉ የኢትዮጵያ መንግስት የአሁን ብቻ ፍላጎት ሳይሆን ቀደም ሲልም እያከናወነው ያለው ድርጊትም ጭምር ነው::

**አዲስ ዘመን፡-ሰሞኑን ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሁለተኛው ተርባይን ማመንጨት ጀምሯል፤ ኢትዮጵያ ይህን ድል መጎናጸፍ የቻለችው በቀላሉ እንዳልሆነ ይታወቃልና እዚህ ላይ ምን አስተያየት አለዎት?**

**አቶ ክፍለዮሐንስ፡-** ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ላይ ግድብ ለመስራት የሚያስችላትን መሰረት ከጣለች በኋላ በተለያዩ አካላት ይደርስባት የነበረው ተጽዕኖ በቀላሉ ተገልጾ የሚታለፍ አይደለም:: አንድ አገር ሊደርስባት ከሚችለው ተጽዕኖ በላይ ነው ቢባል የተጋነነ ነገር አይኖረውም:: ኢትዮጵያ በተፈጥሮ የተቸረችውን ውሃ እንዴም ቢሆን ብቻዬን ልጠጣ እንዲሁም ልጠቀምበት ብላ አታውቅም ፤ በዓባይ ወንዝ ላይም ግድብ ለመገደብ ስትነሳ ልክ ሌላው አገር እንደሚያደርገው ሁሉ የዓለም አቀፍ ህግጋትን ተከትላ በጨለማ ለሚሰቃየው ህዝቧ ብርሃን ለመሆን ነው:: ይህን ስታደርግ ውሃ የጠማውን ሌላኛውን አገር አላጠጣም በሚል ማንአለብኝነት አይደለም:: ልማቷን ለማፋጠን ስትነሳ የተጠማ ይጠጣ፤ መልማት የሚፈልግም ይልማ በሚል መርህ ነው:: ይሁንና ውሃ እንዲጠጡ ይሁንታዋን ከሰጠቻቸው

# ወቅታዊ



**የአገራችን ፍላጎቷ በጨለማ ያለውን ጥቂት የማይባል ኢትዮጵያውያንን ከዚህ ግድብ የብርሃን ፍንጣቂ እንዲያገኙ ማድረግ ነው:: እኛ ውሃውንም ብርሃኑንም ለጎረቤቶቻችን መስጠታችን ይቀጥላል:: ኢትዮጵያውያን ግን እንደዚህ ቀደሙ በድህነትና በጨለማ ሲኖሩ አይፈልጉም፤ እንደደኸዩም አይቀሩም:: ኢትዮጵያ በተዘዋዋሪ የሚደረግባትን የተለያየ አይነት ሴራም ከዚህ በኋላ የሚሸከም ትከሻ አይኖራትም**

አገራት የጠበቃት ምላሽ ግን ምስጋና ያለመሆኑ እውን ነው::

ይደረግ ከነበረው አንዱ ለታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ የሚሆን ምንም አይነት ብድር ማንም አገራችንን እንዳያበድራት ማድረግ ነው:: እንዲያም ሆኖ ዜጎቿ ይህን አይነት መሸነፍ በጅ የማይሉ በመሆናቸው ካላቸው ሳይሆን ከጉድለታቸው ሰጥተው የተቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል፤ በማድረግ ላይም ይገኛሉ:: በተመሳሳይ ምንም እንኳ ውጤታማ መሆን ባይቻላቸውም ባገኙት ትልልቅ መድረኮች ላይ ሁሉ ከህዳሴ ግድቡ ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ ላይ ማዕቀብ እንዲጣል በብዙ ደክመዋል:: ይህ ደግሞ መሬት ላይ ካለው እውነታ ጋር የሚጋጭ በመሆኑ ስኬታማ ሊያደርጋቸው አልቻለም:: ምክንያቱም በዓባይ ወንዝ ላይ ለዘመናት ሲነገር የነበረው ከእውነት የራቀ ትርክት እውነት ሆኖ መቀጠል አልቻለም፤ የሐሰት ትርክቱ እውነት ሆኖ እንዳይቀጥል ደግሞ ጉምቱ ኢትዮጵያውያን ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ እውነቱን ከሐሰት መለየት የሚያስችለውን መረጃ ይፋ እያደረጉ በመምጣታቸው ጭምር ነው::

ለአብነት ያህል አንድ ማሳያ ብቻ ማስቀመጥ ቢቻል፤ ኢትዮጵያ እየገነባች ያለችው የህዳሴ ግድብ ውስጥ የመጀመሪያው ዙር አራት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ውሃ ልትሞላ በተዘጋጀችበት ወቅት ሌሎች የተፋሰሱ አገራት ጠብታ ውሃ ማግኘት እንደማይችሉ በምሁራኑ ጭምር ሲነገር ነበር:: ይሁንና ወትሮ ከነበረው የውሃ ፍሰት የመጣ ለውጥ አልነበረም:: ባለፈው ጊዜም ሁለተኛውም ዙር የህዳሴ ግድብ ውሃ ሙሊት ከመከናወኑ አስቀድሞ ሱዳን እና ግብጽ ኢትዮጵያ ቀጣዩን ዙር የግድቡን ውሃ ሙሌት ከማከናወኗ በፊት በሦስቱ አገራት መካከል ከስምምነት መደረስ አለበት ማለታቸው ይታወሳል። ነገር ግን ኢትዮጵያ መርህን ተከትላ የምትሰራ አገር እንደመሆኗ የማንንም መብት ሳትነካ ሁለተኛውንም ዙር የውሃ ሙሊት በስኬት ማጠናቀቋ ይታወቃል ፤ ሁለተኛውን ዙር በመሙላቷ በሱዳንም ሆነ በግብጽ ላይ የደረሰ ተጽዕኖ የለም:: ይልቁንም ውሃው ለሱዳንም ሆነ ለግብጽ እንኳን ሊያንሳቸው ቀርቶ ሞልቶ የተትረፈረፈበት ወቅት ነበር ማለት ይቻላል:: የሕዳሴ ግድብ መሞላት ለውሃ ጥም የሚጥላቸው መሆኑን ስጋታቸው እንደሆነ በየመድረኩ ሲነገር ቢሰነብትም የዓባይ ወንዝ ከመንፎልፎል የከለከለው አልነበረም:: ከዚህ ቀደም የሚያከናውኑት የልማት ስራም ቢሆን አንዳች አልተስተጓጎለም::

ኢትዮጵያ ልጆቿን ይዛ ጀምሬ መንገድ ላይ አልተወውም ብላ ወደማጠናቀቁ እየሄደች ካለው የህዳሴ ግድብ ብርሃን ማየት ጀምራለች :: ሶስተኛውን ዙር የውሃ ሙሊትም በስኬት አጠናቃ ከሁለተኛው ተርባይን ደግሞ ኃይል ማመንጨት ቀጥላለች። ይህን ስታደርግ ግን ጥቅሙ ለራሴ ብቻ ነው የሚል እሳቤ የላትም:: ከጎረቤት አገር ጋር በልማትም ሆነ በሰላሙ በኩል ያላት ትብብር የሚቆም አይደለም:: የኢትዮጵያ ጥንካሬ እና ትጋት ጎረቤቶቿንም ጭምር ተጠቃሚ የሚያደርግ እንጂ የሚያገል አይደለም:: የእኛ የኢትዮጵያውያን ፍላጎት ውሃው ለሁላችን የሚበቃ በመሆኑ ተጠቃሚነታችንም የጋራ እንዲሆን ማድረግ ነው::

ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ኃይል እንዲያመነጭ የተያዘው ውሃ ተርባይኑን መትቶ የሚያልፍ በመሆኑ የተፋሰሱን አገራት የሚጎዳ አይደለም:: ይልቁኑም ኢትዮጵያ እያለች ያለችው ብርሃን እየሆነ ያለ ግድብ በመሆኑ ከዚህ ብርሃን መቋደስ የሚፈልግ ካለ በሩ ክፍት ነው የሚል ነው:: አገራችን ፍላጎቷ በጨለማ ያለውን ጥቂት የማይባል ኢትዮጵያውያንን ከዚህ ግድብ የብርሃን ፍንጣቂ እንዲያገኙ ማድረግ ነው:: እኛ ውሃውንም ብርሃኑንም ለጎረቤቶቻችን መስጠታችን ይቀጥላል:: ኢትዮጵያውያን ግን እንደዚህ ቀደሙ በድህነትና በጨለማ ሊኖሩ አይፈልጉም፤ እንደደኸዩም አይቀሩም:: ኢትዮጵያ በተዘዋዋሪ የሚደረግባትን የተለያየ አይነት ሴራም ከዚህ በኋላ የሚሸከም ትከሻ አይኖራትም::

**አዲስ ዘመን፡- የህዳሴ ግድብ እውን እየሆነ በመጣ ጊዜ ግድቡ እንዳይጠናቀቅ በተለያዩ አካላት የተለያዩ ክሶች ሲሰነዘሩ ቆይተዋል፤ ከዚህም አልፎ ማዕቀብም እንዲጣል ብርቱ ጥረት ተደርጓልና የክሳሾቹ ድካም ውጤት እንዴት ገመገሙት ?**

**አቶ ክፍለዮሐንስ** ፡- በሚያስገርም ሁኔታ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንደ ዓባይ ወንዝ የተጠና ወንዝ ያለ አይመስለኝም:: በዓለም አቀፍ ደረጃ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ግድቦች አሉ፤ የህዳሴን ግድብ ያህል ያነጋገረ ግድብ አለ ማለት አያስደፍረኝም:: የቱንም ያህል ጥናትና ምርምር ቢካሄድበት፤ የቱንም ያህል ስኬታማ እንዳይሆን የሐሰት ትርክት እየተነገረ እንዳይገነባ ቢደረግ እና የተለያዩ ክሶችና ማዳከሞች ቢካሄድበትም ስጋት የወለደው ጩኸት ሆኖ ቀረ እንጂ በህዳሴ ግድባችን አለመሳካት ያመጣው ውጤት የለም፤ አይኖርምም:: ይህ በመሆኑም የትኛውም አካል የተቻለውን ያህል ቢለፋ ቢደክም ኢትዮጵያን ከልማት ጉዞዋ ሊያስተጓጉላት አልቻለም፤ አይችልምም ::

በእርግጥ በተቃራኒው ከቆሙ አካላት ሲነገር የነበረው የሐሰት ትርክት እውነታው እስኪታወቅ ድረስ ፈተናዎች ጠንክረው እንዲቆዩ አድርጎ መሰንበቱ ይታወቃል:: ከዛም የተነሳ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድባችንን 24 ሰዓት ለማስጠበቅ ተገደናል:: በእኔ እምነት ይህ መሆን አልነበረበትም:: በዓባይ ወንዝ ላይ ግድብ ገድበን ብርሃን ማግኘትም፤ ልማታችንን ማፋጠንም ስለምንችል የምናደርገውን ስራ በነጻነት ማድረግ እንችል ነበር የሚል አተያይ አለኝ:: በተቃራኒው ከቆመው አካል እየተስተዋለ ያለው ነገር ግን የሰላምን መንገድ መምረጥና መከተል የአንድ ወገን ጥቅም ብቻ አለመሆኑን ያለመረዳት ነውና በኢትዮጵያ በኩል ግድቡን መጠበቁ ግድ ብሏል::

**አዲስ ዘመን፡- ግድቡ ለሱዳንም ሆነ ለግብጽ እንዲሁም ለተፋሰሱ አገራት ስጋት አለመሆኑ ተደጋግሞ የተነገረ ጉዳይ ነው፤ ስለሆነም የኢትዮጵያ መልማት በሌሎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እስካላደረሰ ድረስ ከስጋት ነጻ ይሆኑ ዘንድ ምን አይነት መልዕክት ያስተላልፋሉ?**

**አቶ ክፍለዮሐንስ፡-** ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ዛሬም ድረስ በአገራችን የኤሌክትሪክ ብርሃን ላላገኙ የኅብረተሰብ ክፍል ብርሃን እንዲያገኙ ማድረግ ነው:: ከግብፅ እና ከሱዳን በኩል ሲደመጥ የቆየው ግን ከእነርሱ እውቅና እና ፍላጎት ውጪ ኢትዮጵያ በሀብቷ የመጠቀም መብት እንደሌላት ነው:: ይህ ሀሳብ ደግሞ ኢትዮጵያን በራሷ ሀብት የመጠቀም መብትን የሚሽር ነው:: በዚህ አይነቱ አካሄድ ውስጥ በመሆን ምላሽ ለሚሻው ምላሽ እየተሰጠና ትኩረት ለሚያስፈልገውም ጉዳዮቹን በአንክሮ ለማየት እየተጣረ ዛሬ ላይ መድረስ ተችሏል::

ግድቡ እውን ከመሆን አልፎ ብርሃን እንድናይ ያደረገ በመሆኑ ከዚህ በኋላም ኢትዮጵያ በመጣችበት ትክክለኛ ፖሊሲዋ ትቀጥላለች:: በዚህ ውስጥ ሁሉ ደግሞ አገራችን የማንም ስጋት እንዳልሆነች ሁሉ በቀጣይም የማንም ስጋት ሳትሆን የምትቀጥል በመሆኑ እንቅስቃሴዋ የማንንም ሰላም አይነሳም:: ይልቁኑ በስጋት ለሚመለከታቸው አካል ግድቡ ተስፋም ጠቃሚም መሆኑን ቢረዱ መልካም ነው::

እኛ የዓለም አቀፉን ሕግጋት እንደምናከብረው ሁሉ ሌሎቹም ይህንኑ ያከብሩ ባይ ነኝ:: ከዚህ በኋላም ቢሆን በከሰሱን ቁጥር ሄዶ መከራከሩ አሰልቺ ከመሆኑም በተጨማሪ ጊዜያችንን በከንቱ እንዳይጠፉ ቢያደርጉ መልካም ነው የሚል አመለካከት አለኝ:: እንዲያውም በተከሰስን ቁጥር ቀርበን ምላሽ በሰጠንበት ወቅት ያወጣነው ወጪም ሆነ ጊዜም ቢጠና እንዲሁም በጉዳዩ ላይ የተሳተፈው ምሁሩም ሆነ ዲፕሎማቱ ያስቀመጠው ሐሳብ ቢጠና መልካም ነው የሚል እምነት አለኝ:: ይህ በራሱ አንድ ትልቅ ታሪክ ነውና::

**አዲስ ዘመን፡- ስቃስ ምልልሱ ፈቃደኛ ሆነው ቢሮአችን ድረስ ስለመጡልን ከልብ እናመሰግናለን::**

**አቶ ክፍለዮሐንስ፡-** እኔም አዲስ ዘመን ለሰጠኝ እድል አመሰግናለሁ::

# ዓለም አቀፍ

## በኬንያ ምርጫ ሁለት ተፎካካሪዎች በተቀራራቢ ውጤት እየመሩ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር




ራይላ ኦዲንጋ እና ዊሊያም ሩቶ

አዲስ አበባ፡- በኬንያ በተካሄደው ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ከተገኘው ውጤት ከአንድ ሦስተኛ በላይ የሚሆነው በምርጫ ኮሚሽኑ የተረጋገጠ ሲሆን ሁለቱ ተፎካካሪ እጩዎች በቅርብ ርቀት በመፎካከር ላይ ናቸው።

እስካሁን በተረጋገጠው ድምጽ ምክትል ፕሬዚዳንት ዊሊያም ሩቶ 51 በመቶ ሲመሩ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ራይላ ኦዲንጋ 48 በመቶ ድምጽ አግኝተዋል። የምርጫ ኮሚሽኑ ኃላፊ ማክሰኞ የተካሄደውን ምርጫ ውጤት ይፋ ማድረግ በጣም አዝጋሚ መሆኑን አምነዋል።

በሁለቱ ዋና ዋና እጩዎች ደጋፊዎች ቅሬታ ማቅረባቸውን ተከትሎ ውጤቱን የማረጋገጥ ሥራ በተደጋጋሚ ተቋርጧል። የራይላ ደጋፊዎች ውጤቱን የማጣራት ሂደቱን በተደጋጋሚ በማስተጓጎላቸው ታውቋል። አንዳንድ የምርጫ አስፈፃሚዎችን ድምጽ እያጭበረበሩ ነው በማለት ከሰዋል።

በውዝግቡ መካከል የራይላ የምርጫ ዘመቻ ሥራ አስኪያጅ የምርጫ ኮሚሽኑ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ወደሚጠቀሙበት በማቅናት ውጤቱን የማጣራት ሂደቱን ተችተዋል።

"የኬንያው ቦማስ የወንጀል ማዕከል መሆኑን ለሕዝብ ማሳወቅ እፈልጋለሁ" ሲሉ ዋና ሥራ አስኪያጁ ሳይታባኦ ኦሌ ካንቾሪ ተናግረዋል።

በኋላም ድምድ ማጉያው ተቋርጦ ከስፍራው እንዲርቁ ተደርጓል። ቦማስ በናይሮቢ የሚገኝ የባህል ማዕከል መጠሪያ ሲሆን እንደ ዋና የድምጽ መቁጠሪያ ማዕከል በመሆን ያገለግላል።

በስፍራው ጸጥታውን ለማስከበር የአድማ በታኝ ፖሊሶች በህንጻው ተሰማርተዋል። ከ292 የምርጫ ክልሎች የ141 ውጤት ተረጋግጧል።

የመገናኛ ብዙሃን ድርጅቶች ከ46 ሺህ የምርጫ ጣቢያዎች ይፋዊ መረጃን በመጠቀም ጊዜያዊ ውጤቶችን እየለቀቁ ነበር። በሁለቱ

እጩዎች መካከል ከፍተኛ የውጤት መቀራረብ መኖሩን አሳይተዋል።

ወደ 14 ሚሊዮን ድምጽ የሰጡ ሲሆን ይህም ከተመዘገቡት መካከል 65 በመቶ ያህሉ ነው። የምርጫ ኮሚሽኑ እስከ ማክሰኞ ድረስ ውጤት ማሳወቅ ይጠበቅበታል።

ውጤቱን ለማሳወቅ "አንዳንድ ማሻሻያዎችን ማድረግ ተጠብቆብናል" ሲሉ የኮሚሽኑ ኃላፊ ዋፉላ ቼቡካቲ ተናግረዋል። ይህም አሠራራቸውን ለማፍጠን እንደሚረዳቸውን አስታውቀዋል። ተጨማሪ የፖሊስ ኃይል በአካባቢው ተሰማርቷል።

ከምርጫ ጣቢያዎች የተሰበሰበው እና በኮሚሽኑ ድረ ገጽ የተለጠፈው ጊዜያዊ ውጤትን በመጠቀም መገናኛ ብዙሃን የሰሯቸው የውጤት መግለጫዎች መለያየት ግርታን ፈጥሯል። ድረ ገጹ በመረጃ በርባሪዎች ተሰብሮ ውጤት ተቀይሯል መባሉን የኮሚሽኑ ባለሥልጣናት አስተባብለዋል።

ከዚህ ቀደም ከምርጫ ጋር ተያይዞ የተነሳ አለመረጋጋት በመኖሩ በሕብረተሰቡ ዘንድ ስጋት ተፈጥሯል። እአአ በ2007 የተካሄደው ምርጫ ተሰርቋል በሚል በተነሳ አለመረጋጋት አንድ ሺህ 200 ያህል ሰዎች ሲገደሉ 600 ሺህ ያህሉ ደግሞ ከመኖሪያ ቤታቸው ተፈናቅለዋል።

በ2017 የተካሄደውን ምርጫ ተከትሎ ከፍተኛ የሎጂስቲክ ክፍተት ነበር በሚል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ምርጫው በድጋሚ እንዲካሄድ ውሳኔ አስተላልፏል። የአሁኑ ምርጫ ስኬታማ እንዲሆን ባለሥልጣናት ጫና ውስጥ ገብተዋል።

በመላ ሀገሪቱ እንስቃሴዎች ቀዝቀዝ ያሉ ሲሆን ትምህርት ቤቶችም ተዘግተዋል። በኬንያ የምርጫ ማጭበርበር ስሞታ ለዘመናት የነበር ጉዳይ ነው።

በዘንድሮው ምርጫ ለሦስተኛ ጊዜ ቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ እንዲውል ቢደረግም ተቀናቃኞችን ፍርድ ቤት ደጅ ከመጥናት እንዳላቆመ ቢቢሲ ዘግቧል።




## ፕሬዚዳንት ዘለንስኪ በዩክሬን ኒውክሌር ጣቢያ የሚገኙ የሩሲያ ወታደሮችን አስጠነቀቁ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የዩክሬን ፕሬዚዳንት በሩሲያ ይዞታ በሚገኘው የዛፖሪዝህዚያ የኒውክሌር ጣቢያ ላይ የሚተኩሱ የሩስያ ወታደሮች በጸጥታ አካላት ጥቃት እንደሚደርስባቸው አስጠነቀቁ።

ፕሬዚዳንት ቮሎድሚር ዘለንስኪ በትናንትና ምሽት ንግግራቸው በኒውክሌር ጣቢያው ላይ ሆኖ ወይም ወደ ጣቢያው የሚተኩስ የዩክሬን "ልዩ ኢላማ" ይሆናሉ ብለዋል።

በተጨማሪም ሩሲያ የኒውክሌር ጣቢያውን ወደ ጦር ሰፈር በመቀየር "ለኒውክሌር ማስፈራሪያነት" እየተጠቀመች ነው ሲሉም ከሰዋል። ሩሲያ በመጋቢት ወር ከፍተኛ ፍልሚያ አድርጋ ጣቢያውን መቆጣጠሯ ይታወሳል።

ጣቢያው በአውሮፓ ውስጥ ትልቁ የኒውክሌር ኃይል ማመንጫ ሲሆን በደቡባዊ ዩክሬን ኒኮፖል ከተማ ውስጥ ስትራቴጂካዊ የሚባል ቦታ ላይ ይገኛል ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው። ጣቢያው በሩሲያ ይዞታ ስር ቢሆንም የዩክሬን ቴክኒሻኖች አሁንም በስራ ላይ ናቸው።

በጣቢያው ላይ የሚገኙት በርካታ የዩክሬን ሰራተኞች በታጠቁ ጥበቃዎች እየተጠበቁና በፈታኝ ሁኔታ መሆናቸውን ቢቢሲ ባሳለፍነው ሳምንት መጀመሪያ ላይ በሰራው የምርመራ ዘገባ አጋልጧል። በዚህ ሳምንት ሐሙስ የቡድን ሰባት አገራት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ሩሲያ ጣቢያውን ለቃ እንድትወጣ ጠይቀዋል።

እንደ ዘገባው ጣቢያው በከባድ መሳሪያ የተደበደበ ሲሆን ለጥቃቱም ሩሲያ እና ዩክሬንም እርስ በርስ ተወነጃጅለውበታል። ፕሬዚዳንት ዘሌንስኪ ከመዲናዋ ኪዬቭ ባደረጉት ንግግር ሩሲያ በኒውክሌር ጣቢያው ላይ በመተኮስ "የማያቋርጥ ትንኮሳዎችን" እንዳደረገች ገልጸው በዚያ የሰፈሩት የሩሲያ ወታደሮች ኒኮፖልን እና በአቅራቢያው የምትገኘውን ማርጋኔት ከተማን ለማጥቃት እንደ ጦር ሰፈር እየተጠቀሙበት ነው ብለዋል።

ፕሬዚዳንቱ "እያንዳንዱ የሩስያ ወታደር በጣቢያው የተኮሰ፤ ጣቢያውን ሽፋን አድርጎ የተኮሰ በጸጥታ ኃይሎቻችን፣ በደህንነታችን እንዲሁም በሠራዊታችን ልዩ ኢላማ እንደሚሆን መረዳት አለበት " ብለዋል።

አክለውም "ሩሲያ የኒውክሌር ጣቢያን ተቆጣጥራ መቀጠሏን በአውሮፓ ላይ የጨረር (ራዲዬሽን) ስጋትን ይጨምራል" በማለት አጽንኦት ሰጥተዋል።

# ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም

## ውድመት የደረሰባቸው ትምህርት ቤቶችን ግንባታ

ሕወሓት ባደረሰው ኪሳራ ውድመት ከደረሰባቸው ትምህርት ቤቶች መካከል በአፋር እና በአማራ ክልል ይገኛሉ፡፡ጉዳት የደረሰባቸውን ትምህርት ቤት ለመገንባትም በአፋር ክልል የዳርሳጊታ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን፤በአማራ ክልል ደግሞ የደሴ ሆጤ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግንባታ ለማስጀመር የመሠረት ድንጋይ መቀመጡ አይረሳም፡፡

ባሳለፍነው ሳምንትም በሁለቱም ክልሎች ላይ ተመሳሳይ ሥራ መሠራት ተችሏል፡፡ የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ በሰሜን ወሎ ዞን በመርሳ ከተማ ለሚገነባ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመሰረተ ድንጋይ ባስቀመጡበት ወቅት እንዳሉት፤ አሸባሪው ሕወሓት ህዝባዊና ሀገራዊ ጥላቻውን ከሚገልጽባቸው ተቋማት ዋናዎቹ ትምህርት ቤቶች ናቸው። ቡድኑ ለሀገር ተስፋ የሆነውን ወጣት ህልም ለማምከን አልሞ በመንቀሳቀስ በወራራ በገባባቸው አካባቢዎች አንድ ሺህ ሦስት መቶ ትምህርት ቤቶች ላይ ውድመት አድርሷል።



ግንባታውን ለማስጀመር የመሠረት ድንጋይ ሲቀመጥ

አካባቢዎቹ ከአሸባሪው ነጻ ሲወጡ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ገበታ ለመመለስ የትምህርት ቤቶች መውደም ችግር ፈጥሮ መቆየቱን ያወሱት ሚኒስትሩ ፤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ትምህርት ቤቶችን በፊት ከነበሩበት በተሻለ ለመገንባት ከአጋር አካላት፣ ባለሃብቶችና ከኅብረተሰቡ ጋር በመተባበር ጥረት እያደረገ እንደሚገኝም ይገልጻሉ።

ትምህርት ቤቶችን ለመማሪያ ብቻ ሳይሆን ለማኅበረሰቡም ሳቢና ማራኪ አድርጎ መገንባት ይጠበቃል ያሉት ፕሮፌሰር ብርሃኑ ፤ በአሸባሪው የወደሙ ትምህርት ቤቶች ደረጃቸውን በጠበቀ መልኩ በተሻለ እንደሚገነቡ አስታውቀዋል። በሰሜን ወሎ ዞን መርሳ ከተማ የሚገኘውን የመልካ ጨፌ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሰዎች ለሰዎች ከተባለ ግብረ ሰናይ ድርጅት ጋር በመተባበር መልሶ ለመገንባት የመሰረተ ድንጋይ መቀመጡም ተመላክቷል።

በተመሳሳይ በአፋር ክልል የጭፍራ አጠቃላይ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግንባታ በ60ሺ ካሬሜትር ላይ የሚያርፍ ሲሆን፤ አጠቃላይ የገንዘብ ወጪው ሜንሺን ፎር ሜንሺን በተባለ ግብረሰናይ ድርጅት የሚሸፈን ይሆናል፡፡ሥራውም ከዘጠኝ ወራት ባነሰ ጊዜ ተጠናቆ ወደ አገልግሎት የሚገባ እና በቀጣይም በተመሳሳይ በጦርነቱ የወደሙ የትምህርት ተቋማት ግንባታ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም ፕሮፌሰሩ አንስተዋል ፡፡

የትምህርት ጥራትን ለማሻሻልና የተቋማቱን ደረጃ የማሳደግ ሥራ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በትኩረት እየሠራ መሆኑንም የጠቆሙት ፕሮፌሰር ብርሃኑ፤ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በክልሎች ትምህርት ቤቶችን የሚገነባውን ሰዎች ለሰዎች ግብረ ሰናይ ድርጅትም አመስግነዋል።

ሚኒስትሩ በጭፍራ ወረዳ የወደሙ ትምህርት ቤቶችን ለማስገንባት የመሰረት ድንጋይ ካስቀመጡም በኋላ በሰመራ የክልሉ ትምህርት ቢሮ የጎበኙ ሲሆን፤ በጉብኝታቸው ቢሮው ምቹ የሥራ ሁኔታ ለመፍጠር የሠራቸውን ሥራዎች እና አጠቃላይ በመማር ማስተማር ስራዎች ላይ ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በተጨማሪም ሚኒስትሩ እየተካሄደ የሚገኘውን የ2014 ዓ.ም የስምንተኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና የእርማት ሂደት ጎብኝተዋል።

የአፋር ክልል ትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ አሊ መሀመ ቢሮው ከማሻሻያው በኋላ የተገበራቸውን ዋና ዋና የለውጥ ሂደቶች ማብራራታቸውን ከክልሉ ኮሙኒኬሽን ያገኘነው መረጃ ያመላክታል፡፡ በተለይም ጥሩ የሥራ ከባቢን መፍጠርና የመማር ማስተማር ሥራው የተሳለጠ እንዲሆን ምቹ መደላድል መፈጠሩን ጠቁመው፤ የትምህርት ሚኒስቴርም የክልሉን የመማር ማስተማር ሂደት በተሻለ መልኩ ለማከናወን ድጋፉን አጠናክሮ እንዲቀጥል ጠይቀዋል።

የሰሜን ወሎ ዞን አስተዳዳሪ ጋሻው አስማሜ በበኩላቸው ፤አሸባሪው ሕወሓት የሰሜን ወሎ ዞን የሚገኙ ሰባት መቶ 77 ትምህርት ቤቶች ላይ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ውድመት ማድረሱን ገልጸዋል፡፡

የአፋር ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ኤለማ አቡበከር በክልሉ በጭፍራ ወረዳ በጦርነት የወደሙ ትምህርት ተቋማትን መልሶ ለመገንባት ከፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ ጋር የመሰረተ ድንጋይ ባስቀመጡበት ወቅት እንዳሉት፤ ኢትዮጵያውያን የሚገጥሙንን ፈተናዎች በወንድማማችነት መንፈስ ለመፍታት እየተረዳዳንና እየተጋገዝን ከሄድን ወደ ስኬት በቀላሉ መድረስ እንችላለን፡፡

አሸባሪው ሕወሓት በሀገር ላይ የደቀነውን አደጋ በመቀልበስ ሁሉም ኢትዮጵያውያን በጋራ ተረባርበው አክሽፈዋል ያሉት ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ፤ ይሁን እንጂ በክልሉ ከ21 በላይ በሆኑ ወረዳዎች ጦርነቱ ትቶ ያለፈው ሰብአዊ፣ ሰነ ልቦናዊና ኢኮኖሚያዊ ውድመት በቀላሉ የሚገመት እንዳልሆነ ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም ኢትዮጵያውያን የሀገራቸውን ህልውና ለማረጋገጥ ያሳዩት ወንድማዊ ትብብርና አጋርነት በጦርነቱ የወደሙ ተቋማትን መልሶ መገንባት ላይ በመድገም በሀገራዊ ብልጽግና ማሳካት እንደሚገባም አስገንዝበዋል፡፡ በትምህርት ሚኒስቴርና አጋሮቹ በክልሉ የወደሙ ትምህርት ተቋማትን መልሶ ለመገንባት የሚደረገው ጥረት የዚሁ ወንድማዊ አጋርነት መገለጫ ነው፤ ይህ የትብብር መንፈስ በሁሉን የልማት መስክ መድገም ይገባልም በማለት ይገልጻሉ፡፡

የሜንሽን ፎር ሜንሽን ፋውንዴሽን የኢትዮጵያ ተወካይ አቶ ይልማ ታየ የትምህርት ቤቱ ግንባታ ትምህርት ሚኒስቴር ባወጣው ስታንዳርድ መሠረት የሚገነባ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሒታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ስፖርት
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ዋልያዎቹ ለቻን የመጨረሻ ማጣሪያ በአዳማ እየተዘጋጁ ነው

**ቦጋለ አበበ**

በአልጄሪያ አስተናጋጅነት ለሚካሄደው የአፍሪካ አገራት ቻምፒዮንሺፕ (ቻን) ዋንጫ ለመሳተፍ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ የደረሰው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ከሩዋንዳ ጋር ለሚጠብቀው የደርሶ መልስ ጨዋታ ዝግጅቱን ከቀናት በፊት ጀምሯል።

ደቡብ ሱዳንን በድምር ውጤት 5-0 አሸንፎ የመጨረሻውን ዙር ማጣሪያ የተቀላቀለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ባለፈው ሐሙስ ተሰባስቧል። በአሰልጣኝ ውበቱ አባተ ጥሪ ከቀረበላቸው ተጫዋቾች መካከል ሱራፌል ዳኛቸው በጉዳት ምክንያት በወንድማገኝ ኃይሉ የተተካ ሲሆን ሙሉ ቡድኑ ሐሙስ እለት በጁፒተር ሆቴል ተሰባስቦ የጂምናዚየም ስራዎችን ከከወነ በኋላ አርብ እለት ወደ አዳማ ተጉዞ በአዳማ ኤክስኪዩቲቭ ሆቴል ማረፊያውን በማድረግ በእለቱ በአበበ ቢቂላ ስታዲየም ከ10:30 ጀምሮ የመጀመሪያ ልምምድ አከናውኗል።

የፊታችን ነሐሴ 20 እና 29 የደርሶ መልስ ጨዋታውን የሚያደርገው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ልምምዱን በአዳማ በመቀጠል ነሐሴ 18 የሜዳ ጨዋታውን ወደሚያደርግበት ታንዛንያ እንደሚያመራ ከኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ከሩዋንዳ ብሔራዊ ቡድን ጋር የሚያደርገው የማጣሪያ ጨዋታ የሚከናወንበት ቀናት እና ቦታዎች በሳምንቱ መጨረሻ ይፋ መደረጉ ይታወቃል። በዚህም በመጀመሪያው ጨዋታ ዋልያዎቹ ባለሜዳ ሆነው ነሐሴ 20/2014 ታንዛንያ ቤንጃሚን ምካፓ ስታዲየም ላይ ጨዋታቸውን የሚያደርጉ ይሆናል። የመልሱን ጨዋታ ደግሞ ነሐሴ 29/2014 ሩዋንዳ ላይ እንደሚደረግ የወጣው መርሐ



**ዋልያዎቹ በቻን ዋንጫ ለሶስተኛ ጊዜ ለመሳተፍ ሩዋንዳን በደርሶ መልስ ውጤት ማሸነፍ ይኖርባቸዋል፤**

ግብር ያሳያል።

በአገር ውስጥ ሊጎች በሚጫወቱ ተጫዋቾች ብቻ በካፍ አዘጋጅነት በየሁለት አመቱ የሚደረገው የቻን የአፍሪካ ዋንጫ ውድድር የማጣሪያ ጨዋታዎች ከነሀሴ ወር መጀመሪያ አንስቶ እየተከናወኑ ይገኛሉ። በቅድመ ማጣሪያ ጨዋታው ከደቡብ ሱዳን ጋር የተደለደለችው የኢትዮጵያ ስቴድየሞች የካፍን መመዘኛ መስፈርት አለማሟላታቸውን ተከትሎ በተጣለው ዕገዳ ልክ እንደ አፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታዎቿ ሁሉ ይህንንም ጨዋታ ከሜዳዋ ውጪ ታንዛኒያ ላይ ለማድረግ ተገዳለች።

የመጨረሻውን የማጣሪያ ጨዋታም ኢትዮጵያ እና ተጋጣሚዋ ሩዋንዳ የካፍን መስፈርት የሚያሟላ ስታዲየም የሌላቸው መሆኑን ተከትሎ እገዳ ላይ ቢገኙም ሩዋንዳ ቀናት በፊት አንድ ስቴድየሟ ጨዋታ እንዲያስተናግድ ፍቃድ ማግኘቱ ታውቋል። ይህንን ተከትሎ ሩዋንዳ ነሐሴ 29 የሚደረገውን የመልስ ጨዋታ በሁዬ ዓለም አቀፍ ስታዲየም እንደምታስተናግድ ይፋ ተደርጓል። ኢትዮጵያ ግን አሁንም ስቴድየሞቿ ፍቃድ ስላላገኙ ከሩዋንዳ ጋር ነሐሴ 20 የሚደረገውን የመጀመሪያ ጨዋታ በታንዛኒያ ዳሬሰላም ቤንጃሚን ምካፓ ስታዲየም እንደምታደርግ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ገልጿል።

በአፍሪካ ከዋናው አፍሪካ ዋንጫ ቀጥሎ ትልቁ የእግር ኳስ መድረክ የሆነው የቻን ዋንጫ በአገር ውስጥ ሊጎች የሚጫወቱ ተጫዋቾችን ብቻ ለማበረታታት በካፍ አማካኝነት እኤአ በ2007 የተዋወቀ ሲሆን 2009 ላይ በኮትዲቯር አዘጋጅነት ለመጀመሪያ ጊዜ ተካሂዷል። ከጊዜ ወደ ጊዜ በውድድሩ የሚሳተፉ አገራት ቁጥርም እያደገ ሄዶ ትኩረት ከሚሰጣቸው የስፖርት መድረኮች አንዱ ሆኗል። የአለምን እግር ኳስ በበላይነት የሚመራው ፊፋም እኤአ 2010 ላይ ለዚህ ውድድር እውቅና ሰጥቶታል።

ኢትዮጵያ ከሰላሳ አንድ አመታት በኋላ እኤአ 2013 ላይ በደቡብ አፍሪካ አዘጋጅነት በተካሄደው የአፍሪካ ዋንጫ መሳተፏን ተከትሎ በእግር ኳሱ የተፈጠረው ከፍተኛ መነቃቃት ይታወሳል። የዚያ ትውልድ ታሪካዊ ተጫዋቾችና የዋልያዎቹ አሰልጣኝ የነበሩት ሰውነት ቢሻው ከአፍሪካ ዋንጫው ማግስት በተመሳሳይ ደቡብ አፍሪካ ላይ በተካሄደው የቻን ዋንጫ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ መሳተፍ ችለዋል። ለዚህ ተሳትፎም የመጨረሻውን የማጣሪያ ጨዋታ ከሩዋንዳ ጋር ከሜዳቸው ውጪ ተፋልመው ማለፋቸው አይዘነጋም። በተለይም በዚያ የመጨረሻ የማጣሪያ ፍልሚያ የዋልያዎቹ ቋሚ ግብ ጠባቂ የነበረው ጀማል ጣሰው ጨዋታው በመለያ ምት እንደሚጠናቀቅ ከአሰልጣኙ ጋር ቀደም ብለው በመግባባት የመለያ ምት የማዳን የተሻለ ብቃት ያለው ግብ ጠባቂ ሲሳይ ባንጫ ተቀይሮ እንዲገባ ማድረጋቸው አይዘነጋም። ሲሳይ ባንጫም ተቀይሮ ገብቶ ሁለት የመለያ ምቶችን በማዳን ዋልያዎቹን ለቻን ዋንጫ ያበቃበት ክስተት የሚታወስ ነው።

ዋልያዎቹ በቀጣዩ የቻን ውድድርም በአሰልጣኝ ዮሐንስ ሳህሌ እየተመሩ በጋቦን በተካሄደው ዋንጫ ላይ መሳተፍ ችለዋል። በሁለቱም ብቸኛ ተሳትፏቸው ግን ከምድባቸው ሳያልፉ ቀርተዋል። ዘንድሮም በመጨረሻው የማጣሪያ ጨዋታ በአሰልጣኝ ውበቱ እየተመሩ ለሶስተኛ ጊዜ ለመሳተፍ የሩዋንዳን ፈተና ለማለፍ ተዘጋጅተዋል።

## ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# የፋይናንስ ወንጀልና ማጭበርበር - በዘመነ ሳይበር ሌላኛው የዓለማችን ስጋት

**ይበል ካሳ**

የፋይናንስ ወንጀል የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ ዩሮፖል "ባልተገባ መንገድ ገንዘብ ወይንም ሥራ ለማግኘት በግለሰቦች ወይንም በተደራጁ የወንጀል ቡድኖች የሚፈጸም ወንጀል ሲሆን ለዚህ ወንጀል መፈጸም ዋነኛው መንስኤም ኢኮኖሚያዊ ጥቅምን ለማግኘት ነው" በማለት ይተረጉመዋል፡፡ ይህም በሕገወጥ መንገድ የሚገኝን ማንኛውንም ገንዘብ ሕጋዊ አስመስሎ መጠቀም(Money Laundering)፣ የታክስ ማጭበርበር፣ የኢንቨስትመንት ሙስናና ባልተገባ መንገድ ገበያን በሞኖፖል መቆጣጠርን የሚያካትት የወንጀል ዓይነት መሆኑን ጃክ ኒኮላስና ሌሎች ተመራማሪዎች አይ.ኢ.ኢ.ኤስ ጆርናል ላይ ያሳተሙት ጥናት ያመለክታል፡፡ ባልተገባ መንገድ ሪል ስቴት ማበልፀግና መግዛት፣ ወይም ኢንሹራንስ ኩባንያዎች ሄዶ አክሲዮን መግዛት፣ ይህ ሁሉ ሒደት "መኒ ላውንደሪንግ" ተብሎ ለመጠራት የሚችል መሆኑንና የፋይናንስ ማጭበርበር ወንጀል መሆኑን መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

በዓለም ላይ አብዛኛው የፋይናንስ ወንጀል የሚፈጸመው በዚሁ የመኒ ላውንደሪንግ መንገድ መሆኑንም ከላይ የጠቀስነው ጥናትም ያመክታል፡፡ ባንኮችና ሌሎች የመንግሥትና የግል የፋይናንስ ተቋማት የእነዚህ የፋይናንስ ወንጀሎችና ማጭበርበሮች ዋነኛ የጥቃት ዒላማዎች ናቸው፡፡ ከዚህ የተነሳ ዘርፉ በትሪሊዮን ዶላር የሚቆጠር መዋዕለ ንዋይ የሚፈስበት ግዙፍ ኢንዱስትሪ እየሆነ መምጣቱን የዓለም ኢኮኖሚ ፎረም መረጃ ያመላክታል፡፡ በዚህም የግል የፋይናንስ ተቋማት ለዘርፉ ፈተና እየሆነ የመጣውን በመኒ ላውንደሪንግ የሚፈጸም የፋይናንስ ወንጀል ለመቆጣጠር በአውሮፓውያኑ 2017 ዓመት ብቻ ስምንት ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ ወጪ ማድረጋቸውን የዓለም ኢኮኖሚ ፎረምን መረጃ ዋቢ አድርጎ ማክኪንሲ ኤንድ ካምፓኒ ያወጣው ጥናት ይገልጻል፡፡

በአውሮፓውያኑ አቆጣጠር ጃኑዋሪ 1 ቀን 1983 ያለምንም ቁሳዊ ገመድ ኮምፒውተሮችን በያሉበት እርስበእርስ የሚያስተሳስረው በመጀመሪያ "ትራንስፈር ኮንትሮል ፕሮቶኮል/በኋላ ኢንተርኔት ፕሮቶኮል" የተባለው የመገናኛ ዘዴ ሥራ ላይ መዋሉን ተከትሎ ባለፉት አራት አስርታት ደግሞ ከምንጊዜውም በላይ ወንጀሉ በከፍተኛ ፍጥነት እየተስፋፋ መምጣቱን መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ምክንያቱም የፋይናንስ ወንጀለኞቹ የበይነ መረብ ቴክኖሎጂንና የሳይበር ምህዳር የፈጠረላቸውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም ወንጀሉን በቀላሉ የሚፈጽሙበት ዕድል ስለተፈጠረላቸው ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት በዓለም ላይ አብዛኛው የሳይበር ጥቃት የሚፈጸመውም ገንዘብ ወይንም ያልተገባ የኢኮኖሚ ጥቅም ለማግኘት መሆኑም ለዚህ ጥሩ ማሳያ ነው፡፡ በዚህም በዓለም ዙሪያ ከሚፈጸሙ የሳይበር ጥቃቶች 75 በመቶ የሚሆነውን ድርሻ የሚይዘው ገንዘብ ለማግኘት የሚደረገው ጥቃትና በፋይናንስ ወንጀለኞች የሚፈጸመው የሳይበር ጥቃት መሆኑን መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

የበይነ መረብ ቴክኖሎጂ በከፍተኛ ደረጃ እያደገ መምጣቱን ተከትሎ የፋይናንስ ወንጀለኞች የሚፈጽሙት ጥቃትም እንዲሁ በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ የመጣ ሲሆን፣ ጉዳዩ ዓለማችንን ከባድ ዋጋ እያስከፈላት ይገኛል፡፡ በዚህ ረገድ የፋይናንስ ወንጀለኞች አብዝተው ከሚጠቀሙባቸው የፋይናንስ ሳይበር ጥቃቶች መካከል ዋነኛው ዘዴ ክሪፕቶ ከረንሲ ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል፡፡ ከላይ በተጠቀሰው የጃክ ኒኮላስና ጓደኖቹ የይ.ኢ.ኢ.ኢ. ጥናት መረጃ መሠረት ዓለም ላይ ከሚፈጸሙ የፋይናንስ ወንጀሎችና ማጭበርበሮች ስድሳ በመቶው የሚፈጸመው "ዲሴንትራላይዝድ ፋይናንስ" በተባለው የክሪፕቶ ከረንሲ ዘዴ ነው፡፡ በዚህም እስከ አውሮፓውያኑ ሚያዚያ 2021 ብቻ በክሪፕቶ ከረንሲ በሚፈጸም የፋይናንስ ወንጀልና ማጭበርበር ዓለማችን 432 ሚሊዮን ዶላር አጥታለች ወይንም ተዘርፋለች፡፡

ክሪፕቶ ከረንሲ ገንዘብ የማምረትና የማዘዋወር ስልጣን ከብሔራዊ ባንኮችና ከመንግሥታዊ ስርዓት አውጥቶ ለግለሰቦች ለመስጠት ያለመ አሠራር በመሆኑ በዚህ መንገድ እየተፈጸመ ያለው የፋይናንስ ወንጀልና የሳይበር ጥቃት ለባንኮችና የሌሎችም ሃገራዊና ዓለም አቀፋዊ የፋይናንስ ተቋማት ህልውና አደጋ ውስጥ እንዲወድቅ እያደረገው ይገኛል፡፡ ይህም በማክሮ ኢኮኖሚክ ደረጃ ቀውስ የመፍጠር አቅም ያለው በመሆኑ አጠቃላይ በዓለም የኢኮኖሚ ሥርዓት ላይ ከፍተኛ ስጋትን ደቅኗል፡፡ በዚህም ዲጂታል ገንዘብ ወይንም ክሪፕቶ ከረንሲ በግለሰቦች ይሁንታና ስምምነት እንጂ በሕግ ወይንም ኃላፊነት ባለው አካል ወይንም መንግሥት የማይመራ በመሆኑ አጠቃላይ የፋይናንስ ሥርዓቱ ወንጀልና ሽብርተኝነትን ጨምሮ ለተለያዩ ሕገ ወጥ ተግባራት እንዲጋለጥ ምክንያት ሆኗል፡፡

በሩስያና ዩክሬን ጦርነት ላይ ዲጅታል ገንዘቦች በሰፋት ጥቅም ላይ እየዋሉ መሆናቸውም ለዚህ ጥሩ ማሳያ ነው፡፡ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በዓመት 72 ቢሊዮን ዶላር የሚሆኑ የቢትኮይን ግብይቶች ለሕገወጥ ግብይት ይውላሉ፡፡ በአጠቃላይ በቢትኮይን ከሚደረገው ግብይት 44 በመቶ የሚሆነው ጥቅም ላይ የሚውለው ለአደንዛዥ ዕፅ ዝውውር፣ ሽብርተኝነትን ለመደገፍ፣ ለሕገወጥ የገንዘብ ዝውውርና ለሌሎች ወንጀሎች መፈጸሚያ መሆኑንም እነዚሁ ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡

ሌሎች የፋይናንስ ሳይበር ወንጀል መፈጸሚያ መንገዶች ቢኖሩም ከክሪፕቶ ከረንሲ ቀጥሎ ዋነኛ ወንጀሉ መፈጸሚያ መንገድ የሆነው ደግሞ መረጃዎችንና የኮምፒውተር ስርዓቶችን በመቆለፍና አግቶ በመያዝ ገንዘብ የሚያስከፍለው ራንሰምዌር የተባለው የፋይናንስ ወንጀል መፈጸሚያ የሳይበር ጥቀት ነው፡፡ ልክ እንደክሪፕቶ ከረንሲ ሁሉ ይህም ጥቃት በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረና ለዓለማችን ስጋት እየሆነ የመጣ ሲሆን እስከፈረንጆቹ 2021 መጨረሻ ድረስ በዓለማችን ላይ ከደረሰው ጠቅላላ የራንሰምዌር ጥቃት ኪሳራ ሃያ ቢሊዮን ዶላር መድረሱንና በሚቀጥሉት አስር ዓመታት ውስጥ እስከ 2031 ደግሞ ይኸው አሃዝ 265 ቢሊዮን ዶላር ሊደርስ እንደሚችል በተለያዩ የሳይበር ደህንነት ጠበብቶችና ተቋማት የተቀመጡ ግምቶች ያመላክታሉ፡፡

ስለሆነም የሰው ልጅ በየጊዜው በከፍተኛ ደረጃ በማደግ ላይ ያለውን አጠቃላይ የሳይበር ጥቃትና የፋይናንስ ወንጀል ለመከላከልና ራሱን ከጥፋት ለማዳን ቆም ብሎ ሊያስብ ይገባዋል፡፡ ለዚህም የዘርፉ ምሁራን ሦስት መሠረታዊ መፍትሔዎችን ይመክራሉ፡፡ እነዚህም አንደኛ እንደከዚህ በፊቱ ለጥቃት ምላሽ በመስጠት ላይ የተመሠረተ ሳይሆን አስቀድሞ በመከላከል ላይ የተመሠረተ ንቁና ወዲያውኑ ምላሽ መስጠት የሚያስችል(Real time prevention) የሳይበር ደህንነት ሥርዓትን መዘርጋት፡፡ ሁለተኛ በግለሰብ፣ በተቋም በሀገር፣ በቀጣናና በአህጉር ደረጃ ከሚደረግ የተናጠል የሳይበር ደህንነት ሥርዓት ይልቅ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተቀናጀና ሁሉንም ያካተተ(Wholistic) የሳይበር ደህንነት ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ፡፡ ሦስተኛ የሳይበር አጥቂዎቹ የደረሱበትን ደረጃ የሚመጥን፣ ዘመኑን የሚዋጅ ስልጡን የሳይበር ደህንነት ቴክኖሎጂን መጠቀም ለዚህም ቴክኖሎጂው የሚፈልገውን ሁሉ ለማሟላት በቂ በጀት፣ የሰው ኃይልና የአሠራር ማዕቀፍ ለመቅረጽና ለመተግበር ቁርጠኛ መሆን ናቸው፡፡